ብርቱዎችን ማስልጠን፣ ደካማዎችን መደገፍ (መርዳት) ይገባቸዋል። ከሚሰማሟቸው፣ አገልግሎታቸውን ከሚቀበሉት ጋር መተባበር የሰው ሁሉ ተፈጥሯዊ ፍላጎት እንደሆነ ግልጽ ነው። ይሁን እንጂ፣ አስቸጋሪ ናቸው የሚባሉትንም እንዳይገፉ ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው። አስቸጋሪ የሆኑትም ሰዎች የመሪዎቻቸው ፍቅርና በርህራኄ የተሞላ ልብ ያስፈልጋቸዋል። አስቸጋሪ የነበሩ ሰዎች ተለውጠው አንድ ቀን ፍሬያማ አገልጋዮች ሊሆኑ እንደሚችሉ መዘንጋት የለባቸውም። ይሁን እንጂ፣ ጊዜያቸውን፣ ጉልበታቸውን አሟጠው ሊጨርሱባቸው ከሚችሉ አንዳንድ አስቸጋሪ ሰዎች ራሳቸውን መጠበቅ እንዳለባቸው ማወቅ አለባቸው። ኢየሱስ በምድራዊ አገልግሎቱ አስቸጋሪ ሰዎችን ሳይገፋ፣ ፍሬያማ የሆኑትን ደቀ መዛሙርቱን ሚዛኑን ያልለቀቀ ጊዜ በመስጠት ለአገልግሎት ያዘጋጅ ነበር።

ኢየሱስ የግል ሕይወቱን፣ ጊዜውን ሙሉ በሙሉ በማካፈል ደቀ መዛሙርቱን ለአገልግሎት ያዘጋጃቸው ነበር። ደቀ መዛሙርቱም ከኢየሱስ የተማሩትን መልሰው የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ያስተምሩ ነበር። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሌሎችን ለአገልግሎት ማዘጋጀት ከኃላፊነታቸው አንደኛውና ትልቁ እንደሆነ በግልጽ አናያለን። የእግዚአብሔር ዕቅድ ይህን ይመስላል። የዘመኑ መንፈሳዊ መሪዎች ኢየሱስ የእርሱን ምሳሌነት እንዲከተሉ ይፈልጋል። ከእግዚአብሔር በአደራ የተቀበልነውን ኃላፊነት፣ ሌሎችን በማበታጠቅ ለወንጌል አደራ ሰናበታ በእኛ ትከሻ ላይ ያለውን ኃላፊነት ማቃለላችን ብቻ ሳይሆን፣ የወንጌል መልዕክት ለሚቀጥለው ትውልድና በዓለም ዙሪያ እንዲሰፋ ማድረጋችን እንደሆነ ማወቅ አለብን። በተጨማሪ "የበጎቹ ዋና እረኛ የሆነውን ኢየሱስን ምሳሌነት እየተከተል ነው ወይ?" በማለት ራሳችንን መጠየቅና በጥንቃቄ መመርመር አለብን።

## ምዕራፍ ፲

# ግጭት አርጋቢነት

"በእናንተ ዘንድ ጦርና ጠብ ከወዴት ይመጣሉ? በብልቶቻችሁ ውስጥ ከሚዋጉ ከእነዚህ ከምኞቶቻችሁ አይደሉምን? ትመኛላችሁ ለእናንተ አይሆንም ትገድላላችሁ፣ በብርቱም ትፈልጋላችሁ ልታገኙም አትችሉም፤ ትጣላላችሁ፣ ትዋጉማላችሁ፣ ነገር ግን አትለምኑምና ለእናንተ አይሆንም…" (ያዕ. 4፥1-2)።

"በሰላም ተሳስራችሁ ከመንፈስ ቅዱስ የሚገኘውን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ።" (ኤፌ. 4፥3)

"የሚቻላችሁ ቢሆን ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ለመኖር በእናንተ በኩል የሚያስፈልገውን ሁሉ አድርጉ" (ሮሜ 12፥18)።

ሰው ተቀራርቦ ሲኖር፣ አንዳንድ ጊዜ በተለያየ ምክንያት በሀሳብ መስማማት አቅቶት መጋጨቱ የማይቀር ነው። በማያምኑት ሰዎች መካከል ብቻ ሳይሆን፣ አማኝ በሚባሉት ሰዎች መካከልም ግጭት ሊፈጠር ይችላል። ከቤተ ክርስቲያን ውጪ በሆነ ሕብረት ውስጥ ብቻ ሳይሆን፣ በቤተ ክርስቲያንም ውስጥ፣ በአማኞች መካከልም ግጭት ሊፈጠር ይችላል። ሰላም ይኖራል ተብሎ በሚታሰብበት፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዴት ግጭት ይኖራል? ካለስ የግጭቶቹ ምክንያቶች ምን ይሆን? አንዳንድ አስቸጋሪ

ሰዎች በመኖራቸው ምክንያት ይሆን? ግጭታችንን በአግባቡ መሥመር ማስያዝ ብንችል መልካም ነገር ከግጭታችን ውስጥ ማግኘት እንችል ይሆን? መንፈሳዊ መሪ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚፈጠሩትን አንዳንድ ግጭቶች ለማርገብ መውሰድ ያለበት እርምጃዎች ምንድናቸው? በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ለእነዚህና እነዚህን ለመሳሰሉ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ሞክረናል። የመንፈሳዊ መሪ በአመራሩ ያለው ብርታትና አስተዋይነት የሚታወቅበት አንደኛው መለኪያ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚፈጠሩትን አንዳንድ ግጭቶች ለማርገብ በሚወስዳቸው እርምጃዎች ነው። የአመራር ችሎታው የሚለካው ሁሉም መልካም በሚሆንበት፣ በሰላሙ ጊዜ ብቻ ሳይሆን፣ ሕብረቱን ፈታኝ የሆነ ነገር ሲያጋጥመው፣ በአማኞች መካከል ግጭት ሲፈጠርም ነው። በግጭት ውስጥ ማለፍ መጥፎ ነው፤ የበለጠ የከፋ የሚሆነው ግን፣ ግጭት እያለ "ግጭት የለም" ብሎ መካድ፣ እንዲሁም በግጭቱ ውስጥ ያለፉ ሰዎች ከግጭታቸው ምንም ዓይነት ትምህርት ሳይማሩበት የቀሩ እንደሆነ ነው።

በሐዋርያት ዘመን የነበረችው የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ገና እንደተመሠረተች፣ አማኞች ሁሉ በሕብረትና በሰላም አብረው ይኖሩ ነበር። ሉቃስ "*ያመኑት ሁሉ በአንድነት ነበሩ፤ ያላቸውንም ሁሉ የጋራ አደረጉ። ሀብታቸውንና ንብረታቸውንም እየሸጡ ለእያንዳንዱ ሰው የሚያስፈልገውን ያህል ይሰጡት ነበር*" (የሐዋ. 2፥44-47) ይላል። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ለምን ያህል ጊዜ በሰላም እንደኖሩ አናውቅም። ይሁን እንጂ፣ የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 6 ላይ ሁኔታው መልኩን ለውጦ እናያለን። የደቀ መዛሙርቱ ቁጥር እየጨመረ ሲሄድ፣ ያን በመሰለ አንድነት ውስጥ አንዳንድ ቅሬታዎች መፈጠር ጀመሩ። ችግሩን የፈጠሩት ውጪ ያሉት ሰዎች ሳይሆኑ፣ አንድነቱ ውስጥ የነበሩ አማኞች ናቸው። "*...ከግሪክ አገር የመጡ አይሁድ በይሁዳ ይኖሩ በነበሩት አይሁድ ላይ አጉረመረሙ፤ ምክንያቱም በየዕለቱ በሚከናወነው ምግብ የማደል አሠራር ላይ ከእነርሱ ወገን የሆኑት መበለቶች ችላ ተብለው ነበር*" (የሐዋ. 6፥1)። በዚህ ዓይነት አንዳንዶቹ በመካከላቸው "አድሎ" እንዳለ ስለተሰማቸው ቅሬታቸውን ማሰማት ጀመሩ። ሐዋርያትም በወቅቱ በመካከላቸው የተፈጠረውን ቅሬታ ሰምተው "ሁኔታውን ጊዜ ይፈታዋል" በማለት ችላ ብለው በማለፍ ፈንታ፣ ፈጣን የሆነ እርምጃ ወሰዱ። በዚህ ዓይነት ከቀጠለ የቤተ ክርስቲያናቸው ዓላማ ይጨናገፋል ብለው በማሰብ፣ ችላ የተባለው አገልግሎት እንደሚገባው መፈጸም እንዲችሉ አንዳንድ እርምጃዎችን ወሰዱ። ሐዋርያት ቃሉን በማስተማር እንዲተጉ፣ የማዕዱን አገልግሎት እንዲመሩ ከመካከላቸው ሰባት ሰዎች መርጠው በሐዋርያት ፊት አቀረቧቸው። ሐዋርያትም ከጸለዩ በኋላ እጃቸውን ጭነው ለአገልግሎት ለዩአቸው (የሐዋ. 6፥2-6)። እነዚያ ሰባት ሰዎች ከተመረጡ በኋላ ችላ ተብሎ የነበረው አገልግሎት እንደሚገባ መካሄድ ሲጀምር፣ ቀደም ሲል የነበረው ቅሬታ ከመካከላቸው ጠፋ። ከዚህ በኋላ ሌሎች ችግሮች አልተፈጠሩም ማለት



አይደለም። የእግዚአብሔር ቃል እየሰፋ፣ የደቀ መዛሙርቱም ቁጥር እየበዛ ሲመጣ፣ በዚያው መጠን ግጭታቸውም እየጨመረ መጣ።

በሐዋርያት ዘመን እንደነበረው በእኛም ዘመን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ግጭት ወይም አለመስማማት አለ። ቤተ ክርስቲያን ከግጭት ነጻ የሆነችበት ጊዜ የለም። ኃጢአት በበዛበት ዓለም ውስጥ እስከኖርን ድረስ፣ ዛሬም ሆነ ወደፊት፣ ከግጭት ሁሉ ነጻ ሆነን መኖር አንችልም። ክርስቲያኖች በመሆናችን ብቻ ከግጭት ሁሉ ነጻ ሆነን እንኖራለን ብሎ ማሰብ ትክክል አይደለም። ከሰዎች ጋር ባለን ግንኙነት ውስጥ፣ በምንሰጠው ሀሳብም ሆነ አስተያየት፣ በምንመርጠው ምርጫችንና፣ እንዲሁም በምንወስነው ውሳኔ እስከተለያየን ድረስ፣ የሌላው አሳብና ስሜት በግልጽ መረዳት እስካልቻልን ድረስ፣ ክርስቲያኖች በመሆናችን ብቻ፣ ምንጊዜም ቢሆን ከግጭት ሁሉ ነጻ ሆነን መኖር አንችልም። በክርስቲያኖች መካከል አለመስማማት ወይም ግጭት የማይኖር ቢሆን ኖሮ፣ ኢየሱስ በተራራው ስብከቱ "*የሚያስታርቁ ብፁዓን ናቸው...*" (የማቴ. 6፥9) በማለት ባላስተማረም ነበር። ግጭት (አለመስማማት) በግለሰብ መካከል ብቻ ሳይሆን፣ በማኅበር ወይም በድርጅትም ውስጥ ሊፈጠር የሚችል ነው። ቤተ ክርስቲያንም የክርስቶስ አካል ብትሆንም፣ ከግጭት ነጻ አይደለችም። ግጭታቸውን ወይም አለመስማማታቸውን በአግባቡ መሥመር ማስያዝ ካልቻሉ፣ አማኞችም ሆኑ መንፈሳዊ መሪዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚፈጠሩት አንዳንድ ግጭቶች ምክንያት እንደሚጎዱ የታወቀ ነው። *ምንወየላት* በአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ፣ በሽምግልና የሚያገለግል ወንድም ነው። ቤተ ክርስቲያኒቷ ውስጥ በአንድ አማኝ ምክንያት የደረሰበትን የስሜት ጉዳት ሲገልጽ፤

> *"...ስለ እኔ መጥፎ ወሬ የሚያስወራውን ሰው ማንነቱን ባላውቀውም፣ ከአዕምሮዬ ፈጽሞ ላስወጣው አልቻልኩም። ቀንም፣ ማታም፣ ሌሊትም ወደ አዕምሮዬ ይመጣል። መጀመሪያ ላይ ራሴን እታዘበው ነበር። በየቦታው ስለ እኔ የሚያወራው ክፉ ነገር እየበረከተ መጣ። 'ችላ ብዬ ብተወው ከአዕምሮዬ ይጠፋል' ብዬ በማሰብ ሁኔታውን ችላ ብዬ ለማለፍ ሞከርኩ፤ ይሁን እንጂ ከአዕምሮዬ ላስወጣው አልቻልኩም። ይኼ ሰው በእኔ ላይ የሚያወራው አሉባልታ እየሰፋና ለሰው ጆሮ የሚሰቀጥጥ ሆኖ ባገኘውም፣ ለቄ ለማለፍ ሞከርኩ። መጨረሻ ላይ ይኼ ሰው ማን እንደሆነ አወቅሁ። ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሳየው፣ በውነቴ ለውጥውጥ ይልብኛል። ሊያስታውሰኝ ይደርሳል። ሥጋዊው ተፈጥሮዬ ያንን ሰው "አንገቱን አነቀው...አነቀው" ይለኛል። ውስጤ በቁጣና በንዴት ይሞላል። ይህ ሰው በአሉባልታው ብዙ የጎዳኝ ሰው በመሆኑ፣ ቀስ በቀስ ውስጤ በምሬትና በጥላቻ እየተሞላ መጣ። በዚህ ዓይነት ስሜት ውስጥ ተሞልቼ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ፣ ሁሉም ነገር ሰላም እንደሆነ ለማምሰል መሞከሬ የበለጠ የበደለኛነት ስሜት እያጠቃኝ መጣ። እለፍ እለፍ ለዚህ ሰው ፍቅር ባሳየው፣ አንዳንዱንም*

*ሁኔታ ባስረዳው ሁኔታው ይለውጥ ይሆናል ብዬ ማሰቤም አልቀረም። ምናልባት ጥሩ ክርስቲያን ባለመሆኔ ይሆናል፤ ይህንን ሰው ደፍሬ ማነጋገር ያቃተኝ ብዬም አሰብሁ። በእኔና በዚህ ሰው መካከል እኔ ብቻ ሳልሆን ቤተ ክርስቲያንም ተጎድታለች። የተሻለ የሚሆነው እኔ ከሽምግልና አገልግሎቴ ብወርድ ነው፤ ይሄ ከሆነ ምናልባት ቤተ ክርስቲያኒቱ አገልግሎቷን በሰላም መቀጠል ትችል ይሆናል ብዬ አሰብኩ። ይህንኑ ባደርግ ሁልጊዜ ይህን ሰው እያየሁ በዚህ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መቀጠል እንዴት እችላለሁ? ይሄ ነገር በጣም እየጎዳኝ ስለመጣ ዕንቅልፍ በቅጡ አይወስደኝም፤ ጨጓራዬም እየተላጠ ነው" አለ።*

ጤናማ ያልሆነ ግጭት፣ እንደ ምንወየለት ልብን በመራራነትና በጥላቻ ይሞላል። ይህን ዓይነቱ ሁኔታ ሲፈጠር የሚጎዳው አንድ ሰው ብቻ ሳይሆን፣ የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያንም ጭምር ነው። ይህን ዓይነቱ ጤናማ ወይም ገንቢ ያልሆነ ግጭት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መከፋፈልን፣ እርስ በርስ መለያየትን ይፈጥራል። ጤናማ ያልሆነ ግጭት የሚጎዳው ምዕመኑን ብቻ ሳይሆን፣ የቤተ ክርስቲያኒቱን ዋና መሪ ወይም መጋቢ የሆነውንም ሰው ጭምር ነው። ፓስተር ታፈሰ ስሜቱን ሲገልጽ፥

*"አስቸጋሪ ስለሆነብኝ ሰው ባሰብሁ አንዳንድ ጊዜ በጣም እናደዳለሁ። በዚህ ሰው ምክንያት በቤተ ክርስቲያኒቱ ምዕመናንም ሁሉ ላይ የምቆጣበት ጊዜ አለ። ይሄ ሰው ሲያስቀየኝ እያዩና እየሰሙ አንድ ነገር የማያደርጉት ለምንድነው? ብዬ በሽማግሌዎችም ላይ የምቆጣበት ጊዜ አለ። ራሴንም በመጥላት፣ በራሴ የማዝንበትና የምቆጣበት ጊዜ አለ። ይሄ እንዲህ እንዲሆን ለምን ፈቀደ ብዬ በእግዚአብሔርም ላይ የምቀየምበትም ጊዜ አለ። ብዙ ጊዜ ይህን ሁኔታ መቋቋም ያቅተኝ ይሆን? እንዲሁም ምዕመኑ ምን ያስብ ይሆን? በማለት ውስጤ በፍርሃት ይሞላል። አገልግሎቴን ትቼ ብወጣ 'ቤተሰቤን በምን አስተዳድራለሁ' በማለት ፍርሃት ቢለቀኝም፣ ብዙ ጊዜ ሁሉንም እርግፍ አድርጌ ጥዬ 'እግዚአብሔር ሆይ! አሁንስ አቃተኝ! በቃኝ! አንተ እንደሆንክ ስለ እኔ ግድ የለህም! ፍጹም ረስተኸኛል!' በማለት ከአገልግሎት ለመውጣት ይቃጣኛል። ቁጭ ብዬ ለራሴ ማልቀሱ ውጤት እንደሌለው አውቃለሁ። ያንን ሰው የመበቀል ስሜት በውስጤ እያየለ ሲመጣ፣ የበለጠ ሀፍረት ይሰማኛል። ይሄ ሁኔታ ሕይወቴን ጨምድዶ ስለያዘው ያለዕንቅልፍ የማድርባቸው ሌሊቶች እየበረከቱ መጡ። አንዳንድ ጊዜ "ባብድ ነው" ብዬ የማስብበትና የምፈራበትም ጊዜ አለ።...ምን ማድረግ እንዳለብኝ አሁንስ ግራ ገባኝ!" አለ።*

ጎጂ የሆነ ግጭት የመንፈሳዊ መሪውንም ሕይወት ምን ያህል እንደሚያስመርር መጋቢ ታፈሰ በሰጠው አስተያየት መረዳት እንችላለን። ቤተ ክርስቲያን ውስጥም በራስ



ወዳድነት፣ በተንኮል መንፈስ የተሞሉ የእግዚአብሔርን ሕዝብንም ሆነ አገልጋዩን የሚያጠቁ ሰዎች እንዳሉ ማወቅ ይጠቅማል። በአብዛኛው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሚፈጠሩት ግጭቶች ምክንያት የሚሆኑት ሰዎች በቁጥር ጥቂቶች ናቸው። በሁለት ኃይሎች መካከል የሚደረጉ ሁለት ዓይነት ጦርነቶች አሉ። አንደኛው በሁለቱም ወገን ሠራዊታቸውን አሠልፈው፣ የሚያጠቁበትን መሣሪያ ይዘው ፊት ለፊት ገጥመው የሚዋጉበት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ የጎሬላ ወይም የደፈጣ ውጊያ ነው። ከመጀመሪያው ይልቅ ሁለተኛው የበለጠ አደገኛና ከባድ ነው። የጎሬላ ውጊያ የሚያካሂዱት ቁጥራቸው በጣም አነስተኛ ቢሆንም፣ የማጥቃት ዘዴያቸው ከጠላት ጋር ፊት ለፊት በመግጠም ሳይሆን፣ "መትቶ መሮጥ" ነው። ይህን በሚመስል ጦርነት ውስጥ አሸንፎ ውጊያውን ከመጨረሻ ደረጃ ማድረስ አይቻልም። የቤተ ክርስቲያንም ጦርነት አንዳንድ ጊዜ የጎሬላ ጦርነት ይመስላል። ውጊያውን የጀመሩትና የሚያካሂዱት ማንነታቸው በግልጽ አይታወቅም። ሰላማዊ መስለው ያመልካሉ፣ ያገለግላሉ፣ ይሰብካሉ። በዚህ ዓይነት ውስጥ የሚያገለግሉ መንፈሳዊ መሪዎች መቀጠል የሚችሉት እንዴት ነው? አገልግሎታቸውን የሚፈጽሙት "ጦረኛ" ወይስ "ገንቢ" ሆነው ነው?

## 1. ዳዊትንና ሰሎሞንን የሚመስሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አሉ

በብሉይ ኪዳን ውስጥ አባትና ልጅ፣ ይኸውም ዳዊትና ሰሎሞን በራሱ በእግዚአብሔር ተመርጠውና ተቀብተው የእስራኤል ንጉሥ ሆነው ተራ በተራ አገሪቱን ይመሩ እንደነበረ እናውቃለን።

### 1.ሀ. ዳዊትን የሚመስሉ በትግል ውስጥ የሚያልፉ መሪዎች

ዳዊት ዘመኑን ሁሉ ያሳለፈው "ጦረኛ" ሆኖ ነው። ብዙ ደም አፍሷል። ለእግዚአብሔር መኖሪያ እንዲሆን ቤተ መቅደስ ለመሥራት ፈልጎ እግዚአብሔር *"ብዙ ደም በእጅህ ፈሷልና ቤተ መቅደስ ለእኔ አንተ አትሠራልኝም"* ብሎ እንደከለከለው እናውቃለን። ሰሎሞን ግን የነገሠው አገሪቱ ፍጹም ሰላም በነበረችበት ዘመን ነበር። እንደ አባቱ እንደ ዳዊት ብዙ ደም አላፈሰሰም። እግዚአብሔርም አባቱ ዳዊት ሊሠራለት ያሰበውን ቤተ መቅደስ ሰሎሞን እንዲሠራለት መፍቀድ ብቻ ባይሆን፣ ሀብትን፣ ማስተዋልንና ጥበብን ጨምሮ ሰጠው። ሠለሞን ቤተ መቅደሱ ሲገነባ፣ መሠረቱ ከተጣለበት ጊዜ ጀምሮ ገንባታው እያደገ ሲሄድ፣ በመጨረሻም ቤተ መቅደሱ ተሠርቶ አልቆ የእግዚአብሔር ክብር በኃይል ሲገለጥ በዓይኑ የማየት ዕድል አጋጥሞታል። ብዙ አገልጋዮች በአገልግሎታቸው ዘመን እንደ ዳዊት "በውጊያ" ውበጥ፣ ወይም እንደ ሰሎሞን፣ አንዳንዶቹ ደግሞ በሁለቱም ዓይነት ሁኔታዎች ውስጥ የሚያስልፉ አሉ። አንዳንዴ "ጦረኞች" ሌላ ጊዜ ደግሞ "ገንቢዎች" ሆነው የሚያልፉ እሉ።

አንዳንድ መንፈሳዊ መሪዎች (መጋቢዎች) የዳዊትን ዓይነት ሚና የሚጫወቱ አሉ። በአንዳንድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተደም ሲል የነበረ፣ ሥር የሰደደ የሥልጣንና የደረጃ መዋቅር ላይ ያሉ፣ በግልጽም ሆነ በተዘዋዋሪ ቤተ ክርስቲያኒቷን በእነርሱ ቁጥጥር ውስጥ ያደረጓት አንዳንድ ሰዎች አሉ። ከነዚህ ውስጥ አንዳንዶቹ "ቤተ ክርስቲያኒቷን የጀመርነው እኛ ነን" የሚሉ ናቸው። በለሆነም እነዚህ ሰዎች በመሪነት ሥፍራ ላይ የተቀመጡ ባይሆኑ እንኳ፣ እነርሱ የማይፈቅዱት ለውም ሆነ ምንም ዓይነት አገልግሎት በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ እንዲኖር አይፈልጉም። የቤተ ክርስቲያን መሪው (መጋቢው) እነዚህ ጥቂት የተወሰኑ በዎችን ለማስደሰት ብሎ ከመሥመር አልወጣም የሚል፣ እግዚአብሔር በሰጠው ራዕይ መሠረት ብቻ ቤተ ክርስቲያኒቷን ለመምራት የሚፈልግ ከሆነ፣ ሁኔታውን የሚያውቁ አንዳንድ ክርስቲያኖች ያንን ሰው የሚያዩት እንደ ተዋጊ ነው። ለቤተ ክርስቲያኒቷ ዕድገት በማለብ፣ በቅድስና የማይኖሩትን አማኞች የሚገስጽ፣ አንዳንድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑትን ልምምዶች ለማስቀረት ጥረት ሲያደርግ ትልቅ ተቃውሞና ትግል ሊያጋጥመው ይችላል። አገልግሎቱ ሁልጊዜ የትግል ወይም የጦርነት አገልግሎት ይሆናል። እንዲህ ዓይነት መንፈሳዊ መሪዎች እነርሱን ከፍተኛ ዋጋ ቢያስከፍላቸውም፣ ለእግዚአብሔር ሥራ የሚቆረቆሩ ከሆኑ፣ ሁሉንም ታግሰው፣ እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል ሲሠራ ማየትን ይመርጣሉ። እንደ ዳዊት በጦርነት ውስጥ ሆኖ መምራት አልፈልግም በማለት ጥለው የሚሄዱም አሉ። ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጦርነት ቢኖርም፣ በጦርነት ውስጥ ታግሎ መቆየትም የሚያስፈልግበት ጊዜ አለ። ዳዊት የእግዚአብሔር መኖሪያ የሆነው መቅደስ ተሠርቶ አልቆ፣ የእግዚአብሔር ክብር በሙላት ሲገለጽ አይይ እንጂ ለግንባታው ጠቃሚ የሆኑ ዝግጅቶችን ሁሉ ለማድረግ ምክንያት እንደ ሆነ እናውቃለን። እንደ ዳዊት "በውጊያ" ውስጥ የሚያልፉ መንፈሳዊ መሪዎች ማስተዋል ያለባቸው ነገሮች አሉ፥

◆ **1ኛ) ቤተ ክርስቲያን እንድትታነጽ፥ የመሠረት ድንጋይ ጣይ መሆናቸውን**

የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንም በአንድ ሰው መሪነት ተጀምራ፣ ከሙሉ የዕድገት ደረጃ ደርሳ የእግዚአብሔርን ክብር ማንጸባረቅ የምትችልበት ጊዜ አለ። ዳዊት ልጁ ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን ለመሥራት እንዲችል ቅድሚያ ዝግጅት እንዳደረገለት ሁሉ፣ ቤተ ክርስቲያንም ውስጥ መሠረት የሚጥሉ፣ የሚያንጹ የተለያዩ አገልጋዮች ይኖራሉ። ጳውሎስ ለቆሮንቶስ በጻፈው መልዕክቱ *"እኔ ተከልሁ፤ አጵሎስ ውሃ አጠጣ፤ ያሳደገው ግን እግዚአብሔር ነው"* (1 ቆሮ. 3፥6) ሲል፣ ይህንኑ አባብ መግለጹ ነው። አንድ መንፈሳዊ መሪ በአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አገልግሎቱን ሲሰጥ ብዙ ዋጋ ቢከፍልም፣ ለዚያች ቤተ ክርስቲያን ሕልውና መሠረት በመጣል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረገ መሆኑ መዘንጋት የለበትም። እርሱ ከሄደ በኋላ ቤተ ክርስቲያኒቱ በብዙ አቅጣጫ ዕድገት ብታሳይ፣ ዕድገቱ የመጣው እርሱ በመሄዱ ሳይሆን፣ እርሱ መስዋዕት ሆኖ



በከፈለው ከፍተኛ ዋጋ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል መታወቅ ያለበት ይመስለናል። ከጥንት መንፈሳዊ አባቶች መካከል አንዱ፣ ተርቱልያን የተባለው ሰው፣ *"የሰማዕታት ደም የቤተ ክርስቲያን ዘር ነው"* የሚል ምሳሌያዊ አባባል ጽፏል። የአንዳንድ መንፈሳዊ መሪዎች ደም እንደ ሰማዕታት ሲፈስ ባይታይም፣ ከዚያ ባላነሰ መከራ ውስጥ አልፈው አገልግሎታቸውን እንዳኪያሄዱ ግልጽ ነው። ስለዚህ አገልጋዩ ወደ ሌላ ሥፍራ ሲሄድ *"ጌታ ነቀለልኝ..."* ከማለት *"ለቤተ ክርስቲያናችን መሠራት እከሌ ቀደም ሲል ዋጋ ከፈለልን..."* ማለቱ የተሻለ ይሆናል።

◆ **2ኛ) በሕይወታቸው ላይ ከሚደርሰው ነገር ይልቅ፥ በውስጣቸው ስለሚሆነው ነገር የበለጠ የሚያስብ መሆኑን**

እግዚአብሔር ለክብሩ አገልጋዮቹን በሰፊው ከመጠቀሙ በፊት፣ መንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲበጅ፣ የክርስቶስ ውብት በሕይወታቸው ውስጥ እንዲቀረጽ ይፈልጋል። "አገልግሎቴ ትግል የበዛበት ለምን ይሆናል?" ብለው የሚጠይቁ አንዳንድ መንፈሳዊ መሪዎች ቢኖሩ፣ ከዳዊት ሕይወት ትምህርት መቅሰም አለባቸው። ዳዊት ሕይወቱ ትግል (ጦርነት) የበዛበት፣ ሊያጠቁት የሚፈልጉ የቅርብም ሆነ የሩቅ ሰዎች ይነሱበት እንጂ ሕይወቱ በእግዚአብሔር ጥበቃ ውስጥ እንደሆነ ያውቅ ነበር። ይህንንም በጻፋቸው መዝሙሮች መረዳት እንችላለን። *"እኔ በተቸገርኩበት ጊዜ በጠላትነት ተነሡብኝ፤ እግዚአብሔር ግን ጠበቀኝ። እግዚአብሔር ረድቶ ከአደጋ አወጣኝ። በእኔ ደስ ስለተሰኘም፣ ከአደጋ የማመልጥበትን ሰፊ መንገድ ከፈተልኝ"* (መዝ. 18፥18-19) ይላል። መንፈሳዊ መሪ ተዋጊዎቹን እንደ ጠላት ከመቁጠር ይልቅ፣ ለመንፈሳዊ ዕድገቱ እንዲሆን፣ ሕይወቱን እንዲመረምር እግዚአብሔር ያዘጋጀለት ምክንያት አድርጎ ሊጠቀምበት ይገባል።

◆ **3ኛ) ሰው ሁሉ በትክክል ሊረዳው እንደማይችል ማወቅ አለበት**

አንዳንድ ሰዎች መንፈሳዊ መሪውን አንድ ጊዜ "ተዋጊ ነው" የሚል ስም ከሰጡት፣ አመለካከታቸውን ማስለወጥ በጣም ከባድ እንደሆነ ማወቅ አለበት። በየቤታቸው ቢጎበኛቸው፣ በግላቸው የደቀ መዝሙርነት ትምህርት አዘጋጅቶ ቢሰጣቸው፣ በምክር አገልግሎት ቢረዳቸው፣ አንድ ጊዜ ስለ እርሱ መልካም ያልሆነ ነገር በአዕምሯቸው ስለተቀረጸ፣ ልባቸውን ለእርሱ መክፈት ከባድ ይሆንባቸዋል። አንድ ጊዜ በአንድ ነጥብ ላይ ከእነርሱ ሀሳብ ጋር ባለመስማማቱ፣ አለመስማማትን እንደ ኃጢአት አድርገው ስለሚያስቡ፣ በኃጢአት ውስጥ እንደሚኖር አድርገው ይቆጥሩታል። ያለመስማማት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቢፈጠር፣ የግጭቱን ምክንያት አድርገው የሚወስዱት መንፈሳዊ መሪውን ይሆናል። በተለይ ከመሥመር የሚወጣውን፣ በኃጢአት ውስጥ የሚኖረውን የቤተ ክርስቲያን አባል ፊት ለፊት የሚገስጽ ከሆነ እንደ ተዋጊ አድርገው ይቆጥሩታል።

## 1.ለ. እንደ ሰሎሞን የሰላም አገልግሎት ያላቸው መሪዎች

በዚህ ክፍል ውስጥ ያሉ መሪዎች ምዕመናን ሁሉ "አሜን" ብሎ የተቀበላቸው ናቸው። እንደ ዳዊት ሰዎች ሁሉ በትክክል የማይረዱቸው፣ ግጭት የሚበዛባቸው አይደሉም። ሰሎሞን በሕዝቡ ሁሉ ይወደድ እንደነበረው እነዚህም ተወዳጆች ናቸው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥም አንዳንድ መልካም የሆኑ ነገሮች ይታያሉ። መሪው ተቃዋሚ የለበትም። አንዳንድ ልክ ያልሆኑ ሁኔታዎች ቢኖሩም፣ ያደረጋቸው በጎ ነገሮች ጎልተው የሚታይለት ነው። ሁሉ ነገር መልካም ሲሆንለት፣ የቤተ ክርስቲያኒቱ አባሎች ቁጥር፣ ከአሥራትና ከምጽዋት የሚሰበሰበው ገንዘብ እየጨመረ ሲመጣ፣ አገልግሎቱ ከትግል ሁሉ ነጻ ሲሆን፣ "ይህ እንዲህ ሊሆን የቻለው ጥሩ መንፈሳዊ መሪ በመሆኔ ነው" በሚል ሀሳብ ሊፈተን ይችላል። ይሄም በተለይ ገና ወጣት አገልጋይ ከሆነ ራሱን ለአደጋ ያጋልጣል። በሰላም የተሞላ አገልግሎት ሊኖረው የቻለው እንዲሁ በእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ መሆኑን በመዘንጋት፣ "እግዚአብሔር በአገልግሎቱ የባረከኝ መልካም ነገር ስላየ ነው" በማለት በራሱ እንዳይታበይ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ አለበት። ትዕቢት ብዙ ታላላቅ አገልጋዮችን ጥሏል። አንዳንድ መንፈሳዊ መሪዎች አገልግሎታቸው ከችግር ሁሉ ነጻ ሲሆን፣ ለሚያገለግሉት ሰዎች ልባቸው እንደ ድንጋይ የጠጠረ ይሆናል። የአረቦች ምሳሌ፣ "ጸሀይ ሲበዛ፣ በረሃን ይፈጥራል" ይላል። ሁልጊዜ በሰላም የተሞላ አገልግሎት መስጠት ደስ ቢልም፣ ሁሉም ነገር መልካም ሲሆን ቀስ በቀስ መሪዎች የሌሎች ሰዎች መከራና ችግር የማይሰማቸው፣ ደንዳና ልብ እንዲኖራቸው ያደርጋል። ለሚያገለግሏቸው ሰዎች ጊዜ የሌላቸው ይሆናሉ።

## 2. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚፈጠሩት ግጭቶችና ምክንያቶች

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አስቸጋሪ የሆኑትን ሰዎች ማርሻል ሼሊ፣ "ዌል ኢንቴንሺን ድራጎንስ" *(Well Intantioned Dragons)* በሚለው መጽሐፋቸው፣ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አስቸጋሪ የሆኑትን አንዳንድ ሰዎችን "ድራጎን" (Dragan) የሚል የቅጽል ስም አውጥተላቸዋል። ማንኛውም የቤተ ክርስቲያን መሪ (መጋቢ) ይህን መጽሐፍ ገዝቶ ቢያነብ እጅግ በጣም ጠቃሚ ትምህርት ያገኝበታል። ማርሻል ሼሊ እነዚህን "ድራጎንስ" ብለው የጠሯቸውን ሰዎች በአራት ዓይነት ከፍለዋቸዋል።[33]

### ◆ (ሀ) "ዘ በርድ ዶግ (The Bird Dog) ይላቸዋል (በሀገራችን 'አንብጋቢዎች')

እንደነዚህ ዓይነቶቹ "የፓስተሩ ተቆርቋሪዎች ናቸው። የፓስተሩ ጆሮ፣ ዓይን፣ አፍንጫ መሆን የሚፈልጉ ናቸው። እያሸተቱ የሚሄዱበት ምክንያት ተፈላጊነት ለማግ

[33] Shelley, Marshall. Well Intentioned Dragons, Bethany House Publishers, Minneapolis, MN, 1988.



ኘት ነው። ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ልክ ያልሆነ ነገር የሚታያቸው፣ ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ የሚነፍሰውን ወሬ ሁሉ የሚሰሙ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚካሄደውን መጥፎ ነገር የሚያሸቱ ናቸው። ያዩትን የሰሙትን፣ ያሸተቱትን ሄደው ለፓስተሩ ወይም ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሚናገሩ ናቸው። *"...አከሊት ትልቅ ችግር ውስጥ ናትና ሂዱና ጠይቋት... አከሌ በኃጢአት ውስጥ እየኖረ ነውና ማጋለጥ ያስፈልጋል... በእህቶች ሰብ ሰባ ላይ ብዙ ነገር እየተወራ ነውና አንድ ነገር መደረግ አለበት..."* ይላሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ተቆርቋሪ በመምሰል፣ *"...ቤተ ክርስቲያኒቷ የጸሎት ሕይወት የላትም...የአዳር ጸሎት ፕሮግራም መጀመር አለበት...አዳዲስ ነፍሳት ወደ ቤተ ክርስቲያናችን አይመጡም... የምስክርነት ጓድ መቋቋም አለበት"* ይላሉ። አንዳንድ አስተዋይ የሆኑ መጋቢዎች፣ "ጌታ ይህን ለእኔ አልነገረኝም፤ ሀሳቡ ጥሩ ይመስላል። አንተ በዚህ ጉዳይ ላይ ያሰብክበት ስለምትመስል አንድ ነገር ለምን አታደርግም" የሚል መልስ ይሰጣሉ። እውነተኛ የሆኑ "በርድ ዶጎች" በነገሩ የበለጠ ያስቡበታል። እውነተኛነት የሌላቸው ግን እያጉረመረሙ፣ *"ይሄ የአንተ ኃላፊነት እንጂ የእኔ አይደለም። ፓስተሩ አንተ ነህ እንጂ እኔ አይደለሁም። ይህን የነገርኩህ የነገሩን አሳሳቢነት ተገንዝበህ አንድ ነገር እንድታደርግ ነው"* ይሉታል።

በተለይ "ራሳቸውን ተወዳዳሪ የሌላቸው መንፈሳውያን" አድርገው የሚያቀርቡ "በርድ ዶጎች" በየቤተ ክርስቲያኑ አሉ። ሁልጊዜ "ጎደለ" ወይም "የለም" የሚሉትን ነገሮች እየለቀሙ የቤተ ክርስቲያን መሪው (መጋቢው) መንፈሳዊነት የጎደለው ወይም በሕይወቱ ያልጠነከረ መሆኑን ለማሳየት የሚሞክሩ ናቸው። *"ለመንፈሳዊ እንቅስቃሴ እንድንጸልይ ጌታ በልቤ ውስጥ ትልቅ ሸክም ሰጥቶኛልና መጸለይ አለብን! ፓስተር! አይመስልህም?"* ትላለች። "መንፈሳዊ እንቅስቃሴ አያስፈልገንም... አይመስለኝም..." ብሎ የሚከራከር ማን ይኖራል? እንደነዚህ ዓይነቶቹ ከማንኛውም ሰው የበለጠ ለቤተ ክርስቲያኒቷ መንፈሳዊ ሕይወት የሚያስቡ መስለው ይቀርባሉ። ሁኔታቸው የቤተ ክርስቲያኑን መጋቢ የሚያበሳጭ፣ ስለራሱ ጥሩ አስተያየት እንዳይኖረው የሚያደርጉ ናቸው። እውነተኛ ባህሪያቸውን ያልተረዳ ከሆነ፣ የመጋቢነት ኃላፊነቱን እንደሚገባው መወጣት የማይችል፣ የክርስቶስ ልብና አሳብ የሌለው መስሎ እንዲሰማው ይሆናል።

### ◆ (ለ) "ዌት ብላንኬት" (Wet Blanket)

ማርሻል ሼሊ በሁለተኛው ክፍል ውስጥ ያሉትን "ዌት ብላንኬት" (Wet Blanket) ብለው ይጠሯቸዋል። እንደነዚህ ዓይነቶቹ ተለይተው የሚታወቁበት ዋናው ምልክታቸው፣ ሁልጊዜ ሁኔታዎችን አጨልመው የሚመለከቱ ናቸው። ዓይናቸው ሁልጊዜ እንከን ብቻ የሚያይ ነው። ሁልጊዜ ነገርን በቀጥታ ማየት የማይችሉ፣ ሁሉን ነገር አጣመው የሚተረጉሙ፣ ሁሉ ነገር ተጣሞ የሚገባቸው ናቸው። እንደነዚህ ዓይነት አማኞች

የሌሎችን መነቃቃት የሚያከሽፉ፣ ተስፋ የሚያስቆርጡ፣ የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት ወደ ኋላ የሚያስቀሩ (የሚጎትቱ) ናቸው። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አንዳንድ ነገር አቅደው ለምዕመናን ሲያቀርቡ፣ *"...ይሄ የምትሉት ነገር አይሠራም... ከዚህ በፊት እንዲህ ዓይነቱን ነገር ሞክረነው አልሠራም...አሳቡ ጥሩ ቢሆንም ተግባር ላይ የሚያውለው ሰው የለም..."* በማለት ተስፋ የሚያስቆርጡ፣ በሚነደው እሳት ላይ በውሃ የራሰ ብርድልብስ በመጣል እሳቱን ለማጥፋት የሚሞክሩ አስቸጋሪ ክርስቲያኖች ናቸው።

- **(ሐ) "ዘ ኢንተርፕነር" (The Entrepreneur)**

ማርሻል ሼሊ በሦስተኛው ክፍል ውስጥ ያሉትን "ዘ ኢንተርፕነር" (The Entrepreneur) ይላቸዋል። ከላይ የገለጽናቸው ታቃራኒዎች ናቸው። "አይቻልም" ብለው ተስፋ የሚያስቆርጡ ሳይሆኑ፣ "ይቻላል" በማለት ከመጠን በላይ የተነቃቁ ናቸው። የቤተ ክርስቲያን አባሎችን በጣም የሚቀርቡ፣ አዳዲስ ሰዎች ሲመጡ ቀድመው በሳምታ የሚሰጡ፣ ቤታቸው ወስደው የሚጋብዙ ናቸው። ይሄ ሁሉ መጥፎ አይደለም። ግን ዋናው ዓላማቸው ቤተ ክርስቲያን እንድታድግ ፈልገው ሳይሆን፣ ከቤተ ክርስቲያን ውጪ ሌላ ነገር ፈልገው ነው። ፓርላማ ውድድር ውስጥ ካሉ መራጭ ለማግኘት፣ ነጋዴዎች ከሆኑ ንግዳቸውን ለማስተዋወቅ ነው።

- **(መ) "ካፕቴን ብላስተር" (Captain Bluster)**

*ማርሻል ሼሊ በአራተኛው ክፍል ውስጥ ያሉትን ካፕቴን ብላስተር (Captain Bluster)* ብሎ ይጠራቸዋል። እንደነዚህ ዓይነቶቹ ሁልጊዜ ሌላው ስህተተኛ፣ ራሳቸውን ግን ትክክለኛ እንደሆኑ አድርገው የሚያዩና የሚያቀርቡ ናቸው። በማንኛውም ስብሰባ ላይ ከእነርሱ የተለየ ሀሳብ የሚያቀርበውን፣ "አሁን ያቀረብከውን ሀሳብ አልደግፈውም...ልክ አይደለም..." ከማለት ወደ ኋላ የሚሉ አይደሉም። *"...ፓስተሩ የሚከፈለው ደሞዝ ብዙ ነው...ትክክል አይደለም... ቀኑን ሙሉ ምን ይሠራና ነው ይህን ዓይነት ደሞዝ የሚከፈለው..."* በማለት ፊት ለፊት ተቃውሟቸውን ያሰማሉ። እንደነዚህ ዓይነቶቹ በሌላው ሰው ላይ ሲረበረቡ፣ ሌላውን ጨፍልቀው ሲያልፉ ምንም ቅር የማይላቸውና የማይሰማቸው ናቸው። ከነርሱ ጋር መደራደር፣ "ይህን ተው...ይህን ልቀቅ...ይህን ስጥ..." ማለት አይቻልም።

- **(ሠ) "ዘ ፊክል ፋይናንሰየር" (The Fickle Financier)**

*ማርሻል ሼሊ በአምስተኛው ክፍል ውስጥ ያሉትን "ዘ ፊክል ፋይናንሰየር" (The Fickle Financier)* ብሎ ይጠራቸዋል። እንደነዚህ ዓይነቶቹ ገንዘብ ያላቸው በመሆናቸው የቤተ ክርስቲያኒቱን ውሳኔ የማስለወጥ ኃይል ያላቸው ናቸው። ቤተ ክርስቲያኒቱ



ውስጥ የማይፈልጉት ነገር የሚሠራ ከመሰላቸው፣ "ሀሳቡን አልደግፈውም" በማለት በግልጽ አይናገሩም። መቃወማቸውን የሚገልጹት፣ "አስራት መስጠታቸውን በማቋረጥ" ነው። አንዳንዶቹ ፓስተሩን መቅጫ መሣሪያ አድርገው ይጠቀሙበታል። አንዳንዶቹ ደግሞ በሚሰጡት ገንዘብ አማካኝነት ሰዎችን፣ ፕሮግራሞችን በቁጥጥራቸው ለማዋል ይሞክራሉ። ፕሮግራሙ ጥሩ ቢሆንም ባይሆንም እነርሱን ደስ ካላቸው ይሰጣሉ፤ ደስ ካላላቸው ደግሞ ፕሮግራም በጣም ጥሩ ቢሆንም አይሰጡም። የመጋቢው አለቃ ለመሆንም የሚቃጣቸው አሉ። ቤተ ክርስቲያን ደውለው ፓስተሩን ካላገኙት፣ *"ቢሮ መገኘት ባለበት ጊዜ አልተገኘም፤ የእኔ ገንዘብ ለእርሱ ደሞዝ መክፈያ መሆን የለበትም"* በማለት ኃይላቸውን ለማሳየት ይሞክራሉ።

ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል ብትሆንም፣ የአካሉ ብልቶች (ክፍሎች) አማኞች ቢሆኑም፣ በሌሎች ዓለማውያን ድርጅቶች ውስጥ የሚፈጠሩት ችግሮች በቤተ ክርስቲያንም ውስጥ ሲፈጠሩ ይችላሉ። እነዚህ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚፈጠሩ ግጭቶች ምክንያታቸው የተለያየ ነው። ከብዙዎቹ መካከል ጥቂቶቹን ከዚህ ቀጥሎ እንመለከታለን።

## 2.1. ቅናት

በዓለም ውስጥ በግለሰብ መካከል የነበረው የመጀመሪያው ግጭት በሁለቱ ወንድማማቾች፣ በአቤልና በቃየል መካከል የተፈጠረው ነው። የግጭታቸውን ምክንያት ስንመረምር በሁለቱ መካከል የሀሳብ ልዩነት ተፈጥሮ፣ አንደኛው የሌላውን ንብረት በመንጠቁ አልነበረም። እግዚአብሔር በአቤል መስዋዕት በመደሰቱ፣ ቃየን ባቀረበው መስዋዕት ግን ያልተደሰተ በመሆኑ ብቻ ነበር። በዚህ ሁኔታ ቃየን የተናደደና በልቡ ቅሬታ የያዘ መሆኑን የተረዳው እግዚአብሔር ቃየንን፣ *"ስለምን ተናደድህ? ለምንስ ፊትህ ጠቆረ? መልካም ብታደርግ ተቀባይነትን ልታገኝምን? መልካም ባታደርግ ግን ኃጢአት በደጅህ እያደባች ናት፤ ልታሸንፍህ ትፈልጋለች፤ አንተ ግን ተቆጣጠራት" (ዘፍ. 4፥6-7)* በማለት ቀደም ሲል አስፈላጊውን ማስጠንቀቂያ ሰጥቶት ነበር። ይሁን እንጂ፣ ቃየን እግዚአብሔር የሰጠውን ማስጠንቀቂያ ባለመስማቱ ወንድሙን አቤልን *"እስቲ ና ወደ መስኩ እንውጣ አለው፤ በመስኩም ሳሉ ቃየን ወንድሙን አቤልን አጠቃው፤ ገደለውም" (ዘፍ. 4፥8)* ይላል። የግጭታቸው ምክንያት ምን እንደነበረ ያዕቆብ በጻፈው መልዕክት ላይ መረዳት እንችላለን።

- *"ከናንተ ዘንድ ጦርና ጠብ ከወዴት ይመጣሉ? በብልቶቻችሁ ውስጥ ከሚዋጉ ከእነዚህ ከምኞቶቻችሁ አይደሉምን? ትመኛላችሁ ለእናንተ አይሆንም ትገድላላችሁ፤ በብርቱም ትፈልጋላችሁ ልታገኙም አትችሉም፤ ትጣላላችሁ፤ ትዋጋላችሁ፤ ነገር ግን አትለምኑምና ለእናንተ አይሆንም..." (ያዕ. 4፥1-2)።*

ቃየን በወንድሙ በአቤል ላይ የተሰማውን መጥፎ ስሜት (ቅናት) ከውስጡ ማስወጣት ሲገባው፣ ምንም ዓይነት በደል ያላደረሰበትን ወንድሙን ገደለ። ቃየን በግል ሕይወቱ ውስጥ የተፈጠረውን ግጭት ለማስወገድ የተጠቀመበት መንገድ፣ ከመስመር የወጣ ነበር። ይሄ በልቡ ውስጥ የተፈጠረው ቅናት፣ ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስበት እንደሚችል አስቀድሞ እግዚአብሔር የሰጠውን ማስጠንቀቂያ መስማት ስላልፈለገ፣ የራሱን ክፉ እርምጃ ወሰደ። ይሄ የቃየል ችግር ብቻ አይደለም። ዛሬም በቤተ ክርስቲያን አካባቢ በቅናት ምክንያት ወንድሞቻቸውንና እህቶቻቸውን የሚጎዱ ብዙ ቃየንን የሚመስሉ አማኞች አሉ። በአማኖች መካከል የሚፈጠረው ይህን ዓይነቱ ግጭት አንድ ጊዜ ብቻ የሚደርስ ሳይሆን፣ ተደጋግሞ የሚታይ ችግር ነው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሚፈጠሩት ችግሮች መካከል አንደኛውና ዋናው ስቅናት ምክንያት የሚፈጠር ግጭት ከሆነ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ችግሩን ለማርገብ መውሰድ ያለባቸው እርምጃ ምን ይሆን? ብለን መጠየቃችን አይቀርም። አንዳንድ አማኞችን እግዚአብሔር በአገልግሎታቸው ሲባርካቸው ሲያዩ ደስ በመሰኘት ፈንታ ቅር የሚላቸውን አማኞችች ቤተ ክርስቲያን ልትረዳቸው የምትችልባቸው መንገዶች ይኖር ይሆን?

በቅናት ምክንያት በውስጣቸው የተፈጠረውን ችግር በትክክለኛው መንገድ መስመር በማስያዝ ፈንታ እንደ ቃየል በዱላ ደብድበው ባይገሉም፣ ስተለያየ መንገድ ሲያጠቁ ማየት ለብዙዎቻችን አዲስ ነገር አይደለም። ውስጣቸው በቅናት የተሞላ አገልጋዮች፣ የቀኑበትን ሰው ከአገልግሎቱ የሚያስወግዱበት አንደኛው መንገዳቸው፣ እውነትነት የሌለውን መጥፎ ወሬ ማስወራት ነው። ሌላው ችሎታና ብቃት እንዳለው በሕዝብ ሁሉ ዘንድ በግልጽ የታወቀ ቢሆንም፣ በአገልግሎቱ ውስጥ እንዲሳተፍ ዕድል በመንፈግ ነው። ከምዕመናኑ መካከል ሁኔታውን ያስተዋሉ አንዳንድ ሰዎች "እከሌ ለምን አያገለግልም?" ብለው ቢጠይቁ፣ "...ጊዜ የለኝም ስላለ ነው" በማለት እውነት ያልሆነ ምክንያት ይሰጣሉ። ስአጠቃላይ የያዙትን ሥፍራ የሚወስድባቸው ስለሚመስላቸው ከእነርሱ የተሻለ ለመሰላቸው ሰው ልባቸው የተከፈተ አይደለም። እንዲሁም ዋና አስተማሪ ቢጋብዙ ሕዝቡ ያንን ሰው ከወደደው፣ ከሕዝቡ የሚያገኙት እክብሮትና ተቀባይነት የሚቀንስባቸው ስለሚመስላቸው፣ በኮንፍራንሳቸውም ሆነ በሌላ ወቅት ተናጋሪ አድርገው የሚጋብዟቸው፣ ለሕዝቡ መልካም ነገር መስጠት የሚችሉትን አይደለም። እንደነዚህ ዓይነቶቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች "የቃየን መንፈስ" ችግር እንዳለባቸው ግልጽ ነው። "ቅናት" ቤተ ክርስቲያንን፣ እንዲሁም አማኞችን ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊነት የሌላቸውንም ሰዎች የሚጎዳ እንደሆነ የታወቀ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ሥፍራ ተጠቅሷል። እንዲሁም ብዙ ታላላቅ ጸሀፊዎች ቅናት ሊያደርስ የሚችለውን ጉዳት ጠቅሰው ጽፈዋል።

- *"...በእግባቡ እንመላለስ...በክርክርና በቅናትም አይሁን" (ሮሜ 13፥13)።*



- *"ንዴት፣ ጨካኝ፣ ቁጣም ጎርፍ ነው፤ በቅናት ፊት ግን ማን መቆይም ይችላል?" (ምሳ. 27፥4)።*
- *"ጓደኞቸው (ወዳጆቸው) ባገኘው የሕይወት መሳካት ምንም ዓይነት ቅናት ሳይሰማቸው ደስ የሚላቸው ጥቂት ብርቱ ሰዎች አሉ"–አስኪለስ*
- *"ቅናት ሌላው ላይ ተኩሶ የሚያቆስለው የተኮሰበትን ሰው ሳይሆን ራሱን ነው"–ቻርለስ ኮልተን*
- *"ከእርሱ በታች የሆኑትን በመርዳት በሥራ የተጠመደ ሰው፣ ከእርሱ በላይ በሆኑት ሰዎች ላይ ለመቅናት ጊዜ አይኖረውም"–ሄኔሪታ ሚርስ*

"ቅናት" የአማኞችን አንድነት የሚገድል መርዝ ይሁን እንጂ፣ ለቅናት ልባቸውን ላለመክፈት የሚያስችላቸውን ኃይል ከጌታ ተቀብለዋል። ከጌታ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ሲያስተካክሉ፣ በውስጣቸው ያሉትን አንድንድ ጤናማ ያልሆኑ ስሜቶችን ከሕይወታቸው ያስወግዳሉ። ኢየሱስ ***"ከሰው ልብ የሚወጣ ክፉ አሳብ፣ ዝሙት መስረቅ፣ መግደል፣ ምንዝርነት፣ መጎምጀት፣ ክፋት፣ ተንኰል፣ መዳራት፣ ምቀኝነት ስድብ፣ ትዕቢት፣ ስንፍና ናቸውና፤ ይህ ክፉው ሁሉ ከውስጡ ይወጣል፤ ሰውንም ያረክሰዋል"*** አለ *(ማር. 7፥21-23)።*

## 2.2. የቡድን መንፈስ

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሚፈጠሩት "ግጭቶች" ሌላው ምክንያት ስቤተ ክርስቲያን ውስጥ፣ በሚፈጠሩት የተለያዩ ቡድኖች ምክንያት ነው። ይሄ ችግር በሐዋርያት ዘመንም ነበር። ጎልቶ የሚታየው ግን በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበረው ነው። በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የቡድን መንፈሱን ማን እንደፈጠረውና በምን ምክንያት እንደተፈጠረ ባይታወቅም፣ ይሄ የቡድን መንፈስ ቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ትልቅ ችግር እንደፈጠረ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ አማኞች በጻፈው መልዕክት መረዳት እንችላለን። ***"ወንድሞች ሆይ! በመካከላችሁ ክርክር እንዳለ ከቀሎኤ ቤተሰብ ሰምቻለሁ፤ ነገሩም እንዲህ ነው ከእናንተ አንዱ እኔ የጳውሎስ ነኝ ሲል፣ ሌላው እኔ የአጵሎስ ነኝ ይላል፤ ደግሞም አንዱ እኔ የኬፋ ነኝ ሲል፣ ሌላው ደግሞ እኔስ የክርስቶስ ነኝ ይላል። ለመሆኑ ክርስቶስ ተከፋፍሎአልን ጳውሎስስ ለእናንተ ተሰቅሎአልን? ወይስ በጳውሎስ ስም ተጠምቃችኋልን?"*** ይላቸዋል (1 ቆሮ. 1፥11-13)። በተለይ በአሁኑ ዘመን በእግዚአብሔር ሕዝቦች መካከል ከላይ በገለጽነው ምክንያት የእርስ በርስ መከፋፍል ጎልቶ የሚታይበት ዘመን ነው። ለሁለት፣ እንዳንዴም ለሦስት መከፋፈል ያልደረሰበት ቤተ ክርስቲያን ታውቃላችሁ? በአሁኑ ጊዜ በየአካባቢው የሚገኙት ቤተ ክርስቲያናት "በማባዛት የተገኙ ሳይሆኑ በማካፈል" የተፈጠሩ ናቸው። አንዳንዶቻችን ግራ ገብቶን "ቤተ ክርስቲያን ማደግ ያለ

ባት በዚህ ዓይነት ነው ወይ?" ብለን መጠየቃችን አይቀርም። ብዙ ጊዜ የግጭቱ ምክንያት ምዕመናኑ ሳይሆን፣ ከላይ እንደገለጽነው በቡድን የተከፋፈሉ፣ ራሳቸውን "መሪ" ብለው በሚጠሩ ወይም ሥልጣን በሚፈልጉ ጥቂት ሰዎች ምክንያት እንደሆነ ግልጽ ነው።

በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የነበረው የቡድን መንፈስ "የጳውሎስ... የአጵሎስ... የኬፋ...የክርስቶስ" ቡድን በማለት ለአራት የተከፈለ ነበር። የዛሬዎቹ ቡድኖች የሚከፋፈሉበት የራሳቸው መልክ አላቸው። በውጪ አገር ያሉ የኢትዮጵያውያን ቤተ ክርስቲያናት አንዳንዶቹ ግለሰብ መሪ ያላቸው ሲሆን፣ ሌሎቹ ደግሞ ቀደም ሲል የመጡበትን አገር ወይም ቤተ ክርስቲያን በመለየት ነው። *"ከሱዳን የመጡ...ከጂቡቲ የመጡ... ከአቴንስ የመጡ...ከሳውዝ አፍሪካ የመጡ...ከናይሮቢ የመጡ...ከግብጽ የመጡ ወዘተ."* በማለት ሲሆን፣ ከኢትዮጵያ የመጡት ደግሞ *"ከሙሉ ወንጌል...ከመሠረተ ክርስቶስ... ከመካነ ኢየሱስ...ከጉባኤ እግዚአብሔር ወዘተ."* በማለት የተከፋፈሉ ናቸው። በዘርም የተከፋፈሉበት ቤተ ክርስቲያናትም መኖራቸውን እንሰማለን። በዚህ ዓይነት ልዩነት ፈጥረው የክርስቶስ አካል የሆነችውን "ቤተ ክርስቲያን እንመራለን" ማለታቸው በጣም ያሳዝናል። መጀመሪያ ምዕራፍ ላይ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ሀልውናዋ "አንድነቷ" መሆኑን ገልጸናል። አካላችን ተቆራርጦ ቢወድቅ፣ የተቆራረጡት ብልቶች ሕይወት አን ደሌላቸው ግልጽ ነው። ልክ እንደዚሁ የተለያዩ ምዕመናን ከአካሉ ጋር ያልተያያዙ ከሆኑ ሕይወት ኖሯቸው ማደግ እንዴት ይችላሉ? ኢየሱስን በአሁኑ ጊዜ የሚያስጨንቀው ነገር ቢኖር አንድነት ማጣታችን ነው።

***"...አባት ሆይ! አንተ በእኔ፣ እኔም በአንተ እንዳለሁ ሁሉም አንድ እንዲሆኑ፣ እንዲሁም አንተ እኔን እንደ ላከኸኝ ዓለም ያምን ዘንድ፣ እነርሱም በእኛ እንዲሆኑ ነው። እኛ አንድ እንደ ሆንን እነርሱም አንድ እንዲሆኑ፣ የሰጠኸኝን ክብር ሰጥቻቸዋለሁ። ይህም እኔ በእነርሱ፣ አንተም በእኔ መሆንህ ነው። አንተ እንደ ላከኸኝና እኔን በወደድኸኝ መጠን እነርሱንም እንደ ወደድኻቸው ዓለም ያውቅ ዘንድ አንድነታቸው ፍጹም ይሁን" (ዮሐ. 17፥21-23) በማለት ዛሬም ይጸልይልናል።***

ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ግጭት (አለመስማማት) ሲኖር፣ ከሁሉም የበለጠ ግጭቱ የሚሰማቸው የቤተ ክርስቲያን መጋቢዎች (መሪዎች) ናቸው። ምክንያቱም የቤተ ክርስቲያኑን ሕብረት ወይም አንድነት የመጠበቅ ኃላፊነት እንዳለባቸው ስለሚታሰብ ነው። ጥሩ መጋቢ መሆናቸው የሚመዘነው፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉት አማኞች እርስ በርሳቸው ተቀባብለው በሰላም መኖር ሲችሉ ነው። ሌላው ምክንያት መጋቢዎች ከሁሉም ሰው ጋር ተስማምተው መኖር የሚጠበቅባቸው በመሆኑ ነው። ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰላም ከሌለ መጋቢዎች በአገልግሎታቸው "ውጤት የለሽ" የሆኑ ይመስላቸዋል። ይሁን እንጂ፣ ከግጭት ነጻ የሆነው፣ ደስ ብሏቸው የሚያገለግሉ መጋቢዎች (ፓስተሮች)



ቢኖሩ፣ በጣም ጥቂቶች መሆን አለባቸው። እግዚአብሔር ጠርቶት በሥፍራው ያላስቀመጠው ከሆነ፣ በአሁኑ ጊዜ ሥፍራውን የሚመኝ ሰው ካለ፣ የሚያስከፍለውን ዋጋ በትክክል ያልተመነ መሆን አለበት። ቤተ ክርስቲያን የምትሰፍርበትን ቀለብ ፈልጎ ከሆነ፣ ሌላ ሥራ ሠርቶ መኖሩ የበለጠ ይመረጣል። በየቦታው የሚፈጠሩትን ችግሮች ስንሰማ፣ "በአሁኑ ዘመን ሥፍራቸውን እንደያዙ ለረጅም ጊዜ መቀጠል የሚችሉ መጋቢዎች ለመሆን እንዴት ዓይነቶቹ ይሆኑ?" ብለን መጠየቃችን አይቀርም። እንደሚባለው ከሆነ፣ "የራሳቸውን ቡድን" ያደራጁት ናቸው። አንድ መጋቢ በሥልጣን ላይ ለረጅም ጊዜ መቀመጥ የሚችለው፣ በራሱ ደጋፊዎች ዙሪያውን የተከበበ እንደሆነ ብቻ ነው። እነዚህ በዙሪያው የሚያሰልፋቸው ሰዎች ለእርሱ ያላቸውን ታማኝነት በተለያየ ጊዜና ሁኔታ ያስመሰከሩ፣ "ተቃዋሚዎቹ ናቸው" የሚላቸውን ሰዎች ሽንጣቸውን ገትረው የሚዋጉለት (የሚቋቋሙለት) ናቸው። በዚህ ዓይነት የተከበበ መሪ ከሆነ፣ አገልግሎቱ ጥራት ባይኖረውም፣ ማስተማር ባይችልም፣ ቅድስና የሌለው ነገር የፈጸመ ቢሆንም፣ የቤተ ክርስቲያኒቱን ገንዘብ ያለአግባብ የተጠቀመም ቢሆን፣ ማንም ሳይነካው ለረጅም ጊዜ መቆየት ይችላል። በአሁኑ ጊዜ መንፈሳዊ መሪ (መጋቢ) ለመሆን ይህን ያህል የማስተማር ችሎታ ወይም ብቃት የሚጠይቅ አይደለም። በየሳምንቱ ሕዝቡን ምን አስተምራለሁ? ብሎ አይጨነቅም። ማስተማር ሰሚፈልገው ሁሉ እንደ ዕቁብ ያከፋፍላል። እርሱም የሚደርሰበትን ድርሻ በዓመት ሁለት ወይም ሦስት ጊዜ የደንቧን ያደርጋል። የእርሱ ሥራ ፕሮግራም ማውጣትና ማከፋፈል ብቻ ስለሆነ፣ ይህን ያህል ከባድና የሚያስጨንቅ ሥራ አይሆንበትም።

ከላይ በገለጽነው ዓይነት፣ በዙሪያው የራሱ የሆኑትን ሰዎች ያላሰለፈ መንፈሳዊ መሪ (መጋቢ) ምንም ያህል እውነተኛ ጥሪ ያለው፣ ማስተማር የሚችል፣ በቅድስና የሚያምንና ሕይወቱን በቅድስና የሚመራ ቢሆን፣ ለሚያገለግለው ሕዝብ እውነተኛ መስጠት ያለው ቢሆን፣ አገልግሎቱን ለግል ጥቅም የማያውል ሀቀኛና እውነተኛ አገልጋይ ቢሆንም፣ በአገልግሎቱ ብዙ ዕድሜ አይኖረውም። ያ እርሱ የያዘውን ሥፍራ የሚፈልጉ ሰዎች፣ መሮት ሰቆ እስኪወጣ ድረስ በግራና በቀኝ መከራውን ያበሉታል። የሚያሳዝነው ግን በአገልግሎቱ የሚደሰቱ ብዙዎች ቢሆኑም፣ ለራሳቸው በሰላም መኖር የሚፈልጉ በመሆናቸው፣ "...አትንኩት.... ምን አደረጋችሁ?" ብለው የሚዋጉ፣ ለእውነት የሚቆሙ አለመሆናቸው ነው። ጥቂት የሚንጫጩ ተቃዋሚዎቹ ግራ ሲያጋቡት እያዩ "...ስለ አንድ ሰው ሰንል ከብዙዎቹ ጋር አንጣላም፤ ደም እንቃባም..." በማለት አፋቸውን ዘግተው ያቀመጣሉ። ብቻውን መሆኑን የሚያየው የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪ (መጋቢ) ጥቂት ሰዎች ባነሱት ችግር ምክንያት ታግሶ መቆም ያቅተውና "ሕዝቡ አገልግሎቴን የማይፈልግ ከሆነ፣ በግድ ላገልግላችሁ ማለቴ ትክክል ነው ወይ?" ብሎ ራሱን ከጠየቀ በኋላ፣ ሥፍራውን ለቆ ይወጣል። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ለቅቆ ሲወጣ ሁኔታውን በማስታረቅ ፈንታ፣ "...ጌታ ነቀለልን..." በማለት እንደ በረከት ይቆጥሩታል። ባዶ የሆነበትን ሥፍራ ለመያዝ ከዚህ በኋላ ሥፍራውን ፈላጊዎች ብዙ ከሆኑ፣ እርስ በርሳቸው መጋደል

ይጀምራሉ። ሥፍራውን ፈላጊ አንድ ብቻ ከሆነ፣ ያ ሰው በዙሪያው ደጋፊዎቹን አሰልፎ ብቅ ይልና ቦታውን እንደምንም ብሎ ይይዛል።

ያ ቀደም ሲል ተገፍቶ የወጣው አገልጋይ ደግሞ እርፎ አይቀመጥም። እዚያው ከተማ ጥቂትም ቢሆኑ እነርሱን ይዞ ቤተ ክርስቲያን ይከፍታል። እርሱም ሌላ አገልጋይ ይጠራና መሪነቱን ያጸናል። በአንድ ከተማ፣ በአንድ መንደር ውስጥ ሁለት ትናንሽ ቤተ ክርስቲያኖች ይፈጠራሉ። ሁለቱም፣ አንዱ ከሌላው ለመብለጥ ከፍተኛ ትግል ያደርጋሉ። ከአንደኛው ቤተ ክርስቲያን ያኮረፈ ሰው ቢኖር፣ ወደ ሌላው ቤተ ክርስቲያን ይሄዳል። በተቻላቸው መጠን ሁለቱም አብረዋቸው ያሉትን ምዕመናን ለማበደሰት ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ። ከምዕመናኑ መካከል አንዱ በኃጢአት ውስጥ ቢኖር፣ "አኩርፎ ይሄድብናል" ብለው ስለሚፈሩ፣ ለመገሰጽና ለመምከር አቅም ያንሳቸዋል። በዚህ ዓይነት የሚያስተላልፉት መልዕክት "በጸጋው እንዴ ድናችኋል...በቅድስና ብትኖሩ፣ ባትኖሩም ምንም አይደለም" የሚል ይመስላል። ሁለቱም ምዕመናኖቻቸውን የሚይዙበት ማኅበራዊ ኑሮን መሠረት ያደረገ ነው።

*ማኅበራዊ ኑርና መረዳዳት "ስህተት ነው" ማለታችን አይደለም። በእውነተኛ ልብ እስከተደረጉ ድረስ፣ ከበስተኋላው ያለው ዓላማ ትክክለኛ እስከሆነ ድረስ ክፋትነት የለውም። እግዚአብሔር ሰው ስላልሆነ፣ የውጪውን ብቻ ሳይሆን የውስጡንም ስለሚያይ ያንን ዓይነት በጎ ነገር ለምን እንዳደረግነው ያውቃል። ይህን ዓይነቱን በጎ አድራጎት ለሌሎቹ ያደርጋሉ ወይ? ችግር የደረሰባቸው ሰዎች እነርሱን የማይደግፉ ከሆነ ከላይ የገለጽናቸውን በጎ ነገሮች ያደርጉላቸዋል ወይ? አይመስለንም!*

*ለእነርሱም ሆነ መሪዎቹን ለሚደግፉ ሰዎች የሚደረገውን በቅርብ የሚያዩ፣ ይህን ከመሰለ ማኅበራዊ ኑሮ መውጣት አይፈልጉም። አንዷ ቤተ ክርስቲያን የምትሄድበትን ምክንያት ስትገልጽ፣ "ቤተ ክርስቲያን የምሄደው በየሳምንቱ የምሰማው መልዕክት ጠቅሞኝ፣ ወይም መንፈሳዊ ሕይወቴን ያሳድግልኛል ብዬ... አንዱ አዝማች ብቻ መቶ ጊዜ ሲዘመር መስማቱ አስደስቶኝ ሳይሆን፣ ዕድር ስለሌለኝ ዘመድ ቢሞትብኝ ለቅሶ የሚደርስ ሰው እንዳላጣ፣ እንዲሁም ብታመም ጠያቂ እንዳላጣ ብዬ ነው" አለች። ቤተ ክርስቲያን ለመሄድ ይሄ ቀሲቃሽ ምክንያት ይሆናል? መንፈሳዊ መሪዎችም እነዚህን ከላይ የጠቀስናቸውን ነገሮች ጥሩ አድርገው ስለሚሠሩት፣ "ክብቃት ማነስ ሥራችንን እናጣ ይሆን?" የሚል ፍርሃት አይኖርባቸውም።*

ዛሬ የቤተ ክርስቲያን ዕድገት የሚለካው የምዕመናኑ ቁጥር በመብዛት ስለሆነ፣ ቁጥራቸውን የሚያሳድጉት በምን ዓይነት ሁኔታ ይሆን? ቁጥራቸውን የሚያበዙበት፣ ሁሉቱም የሚከተሉት መንገድ አንድ ዓይነት ነው።

*ለአዳዲስ ነፍሳት ወንጌልን ሰብከው የአማኞችን ቁጥር በመጨመር ሳይሆን፣ አማኝ የሆኑትን ከሌላ ሥፍራ በማስመጣት ነው። በአሜሪካና በካናዳ የአማኞች ቁጥር ሲጨምር*



*የምናየው ከአንዱ ስቴት ወደ ሌላው ስቴት ክርስቲያኖችን በማስመጣት ነው። ሌላው ደግሞ "ዲቪ ሎተሪ" ለሚደርሳቸው ሰዎች ስፖንሰር በመሆን ነው። ለዚህም በተለያየ መንገድ ማስታወቂያ እንደሚያወጡ ሰምተናል። ስፖንሰር ማግኘት ለሚቸገሩ ክርስቲያኖች ጥሩ ቢሆንም፣ የቤተ ክርስቲያናቸውን ምዕመናን በዚህ ዓይነት ለሚያሳድጉ መንፈሳዊ መሪዎች ግን ኃላፊነታቸውን በትክክለኛው መወጣታቸው አይመስለንም።*

ሰደተኛን መርዳት በጣም ጥሩ ነው፣ የወንጌልን አገልግሎትን ግን መተካት የለበትም። ይሄ ችግር የሚታየው በውጪ አገር ባሉ በኢትዮጵያውያን አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ነው።

## 2.3. ኃጢአት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሲሰለጥን

"ኃጢአት" ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት ብቻ ሳይሆን እርስ በርሳችን ሊኖረን የሚገባውን የተቀራረበ ግንኙነት የማበላሸት ኃይል አለው። ክርስቲያን በኃጢአት የመውደቅ ዝንባሌ ይኑረው እንጂ፣ በኃጢአት ውስጥ አይኖርም። ኃጢአት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሲሰለጥን፣ ሁሉም "የእኔ አሳብ ከአንተ ይሰያል" በማለት ፈንታ፣ "የእኔ ሃሳብ ከአንተ ይበልጣል" እንድንል ያደርገናል። "ያንተ ፍላጎት ይቅርና የእኔ ፍላጎት ብቻ ይሟላ" የሚል ዝንባሌ ይታያል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰላም ሲጠፋ፣ ማስታረቅ የማይቻል ግጭት በምዕመናኑ መካከል ሲፈጠር፣ ለግጭቱ ጎልቶ የሚታይ ሌላ ምክንያት ሲጠፋ፣ በአንድ ወይም በተወሰኑ ሰዎች ሕይወት ውስጥ ኃጢአት ሥር እየሰደደ መሆኑን እንጠራጠር። ግጭቱ በምን ምክንያት እንደተፈጠረ በንስሓ ምክንያቱ "ሰበ" ወይም ደካማ ሆኖ እናገኘዋለን። "እርስ በርስ ለመሰያየት እንዴት ይሄ ምክንያት ሊሆን ይችላል?" ብለን መጠየቃችን አይቀርም።

በጥሩ መንፈሳዊ አቋም ላይ የምትገኝ አንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ነበረች። ምዕመናኑ እርስ በርስ ያለው የተቀራረበ ግንኙነት፣ መሪዎቹና ምዕመናን የነበራቸው አንድነት ፍጹም ሌላ ነበር። የቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢ የማስተማር ችሎታው ይህን ያህል የሚደነቅ ባይሆንም፣ ምዕመናኑ የሚያድግበትን መንገድ በመፈለግ የተቻለውን ሁሉ ያደርግ ነበር። ጤናማ የሆኑ መጽሐፎችን እየመረጠ ሕዝቡ እንዲያነብ ያደፋፍር ነበር። የተለያዩ ትምህርቶችን በጽሁፍ እያዘጋጀ ሁሉም በየቤቱ እንዲያጠና ከፍተኛ ጥረት ያደርግ ነበር። መዝሙር መዘመር ብቻ ሳይሆን፣ ምዕመኑ ትክክለኛ የሆነ አምልኮት እንዲኖረው ያስተምር ነበር። የቤተ ክርስቲያኒቷ የጸሎት ሕይወት የሚደነቅ ነበር። አዳዲስ ነፍሳትም ወደ ቤተ ክርስቲያን በመምጣታቸው፣ የቤተ ክርስቲያኒቱ አገልግሎቱ እየበዛ በመምጣቱ መጋቢውን የሚረዳ ረዳት መጋቢ እንደሚያስፈልግ መጋቢውና ሽማግሌዎች መወያየት ጀመሩ። ብዙ ከተወያዩና ከጸለዩበት በኋላ፣ ይህን ሥራ ለመሥራት ብቃት አለው ብለው ያመኑበትን አንድ ወንድም ይዘው ቀረቡ። ምዕመናኑ መሪዎቹ ያቀ

ረቡትን በደንብ ካዳመጡና ከተወያዩ በኋላ ሁሉም በአንድ ድምጽ ተስማሙበት። ከአንድ ሳምንት በኋላ ከአንዳንድ አቅጣጫ ቅሬታ ያላቸው ሰዎች ብቅ ማለት ጀመሩ። የሰጡት ምክንያት "ቤተ ክርስቲያኒቷ በአሁኑ ጊዜ የገንዘብ አቅሟ ሁለተኛ መጋቢ ለመቅጠር አይፈቅድላትም" የሚል ነው። ቤተ ክርስቲያኒቱ የገንዘብ ችግር እንደሌለባት መሪዎቹ ቀደም ሲል ባቀረቡት የሂሳብ ሪፖርት በሚገባ የገለጹት ቢሆንም፣ "...ዋናው መጋቢ ምን ሊሠራ ነው ምክትል የምንቀጥርለት..." በማለት ማጉረምረማቸውን ቀጠሉ። ቀደም ሲል በተወሰነው መሠረት ረዳት መጋቢው አገልግሎቱን ጀመረ። እነዚያ ተቃውሟቸውን ያሰሙት አማኞች ከቤተ ክርስቲያን ቀሩ። ጥቂት ቆይተው "እኛ የራሳችንን ጀምረናልና ቤተ ክርስቲያናችንን እወቁልን" አሉ።

ችግሩን ወይም የተፈጠረውን የሃሳብ ልዩነት ለመፍታት በጥበብና በማስተዋል የተሞላ ምንም ዓይነት አስታራቂ ሰው ቢመጣ፣ ችግሩን ሊፈታውና እርቅ ሊያመጣ አይችልም። የተፈጠረው ችግር መፍትሄ የሌለው በመሆኑ ሳይሆን፣ ከእግዚአብሔር ሕዝብ አንድነት የበለጠ የራሱን ፍላጎት የሚያስቀድም ሰው ስላለ ነው። "ረዳት መጋቢ አያስፈልገንም" ያለው ሰው ምክንያት፣ ቤተ ክርስቲያኒቱ በእርግጥ አቅም የላትም ብሎ ሳይሆን፣ ያንን ሥፍራ እርሱ ራሱ ይመኘውና ይፈልገው ስለ ነበረ፣ ከእርሱ አልፎ ለሌላ ሰው በመሰጠቱ ብቻ ነው። ይህንን መንፈሱን ግንም ሰው እንዳያውቅበት "እኔ ቦታውን ፈልጌ እንዳይመስላችሁ...እግዚአብሔር ይመስገን እኔ ጥሩ ሥራ አለኝ..." ይላል። ይሁን እንጂ፣ ችግሩ በሌላ ምክንያት የመጣ ሳይሆን፣ የእርሱ ፍላጎት ማየል ብቻ ነው። መፍትሄ የሚያገኘው፣ "ልቤ በራስ ወዳድነት ኃጢአት የተሞላ ነው" ብሎ በጌታ ፊት ንስሀ ካልገባና የያዘውን ካልለቀቀ፣ ቤተ ክርስቲያኒቷ ለሁለት መከፈሏ ምንጊዜም አይቀርም። ዛሬ በኢትዮጵያውያን መካከል የሚታየው መከፋፈልና መበጣጠቅ አንደኛውና ትልቁ ምክንያት ሌላ ነገር ሳይሆን ይሄ እንደሆነ ለመረዳት "የአንጎል ቀዶ ጥገና ሀኪም" መሆንን አይጠይቅም።

## 3. ከግጭት ውስጥ በጎ (መልካም) ነገር ሊወጣ ይችላል

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዛሬ ብቻ ሳይሆን፣ ጥንትም ግጭቶች እንደነበሩ ገልጸናል። ግጭት ወይም አለመስማማት፣ በአግባቡ ከተጠቀምንበት ጎጂ ብቻ ሳይሆን ጠቃሚነትም እንዳለው የታወቀ ነው። አለመስማማት ኃጢአት አይደለም። የእግዚአብሔር ወዳጅ የተባለው አብርሃምም ከሎጥ ጋር ያልተስማማበት ጊዜ ነበር። አብርሃምን የተለየ ያደረገው ግን፣ አለመስማማታቸውን ትክክለኛ በሆነ መንገድ መስመር እንዲይዝ ያደረገ መሆኑ ነው። አብርሃም ሎጥን፣ *"...እኛ ወንድማማቾች ነንና በእኔና በአንተ፣ በእረኞቼና በእረኞችህ መካከል ጠብ እንዳይሆን እለምንሃለሁ..."* (ዘፍ. 23፥8) በማለት



ሰላምን ፈጠረ። በአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያንም በአማኞች መካከል አልፎ አልፎ ግጭት ነበር። ጳውሎስና በርናባስ ያልተስማሙበት ጊዜ ነበር (የሐዋ. 15፥36-41)። ጳውሎስ ለገላትያ ቤተ ክርስቲያን በጻፈው መልዕክቱ *"...ጴጥሮስ ወደ አንጾኪያ በመጣ ጊዜ በግልጥ ተነቅቶ ስለ ነበር ፊት ለፊት ተቃወምሁት"* (ገላት. 2፥11) የሚለውን ስናነብ፣ በጳውሎስና በጴጥሮስ መካከልም ግጭት ተፈጥሮ እንደነበረ መገንዘብ እንችላለን። በግለሰብ መካከል ብቻ ሳይሆን፣ በማህበር ውስጥም አለመስማማት እንደነበረ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እናነባለን። በሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ፣ የግሪክ ቋንቋ የሚናገሩ አይሁዳውያን "መበለቶቻችን ተረሱብን" (የሐዋ. 6፥1) የሚል ቅሬታ ስላሰሙ፣ አለመግባባት ተፈጥሮ እንደነበረ ቀደም ሲል ገልጸናል። በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ግጭታቸውን መስመር ማስያዝ አቅቷቸው፣ ፍርድ ቤት ድረስ እስከመካሰስ የደረሱ አማኞች እንደነበሩ እናውቃለን። *"ከእናንተ አንዱ ክርስቲያን ከሆነው ወንድሙ ጋር ቢጣላ፣ ጉዳዩን የእግዚአብሔር ሰዎች በፍርድ እንዲያዩለት በማድረግ ፈንታ ለክስ ወደ አረማውያን የፍርድ ሸንጎ ለመሄድ እንዴት ይደፍራል? የእግዚአብሔር ሰዎች በዓለም ላይ እንደሚፈርዱ አታውቁምን? ታዲያ በዓለም ላይ የምትፈርዱ ሲሆን በዚህ በትንሽ ነገር ላይ መፍረድ እንዴት አቃታችሁ?"* (1 ቆሮ. 6፥1-2) በማለት ሐዋርያው ጳውሎስ እንደወቀሳቸው እናውቃለን። የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን በተለያየ ምክንያት ግጭት (አለመስማማት) አጋጥሟቸው ግጭታቸውን በአግባቡ መስመር ያስይዙ እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጠቅሷል።

- ለጣኦት ከታረደው ሥጋ በመብላት ምክንያት የተነሳው ጭቅጭቅ መፍትሄ ተገኘለት (ሮሜ 14)
- ግዝረትን በሚመለከት ነጥብ ላይ ከፍተኛ አለመግባባት እንደነበራቸው እናስታውሳለን (የሐዋ. 15፥1)። ይሁን እንጂ፣ ለእምነታቸው ቋሚ የሆነ መመሪያ ለማውጣት ምክንያት ሆናቸው።
- በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን በቡድን የተከፋፈሉበት ጊዜ እንደነበረ እናውቃለን (1 ቆሮ. 1፥10-12)። መሪዎች አገልጋዮች እንጂ፣ ልዩ ኃይል እንደሌላቸው ማወቅ ቻሉ።
- በሀሰተኞች አስተማሪዎች ምክንያት አንዳንድ አለመግባባት ተፈጥሮ እንደነበረ እናውቃለን (3 ዮሐንስ)። በዚህ ውስጥ ግን ከሀሰተኞች አስተማሪዎች ንዴት መጠንቀቅ እንዳለባቸው መረዳት ቻሉ።

አለመስማማት (ግጭት) ሁልጊዜ መጥፎ አይደለም። ጥሩ ውጤት ሊያስገኝ ይችላል። ሐዋርያት ያጋጠማቸውን አለመስማማት ለመፍታት ተወያይተው መፍትሄ ይሆናል ብለው ያሰቡትን እርምጃ በመውሰዳቸው እንደተጠቀሙ መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክ

ራል። ስለዚህ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የምናያቸው አንዳንድ ግጭቶች ቤተ ክርስቲያኒቷ ጤናማ አለመሆኗን የሚያሳይ አይደለም። እንዲያውም ወደ ዕድገት እየመጣች መሆኗን ያሳያል። ይህንን ስል ትልቅ መራራነት፣ ጥላቻና ጥርስ እስከ መነከስ ድረስ የሚያደርሰውን ዓይነት ግጭት ማለታችን አይደለም። ሰዎች በአንድ ሀሳብ ላይ ባይስማሙ፣ አለመስማማታቸውን በአግባቡ ቢይዙት እንኳን፣ ያን ዓይነቱ አለመስማማትም "ግጭት" ነው።[34] በግጭት ምክንያት አንዳንድ በጎ የሆኑ ነገሮች ሊፈጠሩ ይችላሉ፥

## 3.1. የሚያወያይ አሳብ (ጥያቄ) በአግባቡ እንዲታይ ዕድል ይሰጣል

በአንድ ወቅት፣ በአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከአንዳንድ አማኞች ቅሬታ ይሰማ ነበር። ቅሬታውም "የአምልኮቱ ፕሮግራም ረዘመ... ሁለት ሰዓት ሙሉ መቆም ያደክማል... ለቃሉ የሚሰጠው ጊዜ ሃያ ደቂቃ ብቻ ስለሆነ፣ ሕዝቡ መንፈሳዊ ምግብ አያገኝም..." የሚል ነው። በዚህ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ያሉት ምዕመናን አብዛኛዎቹ ቤተ ክርስቲያን የሚመጡት 2 ሰዓት ዘግይተው ነው። በየሳምንቷ "አባካችሁን ሰዓት አክብሩ" እያሉ ማስታወቂያ ቢናገሩም መሪዎቹ ሰሚ አላገኙም። ዘግይተው የሚመጡበት ምክንያት "ሁለት ሰዓት መቆም አልችልም... አንድ አዝማች 50 ጊዜ መዘመር ሰለቸን... አምልኮቱ ሲያልቅ መድረስ ይሻለናል" በማለት ነበር። የአንዳንድ አማኞች ቅሬታ የቤተ ክርስቲያኒቱን መሪዎች ቅር ስላሰኛቸው ለውይይትም ሆነ ለመውቀስ እነዚያን ቅሬታ ያሰሙትን ሰዎች ሰበሰቧቸው። ችግራቸው ምን እንደሆነ ሲጠየቁ፣ ከላይ የገለጽነውን ሁኔታ ነገሯቸው። ቤተ ክርስቲያናቸው እንደ እግዚአብሔር ፈቃድና አሳብ እንድትመራ የሚፈልጉ አስተዋይ የሆኑ መሪዎች በመሆናቸው፣ "ስአመራራችን ላይ ለምን ቅሬታ ታሰማላችሁ" በማለት እነዚያን ሰዎች ለመውቀስ ፈንታ፣ ችግሩ የሚቃለልበትን ሁኔታ አሳብ እንዲሰጡ ዕድል ሰጧቸው። በዚህ ሁኔታ ላይ ሰፊ ውይይት ካደረጉ በኋላ፣ የአምልኮቱ ሰዓት እንዳይረዝም፣ አምላኪው እንዳይሰለቸው አንድ አዝማች ወይም አዝማቾች ከተወሰነ ጊዜ በላይ እየተደጋገመ እንዳይዘመር ውሳኔ ሰጡ። ከዚያን ጊዜ በኋላ ሕዝቡ በሰዓቱ መጥቶ አምልኮና ቃሉን ሰምቶ ይመለስ ጀመር። ቤተ ክርስቲያኒቷ አዳዲስ ሰዎችን መሳብ፣ ያሉትንም ማቆየት ቻለች። በቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ አንዳንድ ለውጥ ማድረግ አስፈላጊነቱ ቢታያቸውም "ተቃዋሚ... ነቃፊ... የተቀባውን የማያከብር..." እባላለሁ በማለት ቅሬታቸውን በውስጣቸው ይዘው ቤተ ክርስቲያን የሚመላለሱ በአሁኑ ጊዜ ጥቂቶች አይደሉም። ከላይ እንዳየነው መሪዎች ግጭትን ለማርገብ ጥረት የማያደርጉ ቢሆን ኖሮ፣ ቤተ ክርስቲያኒቷ በማደግ ፈንታ ቅር የተሰኙት አማኞች ቤተ ክርስቲያናቸው እየለቀቁ ይወጡ ነበር።

[34] Leas, B. Speed. Mastering Conflict & Controversy. Multnomah, Portland, Oregon, 1973.



## 3.2. ጥሩ ውሳኔ ያስገኛል

ግጭት ወይም አለመስማማት ሌላ ጥቅም አለው። አንዳንድ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንዳንድ ውጥረቶች ከሌሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች "ሁሉም መልካም ነው" ብለው ስለሚያስቡ አንዳንድ ጠቃሚ የሆኑ ነገሮችን ተወያይተው አይወስኑም። አንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የገንዘብ አቅሟ በጣም ትልቅ ባይሆንም፣ ችግር የለባትም። የቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢና ሽማግሌዎች በተለይ በገንዘብ በኩል ጠንቃቃ ናቸው። የቤተ ክርስቲያኒቱን ገንዘብ ያለአግባብ ያባክናሉ ብሎ የሚወቅሳቸው አማኝ የለም። ይሁን እንጂ፣ አንዳንድ አማኞች ቅሬታቸውን ማሰማታቸው አልቀረም። ቅሬታቸውም "ገንዘብ ያባክናሉ" በማለት ባይሆን፣ "ገንዘብ ባንክ ያጠራቅማሉ" የሚል ነው። እርግጥ ነው "ለክፉ ጊዜ ይሆናል" ብለው ባንክ ሃምሣ ሺ ብር አላቸው። ይሁን እንጂ፣ ቤተ ክርስቲያኒቱ ብዙ ነገር የጎደላት ናት። የሙዚቃ መሣሪያቸው ያረጀ ነው... የቤተ ክርስቲያኒቱ ጣራ ያፈሳል...የቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢ የሚሰጠው ደሞዝ ቤተሰቡን ማስተዳደር ስለማያስችለው፣ የሚያገለግለው ከወር እስከ ወር ድረስ እየተጨነቀ ነው...ከቤተ ክርስቲያኒቱ ዕርዳታ የግድ የሚያስፈልጋቸው አንዳንድ አማኞች አሉ። ይሄ ሁኔታ ደስ ያላሰኛቸው አንዳንድ አስተዋይ የሆኑ አማኞች ቅሬታቸውን አሰሙ። መሪዎቹም አስተዋዮችና ቀናዎች በመሆናቸው ቅሬታቸውን ባሰሙ አማኞች ላይ በመቆጣት ፈንታ ስብሰባ ጠርተው መወያየት ጀመሩ። "ሥራው የጌታ ከሆነ፣ ለራሱ ሥራ ግድ የሚለው አምላክ ከሆነ፣ ገንዘብ ባንክ ስናጠራቅም፣ ሲቸግረን አይደርስልንም ማለታችን አይደለም ወይ?" በማለት ቅሬታቸውን አሰሙ። መሪዎችም እንዴት በአመራራችን ላይ ጥያቄ አነሳችሁ በማለት ፈንታ፣ "ቅሬታችሁ ትክክል ነው" በማለት አዳዲስ ውሳኔዎችን አስተላለፉ። ለመጋቢው ቀለቡን አስተካከሉለት...ጣራውም ተሠራ...አዲስ የሙዚቃ መሣሪያ ተገዛ... እንዲሁም ሌሎች ለቤተ ክርስቲያኒቱ የሚያስፈልጓት ነገሮች ሁሉ ተሟሉ። ይህን ዓይነት ጥሩ ውሳኔዎች ሊተላለፍ የቻለው፣ እነዚያ ጥቂት ሰዎች ቅሬታቸውን በማሰማታቸው፣ መሪዎችም ከራሳቸው የተላቀቁ በመሆናቸው ነው።

## 3.3. ምዕመኑ በውይይቱ እንዲሳተፉ ዕድል ይሰጣል

በቤተ ክርስቲያና ለሚወስዱት እርምጃዎች ብዙ ጊዜ ውሳኔውን የሚያስተላልፉት የቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢና ሽማግሌዎች ናቸው። ለሚደረጉት ጥቃቅን ውሳኔዎች ሁልጊዜ ምዕመኑን ማሳተፍ አለባቸው ማለት አይደለም። ይሁን እንጂ፣ አንዳንድ ትላልቅ የሆኑትን ውሳኔዎችን ለመወሰን፣ ምዕመናኑን በውይይቱ ማሳተፍ አስፈላጊ የሚሆንበት ጊዜ አለ። ትላልቅ ናቸው የሚ[illegible]ት ውሳኔዎች እንዴት ዓይነቶቹ ናቸው?– "...የቤተ ክርስቲያናችንን ሥፍራ እንለውጥ...የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ እንግዛ..." ቤተ ክርስቲያኒቷ መጋቢ ከሌላት፣ "ለቤተ ክርስቲያናችን መጋቢ እንዲሆን ማንን እንጥራ?—

ከብዙዎቹ እነዚህ ጥቂቶቹ ናቸው። ሁሉም አጨቃጫቂና ለግጭት ምክንያት የሚሆኑ ናቸው። ይሁን እንጂ፣ ግጭትን በመፍራት ወደ ጎን ተገፍተው መቀመጥ ስለሌለባቸው ምዕመኑ በአንድ ላይ ተሰብስቦ እንዲወያዩበት ማድረግ አስፈላጊ ነው።

## 4. ለግጭቱ መፍትሄ በመፈለግ ፈንታ ችላ ማለቱ መፍትሄ አይሆንም

የብዙ ሰዎች ችግር ግጭት (አለመስማማት) እንዳለ እያወቁ፣ ምንም ዓይነት ችግር እንደሌለ አድርገው ሊያልፉት የሚሞክሩ መሆናቸው ነው። ግጭት መኖሩ በግልጽ እየታየ፣ ለተፈጠረው ችግር በወቅቱ መፍትሄ በመፈለግ ፈንታ፣ "ችላ ብለን ስንተወው በራሱ ይጠፋል ወይም ይስተካከላል" ብሎ ማለፍን እንደ መፍትሄ አድርገው ለመጠቀም የሚሞክሩ ሰዎች እንዳሉ የታወቀ ነው። ክርስቲያን የሆኑም ሆኑ ያልሆኑ፣ በቤተሰብ ውስጥ፣ በጎረቤት መካከል፣ እንዲሁም በመሥሪያ ቤት ውስጥ የሚፈጠሩትን ግጭቶች መፍትሄ በመፈለግ ፈንታ ችላ ብለው የሚያልፉት በምን ዓይነት ሁኔታ ነው? በሁለት ሰዎች መካከል ወይም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ግጭት (አለመስማማት) ሲፈጠር፦

*"አለመስማማት ወይም መጋጨት ጥሩ ጠባይ አይደለም..."*

*"መታዘዝ፣ መታገስ ጥሩ ምግባር ነው..."*

*"ጠባዩ ነው...ጠባዩዋ ነው... እዚሁ ላይ እንተወው..."*

*"...ምንም ችግር የለም... ሁሉም መልካም ነው..."*

*"...ተወው...እርሳው...ያንተ/ያንቺ ጉዳይ አይደለም..."*

ማለት የተለመደ ሆኗል። በባህላችን ግጭት ሲያጋጥም ፊት ለፊት በግልጽ መነጋገር፣ የተለመደ አይደለም። ልጅ ከአባቱ ጋር የማይስማማ አሳብ ማቅረብ ትክክል አይደለም ተብሎ ስለሚታሰብ፣ ልጆች ደስ የማይላቸው ነገር ሲያጋጥማቸው፣ ስሜታቸውን በመግለጽ ፈንታ፣ በውስጣቸው እያጠራቀሙ ያድጋሉ። ሁላችንም ያደግነው ይህን በሚመስል ሕብረተሰብ ውስጥ ነው። ዛሬ ለዚህ ነው በደንብ የሚያውቁን የውጪ አገር ዜጎች *"ኢትዮጵያውያን ስብሰባ ላይ ይስማማሉ፤ ከስብሰባው ወጥተው ከሄዱ በኋላ ግን አይስማሙም"*የሚሉን። አንድ ላይ ስንሆን፣ የማይስማማን ነገር በውስጣችን ቢኖር ፊት ለፊት ለመናገር ድፍረት ስለማይኖረን "ተስማምተናል፤ ሁሉም መልካም ነው" ብለን እንወጣለን። "ከእርሱ አስተያየት የተለየ አሳብ ብሰጥ ቅር ይለዋል" ብለው ከሚያስቡት ሰው ራቅ ብለው ሲሄዱ፣ አለመስማማታቸውን ጉዳዩ ለማይመለከተው ሰው ሲገልጹ ይገኛሉ። ቅሬታቸውን የሚዳምጠውም ሰው፣ "ስብሰባው ላይ ለምን አሳብህን አልገለጽክም? አሁን ለምን ለእኔ ትነግረኛለህ?" ብሎ በማለት በግልጽ አይነግራቸውም። ምክንያ



ቱም እርሱ ራሱ ነጋሪውን ቅር ማሰኘት ስለማይፈልግ ነው። እኛ ኢትዮጵያውያን ብዙ ጊዜ ግጭቶቻችንን በጥሩ ሁኔታ መፍታት እንዳንችል እንቅፋት (ምክንያት) የሚሆንብን ይሄ ነው። በብሉይ ኪዳን ውስጥ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን የመጀመሪያው የእስራኤል ንጉሥ የነበረው ሳኦል ነው። ሳኦል "ከዳዊት ጋር ችግር አለብኝ" በማለት ፊት ለፊት በመነጋገር ፈንታ፣ ምንም ችግር እንደሌለበት ሰው ዳዊትን በጥሩ ሁኔታ ያነጋግረዋል። ዳዊት ከአጠገቡ ዞር ሲል ግን በቅናትና በምቀኝነት ልቡ ተሞልቶ ሲያጠፋው ሲያሴርበት፣ እንዲሁም ሲያሳድደው እናያለን (1 ሳሙ. 18፥ 19፥ 24፥ 26)። አንዳንድ ሰዎች ግጭታቸውን ፊት ለፊት አውጥተው መግለጽ ሲያቅታቸው፣ ችግራቸው የሚገልጹበት የራሳቸው የሆኑ የተለያዩ መንገድ አላቸው። ይኸውም፦

*በአሽሙር ይናገራሉ፥*

*ነቀፋና አግባብ ያልሆነ አስተያየት ይሰጣሉ፥*

*የተጋጩትን ሰው በስውር ዕቅዱን ለማክሸፍ (ለማበላሸት) ይሞክራሉ፣*

*ያኮርፋሉ፣*

*ራሳቸውን ያሸሻሉ።*

ግጭትን መስመር ለማስያዝ በመሞከር ፈንታ፣ ችላ ብሎ ማለፍ የሚያስከትለው የራሱ የሆነ ችግር አለው። ለምሳሌ፣ በሁለት ሰዎች መካከል ግጭት ተፈጥሮ፣ በወቅቱ ግጭታቸውን መስመር ሳያስይዙት ችላ ብለው ከሆነ፣ ከጊዜ በኋላ በእነዚያ ሁለት ሰዎች መካከል ችግር እንዳለ የሚያሳዩ አንዳንድ ሁኔታዎች ጊዜያቸውን ጠብቀው መታየት ይጀምራሉ። በሁለቱ መካከል ያለው ጤናማ ያልሆነ ስሜት፣ የሁለቱን ሰዎች ብቻ ሳይሆን፣ የማህበሩንም አንድነት ወይም ግንኙነት የማበላሸት ዝንባሌ አለው። በአግባቡ መስመር ያላስያዝነው ግጭት፣ በውስጣችን መራራነት ሲፈጥር ስለሚችል፣ መንፈሳዊ ሕይወታችንን ብቻ ሳይሆን በሥጋችንም ውስጥ አንዳንድ ችግሮችን ሊያመጣ ይችላል። ዕንቅልፍ ይነሳናል። ለመንፈስ ጭንቀት፣ ለጨጓራችን መላጥ ምክንያት ይሆንብናል።

አንዳንድ ጊዜ በሰዎች መካከል የሚፈጠረው ግጭት፣ "ሳይሆን አይቀርም" በሚል ከተሳሳተ ግምት የመጣ ሲሆን ይችላል። በተፈጥሯቸው አንዳንድ ሰዎች ችግር ሳይኖር ችግር እንዳለ አድርገው የሚገምቱ አሉ። የሚያሳዝነው ግምታቸው መቶ በመቶ ልክ ነው ብለው የሚያምኑ መሆናቸው ነው። ለምሳሌ፣ ከምዕመናኑ መካከል አንዱ መጋቢውን "ፓስተር እከሌ" ብሎ በመጥራት ፈንታ "እከሌ" ብሎ በስሙ ቢጠራው፣ "እከሌ እኮ የእኔን ፓስተርነት አይቀበልም... ይንቀኛል... አያከብረኝም" የሚል ስሜት ይሰማውና በዚያ ሰው ላይ ልቡ የተቋጠረ ይሆንበታል። ያ ሰው ግን "ፓስተር እከሌ" ብሎ የማይጠራው፣ ፓስተሩን ስለሚጠላው፣ ስለማያከብረው፣ ወይንም ስላልተቀበለው ሳይሆን፣ ከቅርቡ የተነሳ የሚያደርገው ነው። ብዙ ጊዜ የምንቀርበውን ሰው በማዕረግ ስሙ አንጠራ

ውም። ለምሳሌ "ቀኛኸርማች" የሆነ ልጅ ያላቸው አባት፣ ልጃቸውን "ቀኛዝማች" ብለው እንደማይጠሩት የታወቀ ነው። የማይጠሩት ቅርባቸው ስለሆነ እንጂ፣ የልጃቸውን "ቀኛዝማችነት" ስላልተቀበሉት እንዳልሆነ ግልጽ ነው። በዚህ ዓይነት ጥቃቅኑን ነገር እየያዙ ሰው ያላሰበውን ሃሳብ እንዳሰበ አድርጎ በመቁጠር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ግጭትን የሚያስፋፉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አሉ። የሚያሳዝነው፣ የመሰላቸውን ትርጉም በመስጠት የቅሬታ ልብ ይዘው ሀሲናቸውን ሳይቆረቁራቸው የሚያገለግሉ መሆናቸው ነው። ያ ሰው ከልቡ ምንም ነገር ስለሌለ፣ "ፓስተሩ በእኔ ላይ ቅሬታ ይኖረዋል" ብለው ላያስብ ይችላል። እየቆየ ሲመጣ ግን አንድ ቀን የፓስተሩ ጥላቻም ሆነ ቅሬታ መፈንዳቱ አይቀርም። ያኔ ግጭታቸውን ከምንጊዜም የበለጠ ከባድ ሊያደርገው ይችላል። መንፈሳዊ መሪ፥ የአመራር ችሎታ እንዳለው ከሚለካበት መለኪያዎቹ መካከል አንደኛው፥ በምዕመናን መካከል እንዲሁም በእርሱና በምዕመናን መካከል ግጭት ሲፈጠር ግጭቱን ትክክለኛ መስመር ማስያዝ ወይም ማርገብ ሲችል ነው።

# ምዕራፍ ፲፩

# ተግባራዊ ዕቅድ

*"...ሁሉም ነገር በአግባብና በሥርዓት ይሁን"* (1 ቆሮ. 14፥40)

*"...ከኋላዬ ያለውን እየረሳሁ፣ ከፊቴ ወዳለው እዘረጋለሁ" (ፊልጵ. 3፥13)*

*"ከእናንተ አንድ ሰው ሕንጻ ለመሥራት ቢፈልግ፣ መደምደም መቻል አለመቻሉን በመጀመሪያ ተቀምጦ ዋጋውን የማይተምን ማን ነው? መሠረቱን ጥሎ መደምደም ቢያቅተው፣ ያዩት ሁሉ ይዘባበቱበታል።" (ሉቃ. 14፥28-29)*

- *"ግብ"* (Goal) *ወይም "ዓላማ" አቅጣጫችንን፣ የት መድረስ እንዳለብን (መድረሻችንን) ያመለክተናል፤*
- *"ቅደም ተከተል" (Priorities) ካሉን አማራጭ ነገሮች ውስጥ እንድንመርጥ ምርጫዎቻችንን ያሳየናል።*
- *"ዕቅድ" (Planning) ደግሞ ካሰብንበት ግብ ለመድረስ መውሰድ ያለብንን እርምጃዎችን ያሳየናል።*

ያለፈውን ውጤት መሠረት በማድረግ፣ እርግጠኛ ሆኖ "የወደፊቱም ይህንኑ ይመስላል" ማለት፣ አስቸጋሪ ነው። ከዚህ በፊት የተጠቀምንባቸው መንገዶች፣ ሁልጊዜ ከምንፈልግበት ደረጃ (ግብ) ሊያደርሱን ስለማይችሉ ካቀድነው አዲስ ግብ ለመድረስ ከጊዜው ሁኔታ ጋር አብሮ የሚሄድ "ዕቅድ" ማውጣት አስፈላጊ ነው። ዕቅድ ለማውጣት ደግሞ

መድረሻን ወይም ግብን (Goal) ማወቅ ያስፈልጋል። "ዕቅድ ማውጣት" (Planning) ከተፈለገበት "ግብ" ለመድረስ፣ መወሰድ ያለባቸውን እርምጃዎች ያመለክታል። በታቀደው ዕቅድ መሠረት ከተፈለገበት "ግብ" ሁልጊዜ መድረስ ይቻላል ማለት አይደለም። በሂደት ውስጥ ብዙ የምንለውጣቸውና የምናስተካክላቸው ነገሮች ይኖራሉ። ከታሰበው "ግብ" ወይም "ዓላማ" ለመድረስ፣ መሠራት ያለባቸውን ብዙ ነገሮች፣ ሁሉንም በአንድ ጊዜ ሠርቶ ለመጨረስ አቅምም ሆነ ጊዜ ስለማይበቃ፣ የሚሠሩት ነገሮች እንደ አስፈላጊነታቸው ቅደም ተከተል (Priorities) ማስያዝ አስፈላጊ ነው። የምንሠራውን ሥራ በቅደም ተከተል መሥራት ካልቻልን፣ ያወጣነው ጥሩ "ዕቅድ" ብቻውን ከምንፈልገው ግብ ሊያደርሰን አይችልም። ስለዚህ "ግብ" ማበጀት፣ ከታሰበው ግብ ለመድረስ "ዕቅድ" ማውጣትና፣ እንዲሁም ዕቅዶችን በቅደም ተከተል ተግባራዊ ማድረግ፣ ለምድራዊው ድርጅትም ሆነ ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት በጣም አስፈላጊ ነው።

## 1. ውጤታማ ዕቅድ ለማውጣት፥ ግልጽ የሆነ "ግብ" ያስፈልጋል

እጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ዕቅድ ከማውጣቷ በፊት፣ "ግቧን" በቅድሚያ ማወቅ አለባት። የምታወጣውም "ግብ" ሊለካና ልትደርስበት የምትችለው መሆን አለበት። ብዙ ጊዜ "መሆን"፣ ወይም "ማድረግ" የምንፈልገውን ነገር ማወቅ የምንቸገርበት ጊዜ አለ። የምንፈልገውን ካላወቅን ደግሞ፣ ግልጽ የሆነ ዕቅድ ማውጣት አስቸጋሪ ይሆንብናል። የምናወጣው "ግብ" ግልጽ ከሆነ፣ ሰዎች ሊረዱት የሚችሉት "ዕቅድ" ማውጣት እንችላለን። የምናወጣው ዕቅድ ያለፈውን ልምምዳችንን መሠረት አድርገን ይሁን እንጂ፣ ወደፊት ልንደርስበት ያሰብነውን ግብ በአዕምሯችን ይዘን ነው። ዕቅዳችን ምንም ያህል ጥሩ ቢሆን፣ ውጤቱ መቶ በመቶ እንዳሰብነው ላይሆን ይችላል። የወደፊቱ ምን እንደሚመስል በግልጽ ማወቅ የማይቻል ከሆነ፣ ታዲያ ዕቅድ ማውጣቱ ምን ያደርጋል?" ብለን መጠየቃችን አይቀርም። አንወቅ እንጂ፣ ከምንፈልግበት ደረጃ ለመድረስ የሚያስችለንን ዕቅድ ማውጣት ጠቃሚነት የማያጠራጥር ነው። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ የሚለካና ሊደርሱበት የሚችሉት ግብ ሲኖራቸው፣ ከወሰኑት ግብ የሚያደርሳቸውን ዕቅድ አውጥተው በቅደም ተከትለ ሥራቸውን ከሠሩ አገልግሎታቸው ፍሬያማ ሊሆን ይችላል።

- *ግባቸው (Goal)* ~ ግባቸው ምንድነው? "በሚቀጥለው ዓመት መጨረሻ ላይ ሃምሣ አዲስ ነፍሳት ድነው የቤተ ክርስቲያን አባል እንዲሆኑ" የሚል ይሆናል። ይሄ ሊለካ የሚችል፣ (50 አዳዲስ ነፍሳት) ግልጽ የሆነ ግብ ነው።
- *"ዕቅዳቸው" (Planning)* ~ ካሰቡት ግብ ለመድረስ ዕቅዳቸው ምን ለማድረግ ነው? ካወጡት ግብ ለመድረስ፣ ያወጡት ዕቅድ (1) የምስክርነት ጓድ ማቋቋም... (2) የምስክር ጓድ አባል የሚሆኑትን ከምዕመናን መካከል መርጠ የአንድ ሳምንት ሥልጠና አዘጋጅቶ መስጠት፥... (3) አንድ ሺ ትራክቶች (መጣጥፎች) ማሳተም፥... (4) በሳምንት አንድ ቀን የምስክር ጓድ አባሎች ወደ ከተማ ወጥተው ትራክት እንዲሰጡና እንዲመሰክሩ ማድረግ፥... (5) በየሁለት ወሩ ለአዳዲስ ነፍሳት ኮንፍራንስ ማዘጋጀት፥ ወዘተ ይሆናል። ይሄም ሊደረግ የሚችል ግልጽ የሆነ ዕቅድ ነው።



- ***ቅደም ተከተል" (Priorities)*** ~ የቤተ ክርስቲያኒቷ መሪዎች ባወጡት ዕቅድ መሠረት ካሰቡበት ግብ ለመድረስ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ አለባቸው። ይሁን እንጂ ሁሉንም በአንድ ጊዜ ለማድረግ ስለማይችሉ፣ ለሚሠሩት ነገር ቅደም ተከተል ሊኖራቸው ይገባል። ግልጽ የሆነ "ግብ" ማበጀት፣ ዕቅድ ማውጣት፣ የሚሠሩትን ሥራዎች ቅደም ተከተል ማስያዝ ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት ጠቃሚና አስፈላጊ ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ *"...ሁሉም ነገር በአግባብና በሥርዓት ይሁን"* (1 ቆሮ. 14፥40) ሲል፣ ቤተ ክርስቲያን ስለአመራሯ ሥርዓት፣ እንዲሁም ለአሠራሯ ዕቅድ አስፈላጊ መሆኑን ያመለክታል። ቤተ ክርስቲያን አገልግሎቷን እንደሚገባው መፈጸም እንድትችል፥ ዕቅድ ብታወጣ፥ በበጀት ለመተዳደር ብትሞክር፣ በተለይ በአንዳንድ ኢትዮጵያውያን መሪዎች መካከል ሥጋዊ እንደሆነች፣ ወይም መንፈሳዊነት እንደ ጎደላት አድርገው የሚያስቡ ሰዎች እንደማይጠፉ የታወቀ ነው። አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መጋቢዎች ዕቅድ ማውጣትን፥ ሥርዓት ያለው አመራርን ለመቃወም ሲሉ *"በእምነት እንጂ በሰው ዕውቀትና ጥበብ አንመራም"* ይላሉ። የዚህን አባባል ትክክለኛነት ያልተረዱ አንዳንድ የዋህ ክርስቲያኖች *"መጋቢያችን የእምነት ሰው ነው"* በማለት ሲያደንቋቸው እንሰማለን። ሥርዓትን የሚቃወሙት በቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ብቻ ሳይሆን፥ በሚያስተምሩት ትምህርትና በሚሰብኩት ስብከትም ጭምር ነው። *"ጌታ የሰጠኝን እንጂ፥ አዘጋጅቼ ፑልፒት ላይ አልወጣም። መጽሐፍ ቅዱሴን ለሁለት ፍንከት ሳደርገው ጌታ መንፈስ ቅዱስ የሰጠኝን ነው የምሰብከው"* ይላሉ። ለዚህ ነው በአሁኑ ጊዜ በየአብያተ ክርስቲያናቱ መንፈሳዊ ምግብ በማጣት ብዙ ክርስቲያኖች በመንፈሳዊ ረሀብ የሚያልቁት። ይህን ዓይነቱ አባባል ለሰነፎች፥ ጊዜ ወስደው ለማጥናትና ለመዘጋጀት ለማይወዱ፥ ዕውቀትን ለሚጠሉ ይመቻል።

"ግብ" ማለት ምንድነው? *"ግብ" የወደፊቱን (የሩቁን) የሚያሳይ "ሥዕል" ነው።*[38] እዚህ ላይ "የወደፊት" ማለት ከአንድ ወይም ከሁለት ወር በኋላ የሚሆነውን የሚያሳይ ማለት አይደለም። ስአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን "የወደፊቱን የሚያሳይ" የሚለው አሳብ፣ በረጅም ጊዜ ውስጥ የሚፈጸም፣ ወይም የቤተ ክርስቲያኗን ዋና ዓላማ የሚያሳይ ነው። ጥሩ የሆነ "ግብ"፣ የሚባለው፣ ሊለካና እንዲሁም ሊደረስበት (ሊፈጸም) የሚችል ሲሆን ነው። የቤተ ክርስቲያኒቷ መሪዎች "ግብ" ሲያወጡ፣ በሥራ ሊተረጎም ወይም ሊሠራ የሚችል መሆኑን እርግጠኞች መሆን አለባቸው። "ግብ" ሊለካ የሚችል መሆን አለበት ስንል፣ የሚለካው በምን ዓይነት ነው? ብለን መጠየቃችን አይቀርም። "ግብ" በሁለት ዓይ

---

[38] Edward R. Dayton & Ted W. Engstrom

ነት መንገድ ይሰካል። ይኸውም አንደኛ፣ በጊዜ ይለካል። ከታሰበው ግብ መድረስ የሚቻለው መቼ እንደሆነ መታወቅ አለበት። ሁለተኛ፣ በተገኘው የፍሬ ውጤት ይሰካል። ለምሳሌ አንድ አማኝ "ከዛሬ ጀምሮ ጥሩ ክርስቲያን እሆናለሁ" ቢል፣ ግቡ "መቼ?" የሚለውን የጊዜ ጥያቄ አይመልስም። እንዲሁም በአጠቃላይ "ጥሩ ክርስቲያን" ማለቱ ምን እንደሆነ በግልጽ አይታወቅም። ስለዚህ ይሄ ምሳሌ በጊዜና በተግባር ሊለካ የማይችል በመሆኑ ጥሩ ግብ የሚባል አይደለም። አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የራሷ የሆነ ጥሩ ግብና ዕቅድ ሲኖራት፥

- *የአገልግሎቱ ተካፋይ የሆኑት አማኞች ሁሉ፣ ዓላማና መመሪያ ይኖራቸዋል።*
- *ቤተ ክርስቲያኒቱ ምን ዓይነት አቋም ላይ እንዳለች ይታወቃል።*
- *ምዕመናን፣ ለዕድገቷ በየትኛው ሥፍራ ሆነው ማገልገል የሚችሉበትን ሁኔታ ያሳያቸዋል።*

"መድረሻህን ካላወቅህ፣ የትኛውንም መንገድ ብትወስድ ያደርስሃል" የሚል አባባል አለ። መድረሻቸውን ወይም ዓላማቸውን የሚያውቁ የአገልግሎት ተሳታፊዎች፣ አንድ ዓላማ ኖሯቸው በሕብረት መጓዝ ይችላሉ። አሞጽ *"በውኑ ሁለት ሰዎች ሳይስማሙ አብረው መጓዝ ይችላሉን?"* (አሞጽ 3፥3) ሲል፣ በዓላማ አንድ ያልሆኑ ሰዎች አብረው መሄድ እንደማይችሉ መግለጹ ነው። ሰዎች ዓላማቸውን (ግባቸውን) እውቀው በአንድ ላይ መሥራታቸውን ሲያዩ፣ ሕብረታቸውን የበለጠ ያጠናክራሉ። ምዕመናን በአንድ ዓላማ ሥር ሆነው ሲያገለግሉ፣ የበለጠ የሚቀራረቡ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን፣ በአገልግሎታቸውም የበለጠ ፍሬያማ ይሆናሉ።

## 2. "ዕቅድ ማውጣት" (Planning)

*"ዕቅድ ማውጣት" (Planning)* የሚለውን ቃል፣ በግሪክ የተጻፈው አዲስ ኪዳን በሁለት የተለያዩ ቃላት ገልጾታል።

- አንደኛው፥ *"ኤስኪሞኖስ" (EUSCHEMONOS)* የሚለው ቃል ሲሆን፣ ትርጉሙ በሥርዓት መሆን ማለት ነው። ጳውሎስ በሮሜ 13፥13 ላይ ይህን ቃል ተጠቅሞበታል። በሕብረተሰብ ውስጥ ሥርዓት ያልሰቀቀ ሕይወት ይዘን እንድንኖር ሲመክር ይህንን ቃል ተጠቅሞ *"...በአግባብ እንመላለስ..."* ይላል። በቤተ ክርስቲያን አምልኮትም፣ ሥርዓት እንዳንለቅ ሲመክረን፣ *"ሁሉም በአግባብና በሥርዐት ይሁን"* ይላል (1 ቆሮ. 14፥40)።



- ሁለተኛው የግሪክ ቃል *"ታክሲስ" (TAXIS)* የሚለው ቃል ሲሆን፣ ትርጉሙም *"ማደራጀት...ቅደም ተከተል ማስያዝ..."* ማለት ነው (ቆላ. 2፥5)።[36]

አንዳንድ መንፈሳዊ መሪዎች፣ አገልግሎታቸው ፍሬያማ እንዲሆን ዕቅድ ማውጣት እንዴት እንደሚችሉ ከሚያውቁትና ከተረዱት ሰዎች ጠይቆ በመረዳት ፈንታ፥ አለማወቃቸውን ለመሸፈን፥ *"እኔ በእምነት እንጂ በሰው ዕቅድ አልመላለስም"* በማለት የእምነት ሰዎች ለመምሰል በመሞከር ራሳቸውን ብቻ ሳይሆን የሚያገለግሉትንም ሕዝብ ይጎዳሉ። የምዕራቡ ዓለም *"ኢላማ ከሌለን ምንጊዜም ተኩሰን አንስትም"* የሚል አነጋገር አላቸው። ይኸውም፥ ተኩሶ ለመምታት የሚፈልገው ምንም ዓይነት ዒላማ ከሌለው፣ ዝም ብሎ መተኮስ ከሆነ፣ ይህን ያህል ከባድ አይደለም። ያለ "ዕቅድም" ወይም አንድ ዓይነት ግብ (ዓላማ) ሳይዙ ቤተ ክርስቲያንንም ሆነ ሌላውን ድርጅት "በመላ ምት" ለመምራት መሞከር ልክ እንደዚሁ ነው። ማንኛውም ሰው ጉዞ ከመጀመሩ በፊት የት መሄድ እንደሚፈልግ ወይም እንዳሰበ አስቀድሞ ማወቅ አለበት። *"ጉዞዬን ልጀምርና የት ለመድረስ እንደምፈልግ ከዚያ በኋላ እወስናለሁ"* ቢል፣ ወይም *"የት እንደምሄድ መንፈስ ቅዱስ ያሳየኛል"* ብሎ ጉዞ ቢጀምር፣ ያንን ሰው *"የእምነት ሰው ሳይሆን ሞኝ"* ያሰኘዋል። በተጨማሪ ጊዜውን፥ ጉልበቱን ያለአግባብ ያባክናል። መንገድና መድረሻውን አስቀድሞ የሚያውቅ፣ መድረስ ከሚፈልግበት ቦታ እንዴት መድረስ እንደሚችል አስፈላጊውን ዕቅድ ያወጣል።

"ግብ" መድረሻችንን ሲያመለክት፣ "ቅደም ተከተል"፣ ካቀድንበት ግብ ለመድረስ ከምንሠራቸው ሥራዎች ውስጥ የትኛውን ሥራ (ተግባር) ቅድሚያ መስጠት እንዳለብን አሳብ ይሰጠናል። "ዕቅድ" ማውጣት ደግሞ ካቀድንበት "ግብ" ለመድረስ፣ ያለምነውን ሕልማችንን እውን የምናደርግበት መንገድ ነው።

- *1ኛ/ ግብና ዕቅድ ሲኖር፣ በድርጅቱ መዋቅር ሥር ያሉት ኃይላቸውንና ጉልበታቸውን ለአንድ ዓላማ ስለሚያስተባብሩ፣ በሰዎች መካከል ጥሩ አንድነትን (ግንኙነትን) ይፈጥራል። አብሮ ግብ ከማበጀት፣ ስለ ወደፊቱ አብሮ ዕቅድ ከማውጣት፣ በጸሎት መንፈስ ሆኖ እግዚአብሔርን በአንድነት ከመጠበቅ የሚበልጥ (የሚሻል) ሰዎችን አንድ የሚያደርግና የሚያስተባብር ሌላ ነገር የለም።*
- *2ኛ/ ግብና ዕቅድ ሲኖር፣ ድርጅቱን (ቤተ ክርስቲያኒቱን) በሚመለከት አሳብ ላይ ጥሩ ውይይት ማድረግ ይቻላል። ስለ ወደፊቱ ዕቅድ ማውጣት፣ ወቅታዊ ችግር ቢኖር መቻቻልን ያስገኛል። በወቅቱ ባለው ችግር ላይ ትኩረት ሰጥቶ ከመወያየት፣ ዓይናችንን አንስተን ወደ ፊት ስለሚሆነው እንድናይ እንሆናለን።*

---

[36] Morris, H. Charles

- *3ኛ/ ግብና ዕቅድ ሁልጊዜ የሚያመለክተው ወደፊት ስለሚሆነው፣ ገና ያልተፈጸመ አሳብ ላይ በመሆኑ፣ የተበላሸ ነገር ቢኖር፣ ሁኔታውን ለመለወጥና ልክ ለማድረግ ተጨማሪ ጊዜ፣ አዲስ አሳብ ለማግኘት ጊዜን ይሰጣል።"*[37]

## 3. ለጥሩ ዕቅድ አወጣጥ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች

ዕቅድ ማውጣት፣ ከተፈለገበት ግብ ወይም ዓላማ የሚያደርስ "ሂደት" (process) ነው። "ዕቅድ ማውጣት" አርቆ ማሰብንና ሰፊ ጊዜን ይጠይቃል። ዕቅድ አውጪው ሁልጊዜ ተስፋ ማድረግና አርቆ ማሰብ አለበት። ያም ሆኖ አንዳንድ ጊዜ ዕቅዳችን በሥራ ላይ የማይውልበት ጊዜ ሊኖር እንደሚችል በቅድሚያ ማወቅ ይጠቅማል። ያቀድነው ዕቅድ በሥራ ላይ በማይውልበት ወቅት ተስፋ በመቁረጥ ፈንታ "እግዚአብሔር ለክብሩ ሲል፥ ምን ለመሥራት አስቦ ይሆን?" በማለት በጎ ነገር መጠበቅ ይገባናል። ዕቅዳችን በሥራ እንዲውል፣ ከሚመለከታቸው ጋር መመካከር ወይም መወያየት፣ ይጠቅማል። ሰሎሞን *"ምክር ሲጓደል ዕቅድ ይፋለሳል፤ በብዙ አማካሪዎች ግን ይሳካል"* (ምሳሌ 15፥22) ይላል። አንዳንድ ችግሮችን ለመፍታት ብዙ ጥቃቅን የሆኑ ሁኔታዎች፣ እንዲሁም ተግባራት ስላሉ ነው "ዕቅድ" ማውጣት አስፈላጊ የሚሆነው። ኋይት የተባሉ ጸሐፊ፥

> *"ሁኔታዎች ሁሉ በነጠላ ወይም ለብቻቸው የማይፈጸሙ መሆናቸውን መረዳት የጥሩ ዕቅድ አወጣጥ መሠረት ነው። ለማንኛውም ሁኔታ፣ ቀዳሚ ሁኔታዎች (ነገሮች) እንዳሉት ሁሉ፣ ተከታይ የሆኑ ነገሮችም አሉት። እነዚህ ሁኔታዎች እርስ በርሳቸው ለሚኖራቸው ግንኙነት፣ የተፈጥሮ ሕግ ወሰኝነት አለው። ስለዚህ ዕቅድ ማውጣት፣ ነገ የምንፈልገውን ዓይነት ውጤት ለማግኘት፣ ዛሬ የተወሰኑ ነገሮችን ማድረግ ማለት ነው" ሲሉ።*[38]

*ለጥሩ ዕቅድ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች አሉ። ይኸውም፥*

### 3.1. ሠራተኞች

ሥራውን ለማከናወን ወይም ለመጨረስ ምን ያህል ሰዎች እንደሚያስፈልጉ፥ ኃላፊነቱን ማን እንደሚወስድ፥ ማን ምን እንደሚሰራ በዝርዝር ማወቅ፥ ለጥሩ ዕቅድ አስፈላጊ ከሆኑት ነገሮች መካከል አንደኛው ነው። እዚህ ላይ ትኩረት ሊሰጥባቸው ከሚያስፈልጉ ነገሮች መካከል አንደኛው፥ ሁኔታው በሚመለከታቸው ሰዎች መካከል ሊኖር

[37] Edward R. Dayton & Ted W. Engstrom, Strategy For Leadership, Fleming H. Revell Co. Old Tappan, New Jersey, 1960.
[38] White, Ernest. The Desk of Decision, (Nashville: Church Administration, 1976).



የሚገባ ግልጽ የሆነ ግንኙነት (communication) ነው። መንፈሳዊ መሪው ዕቅድ የማውጣቱን ሂደት በአዕምሮው ውስጥ በቅድሚያ ማስላበል አለበት። ቀጥሎ፣ ሥራውን ጥሩ አድርገው ሠርተው መጨረስ የሚችሉ፥ ለሥራው ኃላፊነት ሊሰጣቸው ይገባል ተብለው የታሰቡት ሰዎች በቅድሚያ መታወቅ አለባቸው። አንዳንድ መንፈሳዊ መሪዎች እነርሱ ብቻ ዕቅዱን አውጥተው መጨረስ ያለባቸው ይመስላቸዋል። እርግጥ ነው በመጀመሪያ ደረጃ ያለውን ዕቅድ እነርሱ ማበብ አለባቸው። ይሁን እንጂ፥ ፕሮጀክቱ በበፋ ቁጥር በዕቅድ አወጣጥ ሥራው ላይ ብዙዎች እንዲካፈሉ ዕድል መስጠት የበለጠና የተሻለ ውጤት ያስገኛል። በአሁኑ ጊዜ እኔ በሽምግልና በማገለግልበት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሳለፍነውን ልምምድ ለትምህርታችን እንዲሆን ልጥቀስላችሁ። በአንድ ወቅት ቤተ ክርስቲያኒቱ በጣም እያደገች በመሄዱ፥ በቦታ ጥበት የተነሳ ዕድገቷ ወደ ኋላ እንዳይጎተት ወይም እንዳይቆም የቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢ (ፓስተር) ማሰብ ጀመረ። በወቅቱ የነበረውን ራዕይ አብረነው ለምናገለግለው የቤተ ክርስቲያኒቱ ሽማግሌዎች አካፈለን። እኛም ሽማግሌዎች ራዕዩ ትክክልና ጊዜውን የጠበቀ መሆኑን ስናምን በትን፥ ሽማግሌዎች ብቻ ሳንሆን፥ በተለያየ ሙያ ዕውቀት ያላቸው ሌሎች ምዕመናን ራዕዩ በተግባር የሚውልበትን ዕቅድ በማውጣት እንዲተባበሩ ራዕዩ ተገለጠላቸው። በመጨረሻም ለቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት በሙሉ፣ ሊሠራ የታሰበው ዕቅድ ተገለጸ። ብዙዎች የመከሩበት ዕቅድ በመሆኑ፥ ውጤቱ በጣም ያማረ ሆነ።

### 3.2. አስፈላጊ የሆኑ (Resources) ሀብቶች

አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች የሚባሉት ምንድንናቸው? ከማንኛቸውም አስፈላጊ ነገሮች ሁሉ የበለጠ "የመንፈስ ቅዱስ" አገልግሎት በሕይወታቸው የሚታይባቸው ሰዎች ናቸው። እዚህ ላይ "ሰዎች" ስንል፣ እነዚህኛዎቹ ዕቅዱን የሚያወጡት ባይሆኑ የታቀደው ሥራ ተጀምሮ እስከሚያልቅ ድረስ፣ በተለያየ ዘርፍ ተሰልፈው ሥራውን የሚሠሩት ናቸው። እነዚህ ሥራውን የሚሠሩት ሰዎች በዝርዝር እነማን እንደሆኑ መታወቅ አለባቸው። ተፈላጊ የሆኑ ዕቃዎች ቢያልቁ ይገዛል፤ ወይም አንዳንድ ነገር የጎደላቸው ዕቃዎች ቢኖሩ በቀላሉ መቀየር ይቻላሉ። ሰውን ግን እንደ ዕቃ በቀላሉ የምንለውጠው ወይም የምንተካው ስላልሆነ፣ የበለጠ ጥንቃቄ ያስፈልገዋል። እግዚአብሔር ለመሥራት ያሰበውን ወይም ዓላማውን ለብቻው መፈጸም ቢችልም፣ የመረጠው ከሰው ጋር በመተባበር ነው። ለዚህ ነው እግዚአብሔር በዘመናት ለዓላማው ይስማማሉ፣ ብቃት አላቸው የሚላቸውን ሰዎች በቅድሚያ መርጦ የሚሾማቸው። የታቀደውን ሥራ ሠርቶ ለመጨረስ ሌላው አስፈላጊ ነገር፣ ፋይናንስ ወይም ገንዘብ ነው። ፕሮጀክቱን ሠርቶ ለመጨረስ ምን ያህል ገንዘብ እንደሚያስፈልግ በቅድሚያ መታወቅ አለበት። በዚህ አቅጣጫ ዕውቀት ያላቸውን ሰዎች እንዲሳተፉ ማድረግ መሪዎችን ከብዙ ችግር ያድናቸዋል። ፕሮጀክቱን ለመፈጸም ምን ያህል ገንዘቡ እንደሚበቃ መተመን ብቻ ሳይሆን፣ ገንዘቡ

ከየት እንደሚመጣ መታወቅ አለበት። በዕቅድ አወጣጥ ውስጥ ይህን ዓይነቱ ጥያቄ በጣም አስፈላጊ ነው። አስፈላጊው ገንዘብ ከምዕመናኑ የሚሰበሰብ ከሆነ፤ በምን ዓይነት ሁኔታ እንደሚሰበሰብ በጥንቃቄ መታቀድ አለበት። ብዙ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት በተለይ አሜሪካ ውስጥ ብዙ ችግር ላይ የወደቁት፤ የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ለመሥራት በተነሱበት ወቅት ነው። የተነሱበት ዓላማ ጥሩ ይሆን እንጂ፤ በዕቅድ አወጣጣቸው ላይ ብዙ ስህተት በማድረጋቸው ምክንያት ዋናውን መንፈሳዊ አገልግሎታቸውን እንዳበላሸባቸው ይታወቃል።

## 3.3. እንቅፋቶች ሊደርሱ እንደሚችሉ በቅድሚያ ማወቅ

የትኛውም መንፈሳዊ አገልግሎት፣ ከእንቅፋት ሁሉ ነጻ የሆነ የለም። ስለዚህ አንድ ነገር ለመሥራት ሲታቀድ ያልታሰበ "ዕንቅፋት" ሊደርስ ይችላል ብሎ አስቀድሞ ማሰብ፤ በጣም ጠቃሚ ነው። ሥራውን ወደ ኋላ የሚጎትት፤ ወይም የሚያቆም የገንዘብ ዕጥረትና እንዲሁም ሌሎች ችግሮች ቢከሰቱ እንዴት አድርገው መወጣት እንደሚችሉ መንፈሳዊ መሪዎች አስቀድመው መወያየትና ዕቅድ ማውጣት ያስፈልጋቸዋል። ጥሩ ነገር ለመሥራት የሚያስብ ሰው፣ "እንዲህ ዓይነት እንቅፋት ይደርስ ይሆናል" ብሎ አስቀድሞ ማሰብና መወያየት ደስ የሚለው ሰው አይኖርም። ይሁን እንጂ፣ ጥሩ መሪዎች፤ ራዕያቸውን በተግባር ለማዋል ሲነሱ፤ ሊደርሱ ይችላሉ ብለው የሚያስቡአቸውን አንዳንድ እንቅፋቶችን አስቀድሞ ማወቅ፣ ይጠቅማቸዋል እንጂ አይጎዳቸውም። ምናልባት ሊደርስ ይችላል ብለው የፈሯቸው አንዳንድ ችግሮች ከተፈጠሩ፣ በምን ዓይነት ሁኔታ እነዚያን ችግሮቹን ማቃለል እንደሚችሉ አስቀድሞ በመወያየት መፍትሄ ሊያዘጋጁ ይችላሉ። የፈሩት እንቅፋት ቢደርስ፤ በመደናገጥ ፈንታ ቀድሞ ባዘጋጁት ዕቅድ መሠረት ሥራቸውን ይቀጥላሉ። ዕንቅፋት የእውነተኛ መሪዎች ጉልበት መመዘኛ ወይም መለኪያ እንደሆነ ምሁራን ይገልጻሉ። አንዳንድ መሪዎች በመንገዳቸው ላይ እንቅፋት ሲያጋጥማቸው ችግሩን ለመፍታት መፍትሄ በመፈለግ ፈንታ፤ ወዲያው ተስፋ ቆርጠው የጀመሩትን ከዳር ሳያደርሱ ቶሎ ያቆማሉ። መንፈሳዊ መሪዎች ችግር ሲያጋጥማቸው ተስፋ ቆርጠው ከመውጣታቸው በፊት መጠየቅ ያለባቸው ጥያቄዎች አሉ። ይኸውም፤

ለመሥራት የተነሳንበት ዓላማ አስፈላጊ ነው ወይ?

የምናገለግላቸውን በጎች ችግር የሚያቃልል ወይም የሚያሟላ ነው ወይ?

ለእግዚአብሔር ክብር ይሆናል ወይ?

የእግዚአብሔር ፈቃድ አለበት ወይ?

ለነዚህ ጥያቄዎች የሚያገኙት መልስ "አዎን" የሚል ከሆነ፤ ተስፋ ቆርጠው በመተው ፈንታ ወደ ፊት ሊገፉበት ይገባል። መንፈሳዊ መሪዎች ዕንቅፋት ሲያጋጥማቸው



ከዚህ በፊት ያላወቁት፤ መማር ያለባቸው ነገር እንዳለ ራሳቸውን መጠየቅ አለባቸው። ይኸውም፤

- "በሩ ዝግ ነው፤ ዓላማህን ለመፈጸም ከዚህ በላይ አትሂድ" ማለት ይሆን?
- ሥራው መሠራት ያለበት በዚህ ሳይሆን፤ በሌላ መንገድ ነው" ማለት ይሆን?
- እምነቴ እየተፈተነ ይሆን?
- ሥራውን ስንጀምር በደንብ ሳንመለከተው የቀረነው፤ ሳንሠራው የቀረነው ነገር ይኖር ይሆን?
- ባጋጣሚ እንቅፋት ምክንያት የበለጠ ለሥራው የተሰጠን እንድንሆን፤ እንዲሁም በሙሉ ልብና በቆራጥነት እንድንሠራ ለመቀስቀስ ይሆን?
- ምን ያህል ደካማዎች መሆናችንን ተረድተን በጌታ ብቻ እንድንታመን ይሆን?

በማለት ራሳቸውን መጠየቅ አለባቸው። መንፈሳዊ መሪዎች በመንገዳቸው ላይ አንዳንድ ዕንቅፋቶች ሲያጋጥማቸው መፍራትና መንቀጥቀጥ የለባቸውም። ምክንያቱም አንዳንድ ጊዜ "ዕንቅፋት" ይሆናል ብለው ያልጠበቁትን ልዩ በረከት ይዞላቸው ሊመጣ ስለሚችል ነው። "ዕንቅፋትን" በዕቅዳቸው ውስጥ አስገብተውት ከሆነ፤ ዕንቅፋት ሲያጋጥማቸው በመደንገጥ ፈንታ፤ መፍትሄ ይፈልጉለታል።

## 4. ዕቅድ ማውጣት በእግዚአብሔር አለመተማመን ይሆን?

በእምነትና "በማቀድ" መካከል ያለውን አለመግባባት እንዴት ማስታረቅ እንችላለን? ዕቅድ ማውጣት ወይስ እግዚአብሔርን ተማምኖ መጠበቅ ወይም ማድረግ? አንዳንዶቻችን የእኛ ዕቅድ ማውጣት እግዚአብሔር የራሱን አሳብ፤ የፈቀደውን እንዳይሠራ እንቅፋት ይሆንበት እንደሆን፤ እንዲሁም ዕቅዳችን ወደ እግዚአብሔር ፈቃድ የበለጠ ይመራን እንደሆን መረዳት ያቅተናል። አንዳንዶች *"ማቀድ ወይም ዕቅድ ማውጣት እግዚአብሔር ብቻ ሊያደርገው የሚገባውን ነገር እኛ እናድርግ ማለታችን ስለሚሆን ፍጹም ትክክል አይደለም"* የሚሉ አሉ። ይሁን እንጂ፤ ይህን ዓይነት አቋም የያዙ መንፈሳዊ መሪዎች በአገልግሎታቸው ዕቅድ አውጥተው ስለማይሠሩ ብዙ ነገር ሲበላሽባቸው፣ የጠበቁትን ዓይነት ውጤት ባያገኙ ሲቀሩ እናያለን። ዕቅድ ማውጣት አስፈላጊነቱን እንመን እንጂ የሰው ዕቅድ ሁልጊዜ "የክርስቶስ ፈቃድ አለበት" ማለት አይደለም። የክርስቶስ ፈቃድ ከሌለበት፣ ሰው ምንም ያህል የረቀቀ ዕቅድ ቢያወጣ፣ ዕቅዱ ፍሬ ቢስ ነው። የክርስቶስ ፈቃድ የሌለበት ዓላማ፣ ዕቅድ ሳናወጣ ብንቀር፣ የተዝረከረከ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ፍሬ ቢስም ነው። እንዲሁም የክርስቶስ ፈቃድ በሌለበት ዓላማ ውስጥ ዕቅድ

ብናወጣ ደግሞ፣ ሁኔታው የተደራጀና መልክ ያለው መስሎ መጨረሻው ፍሬ ቢስ ሊሆን ይችላል። በዚህ ዓይነት በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው? በመንፈስ ቅዱስ ሳንተማመን ብንደራጅም፤ ባንደራጅም ኃይል የሌለን ነን። ዕቅድ ብናወጣም ባናወጣም በክርስቶስ ካልታመንን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውን ዓይነት ውጤት አናመጣም።

ዕቅድ ኖሮንም ሆነ ዕቅድ ሳይኖረንም፤ መንፈስ ቅዱስ እንዳይሠራ እንቅፋት መሆን እንችላለን። በሐዋርያት ዘመን በነበረችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰዎች ትክክለኛ ዕቅድ ስላልነበራቸው፣ አንዳንድ መበለቶች እንደተረሱ እናስታውሳለን (የሐዋ. 6፥1-6)። ይሁን እንጂ አንዳንድ መንፈሳዊ መሪዎች ትኩረት መስጠት ያለባቸው ለተራቡት ሰዎች መሆን ሲገባው፣ ትኩረታቸው ጥሩ ዕቅድ ማውጣቱ ላይ ይሆናል። እንግዲያውስ ሰዎች በመንፈሳዊ ረሀብ ሲያልቁ፤ ችግሩን ዕቅድ በማውጣት ማስተካከል የለብንም ወይ? ብለን መጠየቃችን አይቀርም። መጠንቀቅ ያለብን መንፈስ ቅዱስ ብቻ የሚሠራውን ሥራ፤ እኛ እንሠራለን እንዳንል ብቻ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ዕቅድ ማውጣት መንፈሳዊነት የጎደለው መስሎ የሚሰማቸው አሉ። "ዕቅድ ስናወጣ በእግዚአብሔር በመተማመን ፈንታ ባወጣነው ዕቅድ መተማመናችን አይሆንም ወይ?" ብለው ይጠይቃሉ። እዚህ ላይ አንድ መረዳት ያለብን እውነት አለ። ይኸውም፣ መንፈሳዊ አገልግሎታችንን ለመፈጸም ገንዘብ፤ ሕንጻ፤ የሰዎች ጉልበት እንደሚያስፈልገን የታወቀ ነው። እነዚህ ሁሉ የእግዚአብሔርን ዓላማ የምንፈጽምባቸው አስፈላጊ የሆኑ "መሣሪያዎች" ናቸው። "ዕቅድም" ልክ እንደዚሁ የእግዚአብሔርን ዓላማ ከምንፈጽምባቸው ነገሮች አንደኛው መሣሪያ ነው። መንፈሳዊ መሪዎች በግል ሕይወታቸው ስለ ወደፊቱ ጠቃሚ ዕቅድ የሚያወጡ ከሆነ፤ ለመንፈሳዊ አገልግሎት ዕቅድ ማውጣቱ ታዲያ ችግሩ እምኑ ላይ ነው?

"ዕቅድ ማውጣት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው ወይ?" ብለን የምንጠይቅ ከሆነ፣ እግዚአብሔር ራሱ በዕቅድ የሚያምን አምላክ መሆኑ እንዘንጋ። ዓለምን ከመፍጠሩ በፊት ሰው ምን ዓይነት መሆን እንዳለበት ዕቅድ ነበረው። እኛም በእርሱ አምሳል ስለተፈጠርን፤ የዕቅድ ሰዎች መሆን አለብን። እርግጥ ነው ሁኔታዎችን መለወጥም ሆነ፣ እንደምንፈልገው ሆነው እንዲቆዩ የማድረግ አቅምም ሆነ ችሎታ ስለሌለን፣ በሕይወታችን ለሚሆኑት ነገሮች ሁሉ ዕቅድ ማውጣት አንችልም። ያን የማድረግ ኃይል ያለው ኃያሉ እግዚአብሔር ብቻ ነው። እርሱ የዛሬውን ብቻ ሳይሆን የወደፊቱንም ሁኔታችንን ያውቃል። እንዲሁም በሕይወታችን መሆን የሚገባውን መወሰን፣ ዕቅዳችንን (ፕላናችንን) መለወጥ፤ ማስተካከልና በሌላ አቅጣጫ እንድንሄድ ማድረግ የሚችለው አሁንም እግዚአብሔር ብቻ ነው። እግዚአብሔር ለእኛ የራሱ የሆነ ዕቅድ ያለው መሆኑ ብቻ ሳይሆን፤ በፈለገው ሰዓትና በፈለገው ሁኔታ የሰውንም ዕቅድ የመለወጥ ኃይል ያለው ሲሆን፣ በእርሱ ዕቅድ ላይ ግን ምን ዓይነት ተጽዕኖ ማድረግ የሚችል፣ ኃይልም ሆነ ሥልጣን



ያለው ማንም የለም። እግዚአብሔር የእኛን ዕቅድ በራሱ ዕቅድ ሲለውጥ፤ ብዙ ጊዜ ቅር ቢለንም፤ ከጊዜ በኋላ ግን ለውጡ የሚጎዳን ሳይሆን የሚጠቅመን መሆኑን እንገነዘባለን። የእግዚአብሔርን ዕቅድ ችላ ብለው በራሳቸው ዕቅድ የሚመሩ ሰዎች በኃጢአት ላይ ኃጢአት መጨመራቸው እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ***"ለዐመፀኞች ለሆኑ ልጆች ወዮላቸው! እኔ ባለመታዘዛቸው ዕቅድ መመራት ይፈልጋሉ፤ ከእኔም ፈቃድ ውጪ የቃል ኪዳን ውል በመፈጸም በኃጢአት ላይ ኃጢአት ይጨምራሉ"*** (ኢሳ. 30፥1)።

በብሉይ ኪዳን ዘመን ሙሴ ብቻ ሳይሆን በእርሱ ምትክ የተተካው ኢያሱም የዕቅድ ሰው እንደነበረ እናስታውሳለን። ኢያሱ የዐይን ከተማ ባወጣው የጦርነት ዕቅድ እንዴት እንደደመሰሳት ታሪክ ይመሰክራል (ኢያሱ 10፥1-11)። ኢያሪኮን በያዘበት ወቅት ግን እግዚአብሔር ለኢያሱ ድል እንደሚሰጠው ማረጋገጫ ሰጠው እንጂ፤ (ኢያሱ 6፥2-5) የለውን ዓይነት መመሪያና ዕቅድ አልሰጠውም። በዚህ ዓይነት ኢያሱ ከእግዚአብሔር ግልጽ የሆነ መመሪያ ባላገኘባቸው ወቅቶች ሁሉ፣ የራሱ የሆነውን የጦርነት ዕቅድ ያወጣ እንደ ነበር እናውቃለን። በዕቅድ አወጣጡ በጣም የታወቀው ሌላው መንፈሳዊ መሪ ነህምያ ነው። ነህምያ ተጠንቅቆ ዕቅድ ባያወጣ ኖር የፈራረሰው የኢየሩሳሌም ቅጥር በሃምሣ ሁለት ቀናት ተሠርቶ ባላለቀም ነበር (ነህምያ 6፥15)። ሥራው እንዴት እንደሚሠራ፣ ምን ያህል ጊዜም እንደሚፈጅበት፣ በግንባታው እነማን ተሳታፊ እንደሚሆኑ፣ ግልጽ የሆነ ዕቅድ ነበረው (ነህምያ 4፥5-6)።

"ዕቅድ እያወጣን በእግዚአብሔር ላይ መታመን እንዴት እንችላለን?" ብለው የሚጠይቁ ሰዎች አይጠፉም። የምናወጣው ዕቅድ የእኛን ፍላጎት ለማሟላት ሳይሆን፤ የእግዚአብሔር ፈቃድና ዓላማ ላይ ያተኮረ ከሆነ፣ የምናወጣው ዕቅድ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር ይጋጫል ብለን አንፈራም። የራሳችንን ፍላጎት ችላ ማለት አስፈላጊ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፤ የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሌለበት፣ የምናወጣው ጥሩ ዕቅድ የእግዚአብሔርን አሳብ ማስለወጥ እንደማይችል ማወቅ አለብን። አንዳንድ መንፈሳዊ መሪዎች ዕቅድ ማውጣት የማይፈልጉበት ምክንያት ምን ያሆን? ሰው በተፈጥሮውሽንፈትን እንደሚፈራ የታወቀ ነው። "በዚህ ጊዜ ይህንና ያንን እንሠራለን" ብሎ እንዳሰበው መሥራት ካልቻለ፣ በሕይወቱ ሽንፈት የደረሰበት መስሎ ይሰማዋል። እዚህ ላይ ብዙዎች ያልተገነዘቡት አንድ ነገር ቢኖር፣ ሰው በሕይወቱ አልፎ አልፎ የማይሳካለት ነገር ሊኖር የሚችል መሆኑን ነው። ሽንፈትን የሚፈሩት ከአቅማቸው በላይ የሆነ የኃላፊነት ሸክም ለብቻቸው ለመሸከም በመሞከራቸው ይሆናል። *"ይሄንና ያንን በዚህ ጊዜ ውስጥ እሠራለሁ"* ብለን ዕቅድ ስናወጣ፤ *"ጌታ ሆይ! አንተ ከእኛ የምትጠብቀው ነገር እንዳለ ይገባናል። እንግዲህ ብንሠራው አንተን ደስ ያሰኝሃል ብለን ያሰብነው ይሄ ነው። የሳትነው ነገር ቢኖር ከስህተታችን መልሰን። የምንሠራው ሥራ ልክ ከሆነ፤ ጉልበታችንን አበርታልን"* ማለታችን እንደሆነ እናመን። አንዳንዶች ደግሞ ዕቅድ የማያወጡት፣ "ዕቅድ ካላወጣን ስህተት ውስጥ አንወድ

ቅም" ብለው ስለሚያስቡ ነው። ይሁን እንጂ፣ ይህን ዓይነት አስተሳሰብ ልክ እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ያልተገነዘቡት ነገር ያ አንድ መክሊት ተሰጥቶት ዕቅድ አውጥቶ በተሰጠው መክሊት በመሥራትና ትርፍ በማምጣት ፈንታ፣ ጉድ ጓድ ቆፍሮ እንደ ቀበረው ሰው (የማቴ. 25፥18፥ 24-28) መሆናቸውን ነው። ዕቅድ ማውጣትን የሚቃወሙ ሰዎች መንፈሳዊ ምክንያት ለመስጠት ይሞክሩ እንጂ፥ ዋናው ችግራቸውና ድካማቸው ስንፍና፥ ፍርሃትና እንዲሁም ከምቾታቸው ውጪ ለመውጣት ፈቃደኞች ካለመሆናቸው የተነሳ ብቻ ነው። አንዳንዶቹ ደግሞ ዕቅድ የማያወጡት "መንፈስ ቅዱስ የሚሠራውን ሥራ ለመሥራት የሚሞክሩ፣ መንፈሳዊነት የሌላቸው ናቸው" እንባላለን ብለው በመፍራት ነው። የወደፊቱን ማለብ ወይም ስለ ወደፊቱ ዕቅድ ማውጣት፣ "እግዚአብሔር ብቻ የሚሠራውን ሥራ እኔ ልሥራ" ማለት የሚመስላቸውም አሉ። ዋናው ችግራቸው እግዚአብሔር ሁሉን ማድረግ የሚችል ኃያል አምላክ ይሁን እንጂ ሰው ደግሞ የራሱን ድርሻ የመሥራት ኃላፊነት እንዳለበት ካለመረዳታቸው የመጣ ይመስላል።

## 4.1. ዕቅድ ስናወጣ ክርስቶስን ለመታዘዝ መሆን አለበት

ጌታን አምነን የተቀበልን አማኞች በሙሉ ልባችን ክርስቶስን መውደድ እንዳለብን በቃሉ ታዘናል። ትዕዛዛቱንም የምንጠብቀው ስለምንወደው ነው። ኢየሱስ *"እኔ የአባቴን ትእዛዝ እንደፈጸምሁና በፍቅሩ እንደምኖር፥ እናንተም የእኔን ትእዛዝ ብትፈጽሙ በፍቅሬ ትኖራላችሁ"* ይላል (የዮሐ. 15፥10)። ክርስቶስን የምንታዘዝበት ምክንያት እግዚአብሔር አምላካችንን በፍጹም ልባችን፥ በፍጹም ነፍሳችን፥ በፍጹም ኃይላችን፥ እንዲሁም ሰውን ሁሉ እንደ ራሳችን አድርገን ስለምንወድ ነው (የማቴ. 22፥36-40)። ስለዚህ የምናወጣው ዕቅድ እግዚአብሔርንና እንዲሁም እርስ በርሳችን የበለጠ እንድንዋደድ እንዲያደርገን መሆን አለበት። ዕቅዳችን ይህን ዓይነት ውጤት ከሌለው፥ በወረቀት ተጽፎ ሲታይ ምንም ያህል ጥሩ ቢሆን፥ ዋጋ የለውም። የምናወጣው ዕቅድ የአማኞችን መንፈሳዊ ሕይወት በማሳደግ ፈንታ፥ ራሳችንን ለከፍተኛ ሹመት ለማብቃት መሆን የለበትም። የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ እንድንጠብቅ የማያደርገን ማንኛውም ዕቅድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም። ዕቅዳችን በክርስቲያኖች መካከል ያለውን ግንኙነት ለማጠናከር እንጂ በሌሎች ላይ ሸክም ለማብዛት መሆን የለበትም። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የምናወጣው ዕቅድ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሌሎችን ወደ ክርስቶስ የሚያቀርብ ወይም የሚያመጣ መሆን አለበት። ዕቅዳችን ሁሉ የማያምኑትን ሰዎች በቀጥታ ወደ ክርስቶስ ላያመጣ ይችላል። ይሁን እንጂ፥ ዕቅዳችን ሁሉ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ለወንጌል ዕድገት መሆን አለበት። ይኸውም፥ ያመኑትን ጥሩ የክርስቶስ አምባሳደር እንዲሆኑ ለማደራጀት፥ ወይም ክርስቶስን ጥልቀት ባለው መልክና ሁኔታ እንዲያመልኩት፥ ወይም እውነትን ለሌሎች ማስተማር እንዲችሉ ለማዘጋጀት ሊሆን ይችላል።



## 4.2. ዕቅድ ስናወጣ በትህትና መንፈስ መሆን አለበት

ዕቅድ ለማውጣት የምንፈራበት ምክንያት ምን ይሆን? ዋናውና ትልቁ ምክንያታችን፥ እግዚአብሔር የሚፈቅደውን በማድረግ ፈንታ፥ እኛ የምንፈልገውን ነገር ለመሥራት እናቅድ ይሆናል ብለን በመፍራት ይሆናል። ይሄ ነገር በእርግጥ ሊያሳስበን ይገባል። ዕቅድ የምናወጣው የራሳችንን ፈቃድና ፍላጎት ለመፈጸም እንዳይሆን መጠንቀቅ አለብን። ይሁን እንጂ "ዕቅድ አላወጣም" ማለቱ ብቻ ችግሩን አይፈታውም። የራስን ፈቃድ የመፈጸም ፍላጎት፥ ዕቅድ ባናወጣም በውሳኔ አሰጣጣችን ውስጥ ሊኖር ይችላል። ችግሩ ያለው እኛው ራሳችን ላይ እንጂ ዕቅድ ማውጣቱ ላይ እንዳልሆነ ማወቅ ይገባናል። ስለዚህ በራሳችን ዕቅድ ሳንተማመን፣ በእግዚአብሔር ፊት በትህትና መንፈንስ ተሞልተን፣ አስፈላጊውን ዕቅድ ልናውጣ ይገባል። በጸሎት መንፈስ ሆነን ዕቅድ ስናወጣ፥ ዕቅዳችንን በትህትና መንፈስ ለማውጣት እርምጃ መውሰዳችን እንደሆነ ማወቅ አለብን። ዕቅዳችንን በትህትና መንፈስ ስናወጣ፥ እግዚአብሔር ከሚፈልገው ውጪ ምንም ነገር ሳለማድረግ፥ ሁሉን ነገር እርሱ እንደሚፈልገው ብቻ ለማድረግ መወሰናችን ነው። በትህትና መንፈስ ስንሞላ፥ "እኔ" ባይነታችንን በእግዚአብሔር ፊት ጥለን፥ የራሳችንን ክብር በመፈለግ ፈንታ ክብር ለሚገባው ጌታ ብቻ አስፈላጊውን ክብር እንሰጣለን። አንዳንድ ጊዜ የራሳችንን ፍላጎት ከእግዚአብሔር ፍላጎት ጋር በመደባለቅ ግራ የምንጋባበት ጊዜ አለ። ዕቅዳችንን በትህትና መንፈስ የማናወጣ ከሆነ፣ የምናወጣው ዕቅድ ለእግዚአብሔር ክብር ብቻ እንዲሆን ሳይሆን ለራሳችን መታወቂያን ክብር ልናውለው እንችላለን።

እናስተውለው እንጂ፥ በልባችን ውስጥ የሚኖረው ፍርሃት፣ እርምጃችንን ወደ ኋላ የሚጎትትበት ጊዜ አለ። በቤተ ክርስቲያናችን ኃይለኛ ወይም አስቸጋሪ ሰው ነው ብለን የምናስበውን ሰው በመፍራት ዕቅድ አውጥተን ውሳኔ ለመውሰድ እንፈራለን። ፍርሃታችንም ሌላ ነገር ሳይሆን፣ "እኛነታችንን" (ego) እንዳይነካ ነው። "ይሄ የማወጣው ዕቅድ የተፈለገውን ዓይነት ውጤት ያላስገኘ እንደሆን ሰዎች ምን ይሉኛል?" የሚለው ፍርሃታችን፣ አሁንም ራሳችንን ለመጠበቅ ሰንል የምናስበው አሳብ ነው። ስለዚህ ዕቅድ ስናወጣ በእግዚአብሔር ፊት ራሳችንን ዝቅ አድርገን መቅረብ አለብን። ዕቅድ ለማውጣት የምናደርገው ተገቢ የሆነ ዝግጅት፥ የራሳችንን ልብ በጥንቃቄ መመርመር የሚያስፈልገን፣ አንደኛውና ትልቁ ሥራችን መሆን አለበት። ዕቅድ የምናወጣው ለራሳችን ስምና ክብር ለመጨመር ከሆነ፥ ምክንያታችን ትክክል አይደለም። ይሁን እንጂ፥ ጳውሎስ *"እኔ እንደ ማውቀው ከሆነ ኀሊናዬ አይወቅሰኝም፤ ይህም እኔ ንጹሕ መሆኔን አያስረዳም፤ ነገር ግን በእኔ ላይ የሚፈርድ ጌታ ኢየሱስ ብቻ ነው"* (1 ቆሮ. 4፥4) እንዳለው፣ ሙሉ በሙሉ እርግጠኞች አንሆንም ይሆናል። የሆነ ሆኖ ለራሳችን ክብር ሰንል እንዳናገለግል የሚገባውን ሁሉ ጥንቃቄ ማድረግ አለብን። ጳውሎስ *"...ሥጋንና መንፈስን ከሚያረክስ ከማና*

*ቸውም ነገር ራሳችንን እናንጻ፤ እግዚአብሔርንም በመፍራት ቅድስናችን ፍጹም እንዲሆን እናድርግ"* (2 ቆሮ. 7፥1) ይላል።

## 4.3. ዕቅድ ስናወጣ በጸሎት መንፈስ መሆን አለበት

ዕቅድ ለማውጣት ጸሎትን በጣም ከተጠቀሙበት መንፈሳዊ መሪዎች መካከል አንደኛው ነህምያ እንደሆነ ቀደም ሲል ተመልክተናል። ነህምያ የፈረሰውን የኢየሩሳሌምን ቅጥር መልሶ ስመገንባት እስቦ ከተነሳበት፣ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ድረስ ለጸሎት ቅድሚያ ይሰጥ እንደነበረ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ይናገራል። ነህምያ የኢየሩሳሌም ቅጥር መፈራረሷን እንዳወቀ፣ ወደ እግዚአብሔር መጮኽ ጀመረ። *"ይህን ነገር በሰማሁ ጊዜ ተቀምጬ አለቀስሁ፤ በሰማይ አምላክ ፊት አያሌ ቀናት አዘንሁ፤ ጾምሁ፤ ጸለይሁም"* ይላል (ነህምያ 1፥4)። ግንባታው ተጀምሮ እስካለቀበት ጊዜ ድረስ ነህምያ ጸሎትን እንደሚገባው የተጠቀመበት ሰው ነው። ነህምያ የዕቅድ ሰው እንደሆነ፣ ዕቅዱም በጸሎት የተደገፈ መሆኑን፣ (ነህምያ 2፥4) እናውቃለን። ነህምያ ጥያቄውን ለንጉሡ ከማቅረቡ በፊት እጠቃላይ የሆነ ዕቅድ እንደነበረው የምንረዳው፣ ፕሮጀክቱ ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድበት ንጉሡ ለጠየቀው ጥያቄ የሰጠውን መልስ ስንሰማ ነው። *"...ንጉሡ ንግሥቲቱም ጥያቄዬን በመቀበል ጉዞህ ምን ያህል ጊዜ ይወስድብሃል? እስከ መቼስ ትመለሳለህ? ብሎ ጠየቀኝ። እኔም የሚወስድብኝን ጊዜና መቼ እንደምመለስ ነገርሁት"* (ነህምያ 2፥6) ይላል። ነህምያ የተነሳበትን ዓላማ ለመፈጸም በመንገዱ ላይ የተለያዩ ዕንቅፋቶች ሲያጋጥሙት የሚጸልይ መሆኑ ብቻ ሳይሆን በዕቅድ እወጣጣቸው ሊደነቁ ከሚገባቸው መንፈሳዊ መሪዎች መካከል፣ አንዱ መሆኑ ነው። ሌላው በዕቅዱ ውስጥ ጸሎትን የተጠቀመ ሰው ሐዋርያው ጳውሎስ ነው። ለወንጌል ስርጭት ያወጣቸው ዕቅዶች ሁሉ በጸሎት የተደገፉ ናቸው። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ስማወቅ ሲጾምና ሲጸልይ፣ መንፈስ ቅዱስ *"እኔ ለመረጥኋቸው ሥራ በርናባስንና ሳውልን ለዩልኝ"* (የሐዋ. 13፥2) እንዳለ እናስታውሳለን። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መንፈሳዊ መሪዎች፣ እግዚአብሔር የሰጣቸውን ራዕይ ለመፈጸም ሲነሱ፣ ያለጸሎት ዕቅድ ያወጡበት ጊዜ የለም። ስለ ዚህ፣ እኛም አገልግሎታችንን ለመፈጸም ለምናወጣው ዕቅድ እግዚአብሔር ትክክለኛ መመሪያውንና ጥበቡን እንዲሰጠን መጸለይ አለብን። ዕቅድ ከማውጣታችን በፊት፥ ዕቅድ እያወጣንም፥ ያወጣነውንም ዕቅድ በሥራ ላይ በምናውልበት ጊዜና እንዲሁም የወሰድነውን እርምጃ በምንመዝንበት ጊዜ ሁሉ፣ እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ እንዲሠራ በጸሎት መጠየቅ አለብን። የምንፈልገውን ዓይነት ውጤት ማግኘት እንድንችል መጸለያችን፣ አስፈላጊውን ዕቅድ እንዳናወጣ የሚከለክለን እንዳልሆነ ማወቅ አለብን። መጸለይ ብቻ ሳይሆን ባወጣነው ዕቅድ መሠረት እግዚአብሔር ወደሚቀጥለው ደረጃ እስኪያደርሰን ድረስ እርሱን በትዕግሥት መጠበቅ አስብን።



## 5. የዕቅድ አወጣጥ "ሂደት" (Planning Process)

መንፈሳዊ መሪ ጥሩ ዕቅድ ለማውጣት የሚፈልግበት ዋናውን ተቀዳሚ ዓላማው፣ ስሚያደርገው ነገር ሁሉ እግዚአብሔርን ለማክበር መሆን አለበት። ሐዋርያው ጳውሎስ *"እንግዲህ ስትበሉም ሆነ ስትጠጡ ወይም ማናቸውንም ነገር ስታደርጉ፥ ሁሉንም ነገር ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉ"* (1 ቆሮ. 10፥31) ሲል ይመክረናል። ጥሩ ዕቅድ የሚፈልቀው ሕይወቱን ለእግዚአብሔር ክብር ከሰጠ ሰው በመሆኑ፣ መንፈሳዊ መሪ የሚሠራውን ነገር ጥሩ አድርጎ ለመሥራት፣ እንዲሁም ብዙዎችን ወደ ክርስቶስ መሳብ እንዲችል በቅድሚያ ራሱን ሙሉ በሙሉ ለጌታ የሰጠ መሆን አለበት። መንፈሳዊ መሪ (መጋቢ) ምኞቱ በዓስም የሚደነቅ እጅግ በጣም ትልቅ ቤተ ክርስቲያን ለመሥራት፥ ዝነኛ የሆነ ሰባኪና አስተማሪ ለመሆን ከሆነ፥ ዕቅድ የሚያወጣው የራሱን ፍላጎት ለመፈጸም እንጂ፥ ለእግዚአብሔር ክብር እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ጥሩ ዕቅድ፣ *'ዓላማ፥ (purpose) ግብና (goal) 'ቅደም ተከተልን' (priority)* ያካተተ ነው። መንፈሳዊ መሪዎች እብዛኛዎቹ ተመሳሳይ የሆነ ዋና ዓላማ ይኑራቸው እንጂ የሁሉም ዕቅድ እወጣጥ፣ የሚከተሉት ቅደም ተከተል አንድ ዓይነት ይሆናል ማለት እይደለም።

ስለ ዕቅድ እወጣጥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የመጀመሪያውን ትምህርት የምናገኘው፣ በአመራር ችሎታው በጣም ተደናቂ ከሆነው ከዮሴፍ ነው። ዮሴፍ በሕይወቱ የገጠሙት ነገሮች ጥሩም ባይሆኑ፣ በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ እልፎ እንዴት የግብጽ ጠቅላይ ሚኒስቴር መሆን እንደቻለ እናውቃለን። በጲጢፋር ቤት ውስጥ ጥሩ ጅማሬ እግኝቶ የተመቻቸ ኑሮ በመኖር ላይ እያለ ባልጠበቀውና ይሆናል ብሎ ባላሰበው ሁኔታ ወህኒ ቤት ተጣለ። ዮሴፍ በሕይወቱ የጎላ ነገር ሳይሰራ ለረጅም ጊዜ ወህኒ ቤት እንዳሳለፈ ታሪኩ ይመሰክራል። ይሁን እንጂ፣ ወህኒ ቤት በቆየበት ዘመን ነው ዮሴፍ የትኛውም ዩኒቨርሲቲ ቢገባ ሊያገኘው የማይችለውን፣ ከፍተኛን ጠቃሚ የሆነ የአስተዳደር ዕውቀትና ጥበብ የቀሰመው። በዚህም ውስጥ የእግዚአብሔር ዕቅድ እንደነበረበት ግልጽ ነው። ታላላቅ መንፈሳዊ መሪዎች ለተጠሩበት አገልግሎት ብቃት እንዲኖራቸው እግዚእብሔር በተለያየ ሁኔታ የመሪነት ሥልጠናን ይሰጣቸው እንደ ነበር እናውቃስን። ጥሩ ዕቅድ እውጪ ለመሆን ጥሩ ልምምድ አስፈላጊ ነው። ዮሲፍ ይህን ልምምዱን ያገኘው በወህኒ ቤት ውስጥ ሆኖ ነው። *"ስለዚህ የወህኒ ቤት አዛዥ የዮሴፍን የእስረኞች ሁሉ አለቃ አደረገው፤ በእስር ቤቱ ላለውም ነገር ሁሉ ኃላፊ ሆነ። እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር ሆኖ ሥራውን ሁሉ ያሳካለት ስለ ነበር የወህኒ ቤት አዛዥ በዮሴፍ ኃላፊነት ሥር ስላለው ስለማንኛውም ጉዳይ ሐሳብ አይገባውም ነበር"* (ዘፍ. 39፥22-23)። ሙሴም በፈርዖን ቤተ መንግሥት ሆኖ ያልተማረውን ትምህርት እንዲቀስም፣ እግዚአብሔር ወደ ምድያም በረሃ እንደላከው እናውቃለን (ዘጸ. 2፥15)። ዮሴፍ ጥሩ መሪ ሊኖረው የሚገባ ባሕሪ

ዎች ይኸውም ትዕግሥት፣ የመንፈስ እርካታና ብስለት የነበረው ሰው ነበር። ከዚህ ሁሉ በላይ እግዚአብሔር የጥበብን ስጦታ የሰጠው ሰው ነበር።

ዮሴፍ እግዚአብሔር ለፈርኦን የሰጠውን መልዕክት ይኸውም፣ ስለ ሰባቱ የጥጋብ ዓመታትና እንዲሁም ስለ ሰባቱ የረሀብ ዓመታት ከነገረው በኋላ፣ በጥጋቡ ዘመን ምን ዓይነት ዝግጅት ማድረግ እንደሚገባው ለፈርኦን ምክር ሲሰጠው፣ *"እንግዲህ ፈርዖን ብልኅና አስተዋይ ሰው ፈልጎ፣ በመላው የግብፅ ምድር ላይ አሁኑኑ ይሹም"* አለው (ዘፍ. 41፥33)። ፈርኦንም በመደነቅ ዮሴፍን ካዳመጠው በኋላ፣ *"እግዚአብሔር ይህን ሁሉ ስለ ገለጠልህ እንዳንተ ያለ አስተዋይና ብልኅ ሰው የለም"* (ዘፍ. 41፥39) በማለት ዮሴፍን ወዲያው ሾመው። ዮሴፍ ኃላፊነቱን ተቀብሎ ያወጣው ዕቅድ ፈርዖንን ብቻ ሳይሆን ግብጽንና በግብጽ ዙሪያ የሚኖሩት ሕዝቦች ከረሀብ እንዳዳነ ታሪኩን እናውቃለን። አስፈላጊውን ዕቅድ ማውጣት የሚያስፈልገው ጥንት፣ ወይም በብሉይ ኪዳን ዘመን ብቻ ሳይሆን፣ ዛሬም ያስፈልጋል። በዘመናችን ባለችውም የክርስቶስ አካል በሆነችው ቤተ ክርስቲያንም ጤናማ ሆና አገልግሎቷን መፈጸም እንድትችል፣ ዮሴፍን የመሰሰሉ የማስተዳደር ስጦታ፣ ያላቸው መሪዎች ያስፈልጓታል። የኢጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎቷን እንደሚገባው ለመፈጸም እንድትችል ጥሩ ዕቅድ ማውጣት አስፈላጊ እንደሆነ ተወልክተናል። ጥሩ ዕቅድ ለማውጣትም መሠረታዊ ዓላማዋንና ግቦቿን በቅድሚያ ማወቅ ያስፈልጋል።

## 5.1. የኢጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ ዓላማ ምንድነው?

ኢጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሦስት መሠረታዊ የሆኑ ዓላማዎች አሏት። ይኸውም፥

*1ኛ) የወንጌል ስበካ፥ (Evangelism)*

*2ኛ) አማኞችን ማነጽ (ማሳደግ)፥ (Edification)*

*3ኛ) ቤተ ክርስቲያንን ማስፋፋት (ማሳደግ) (Expansion) ነው።*

እነዚህ ሦስት ዓላማዎች ምን እንደሆኑ በደንብ መታወቅ አለባቸው። በአሁኑ ወቅት እነዚህን ሦስት መሠረታዊ ዓላማዎችን በደንብ የተረዱ ስንቶቹ እንደሆኑ አናውቅም። ይሁን እንጂ ማንኛውም የኢጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ መሪ፣ ቤተ ክርስቲያኒቱ አገልግሎቷ በምን ዓላማ ላይ የተመሠረተ እንደሆነ ራሱም ሆነ የሚመራው ምዕመን በግልጽ ማወቅ አለበት።

(1) *ቤተ ክርስቲያን ከምትሰጣቸው አገልግሎቶች ውስጥ አንደኛው ወንጌልን ላልሰሙት ማሰማት፥ ጌታን ለማያውቁት ማሳወቅ ነው።* አንዳንድ ኢጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ከዓላማቸው ውስጥ ይህንን የማይጨምር ይመስላል። አዳዲስ ነፍሳት እንዲድኑ ጥረት በማድረግ ፈንታ በተለያየ መንገድ አማኞችን ስበው በማምጣት የቤተ



ክርስቲያናቸው አባል ለማድረግ ጥረት ሲያደርጉ ይታያሉ። ሆን ብለው ባያደርጉትም፥ የሙዚቃቸው ዘመናዊነት፥ የቤተ ክርስቲያናቸው ትልቅነት፥ ሌላው ቀርቶ የመቀመጫዎቻቸው ማማርና ምቾት ብዙዎችን ወደ እነርሱ ቤተ ክርስቲያን የመሳብ ኃይል አለው። በዚህ ረክተው ከተቀመጡ፥ ወይም ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት አያኮረፉ የሚወጡትን የሚያስተናግዱ፥ ወይም የሚሰቡ ከሆነ፥ ቤተ ክርስቲያናቸው ከተጠራችበት ምክንያት አንደኛውን ችላ ማለቷ እንደሆነ ሊገነዘቡት ይገባል። ከዓላማቸው አንደኛው ወንጌል ላልደረሳቸው ወንጌልን ማዳረስ ከሆነ፥ ምን ያህል አዳዲስ ነፍሳት ድነው ወደ ቤተ ክርስቲያናቸው እንደተጨመሩ ራሳቸውን መጠየቅ አለባቸው። በተለይ አሜሪካ ውስጥ አንዳንድ ቤተ ክርስቲያናት ወንጌልን ሰብከው ነፍሳት እንዲጨመሩ በማድረግ ፈንታ፥ ከሌሎች ስቴቶች ሰዎች እንዲመጡ፥ ሥራ ፈልጎ በማስያዝ፥ ቤት አዘጋጅቶ በመጠበቅ የቤተ ክርስቲያን አባሎቻቸውን ቁጥር ለማሳደግ የሚሞክሩ እንዳሉ እናውቃለን። ሌሎች ደግሞ "የቪዛ ሎተሪ" የደረሳቸውን ክርስቲያኖች ስዖንሰር በመፈለግ፥ እነርሱ ወዳሉበት አስቴት እንዲመጡ በማድረግ ቁጥራቸውን የሚጨምሩ አሉ። በተለይ አሜሪካን አገር ወንጌል ተሰብኮላቸው የዳኑት ምን ያህል እንደሆኑ ብንመረምር ምናልባት ከመቶ አንድ (1%) ይሆናል ብንል የተሳሳትን አንሆንም። የተቀሩት ከሌላ ሥፍራ ድነው የመጡ ናቸው። ከላይ የገለጽነውን ዓይነት ለሰዎች በጎ ነገር ለሰዎች ማድረግ ወይም ሰዎችን መርዳት መጥፎ ነው ማለታችን ሳይሆን፥ በወንጌል ሰበካቸው አዳዲስ ነፍሳት ድነው ወደ ቤተ ክርስቲያን ሕብረት እንዲጨመሩ የሚያደርጉት ጥርት ችላ እንዳይባል ለማሳሰብ ብቻ ነው። ቤተ ክርስቲያን ከዓላማዋ አንዱ የወንጌል ሥርጭት (Evangelism) ከሆነ፥ በዚህ አቅጣጫ ከፍተኛ ትጋት ማሳየት አለባት።

(2) *ቤተ ክርስቲያን ከምትሰጠው አገልግሎቶች ሁለተኛው፣ አማኞችን ማነጽ (ማሳደግ) ነው።* ቤተ ክርስቲያን አማኞቿን ጤናማ የሆነ መንፈሳዊ ምግብ እየመገበች ማሳደግ አለባት። እዚህ ላይ የአማኞችን ቁጥር ማብዛት ሳይሆን፥ የአማኞችን መንፈሳዊ ብስለት የሚመለከት ነው። ዕድገት ስንል፥ ምን ያህል ዘመን ክርስቲያን እንደሆኑ ማወቅ አይደለም። ክርስቲያን ከሆኑ ብዙ ዓመት ቢሆናቸውም ገና ያላደጉ አማኞች ቁጥራቸው ጥቂት አይደለም። የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ይህን ዓይነት ችግር ነበረባት። በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ በግልጽ ይታይ ነበር። አማኞቹ አብዛኛዎቹ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ነበራቸው። ይሁን እንጂ፥ እውነተኛ የሆነ መንፈሳዊ ዕድገት በሕይወታቸው አይታይም ነበር። ለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ እያዘነ፥ *"ወንድሞች ሆይ! በክርስቶስ ገና ሕፃናት እንደ መሆናችሁ እንደ ሥጋውያን እንጂ እንደ መንፈሳውያን ልናገራችሁ አልቻልሁም። ገና ስላልጠነከራችሁ ወተት እንጂ ጠንካራ ምግብ አልመገብ*

*ጓችሁም፤ አሁንም ቢሆን ገና ናችሁ። አሁንም ሥጋውያን ናችሁ...*"(1 ቆሮ. 3፥1-3) ይላቸዋል። አስማደጋቸውን የሚያሳዩ ብዙ ምልክቶችን አይቷል፥

- <u>*በመካከላቸው መለያየት ነበር*</u>። "*...መለያየት በመካከላችሁ አይኑር፤ ሁላችሁም ተስማምታችሁ በአንድ አሳብና በአንድ ዓላማ ጸንታችሁ ኑሩ*" (1 ቆሮ. 1፥10)።
- <u>*ትምክህተኞች ነበሩ*</u>። "*የሚመካ በእግዚአብሔር ይመካ*" (1 ቆሮ. 1፥31)።
- <u>*ሥጋውያን ነበሩ*</u>። "*...እርስ በርሳችሁ ስስምትቀናኑና ስለምትከራከሩ ሥጋውያን መሆናችሁ አይደለምን? የእግዚአብሔር ሰዎች መሆናችሁ ቀርቶ የዓለም ሰዎች መሆናችሁ አይደለምን?*" (1 ቆሮ. 3፥3)።
- <u>*የቅድስና ሕይወት አይኖሩም ነበር*</u>። "*በመካከላችሁ አሳፋሪ የዝሙት ሥራ መኖሩ ይወራል፤ እንዲህ ዐይነቱ የዝሙት ሥራ በአረማውያን ዘንድ እንኳ የማይደረግ ነበር፤ ይኸውም የእንጀራ እናቱን እንደ ሚስት አድርጎ የሚኖር አለ ተብሎአል*" (1 ቆሮ. 5፥1)።
- <u>*የአሉባልታ ወሬ በመካከላቸው ነበር*</u>። "*...የእግዚአብሔር መንግሥት የወሬ ጉዳይ ሳይሆን የእግዚአብሔር ኃይል ነው*" (1 ቆሮ. 4፥20)።

በአሁኑ ጊዜ እጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ምዕመናኖቻቸውን ለማነጽ ወይም ለማሳደግ የሚያደርጉት ጥረት ምን ዓይነት ይሆን? የቤተ ክርስቲያን አንደኛው ዓላማዋ ክርስቲያኖችን ማነጽ ወይም ማሳደግ ከሆነ፥ የቤተ ክርስቲያን መጋቢ ጠቃሚ ትምህርቶችን በየጊዜው መስጠት አለበት። በዚህ አቅጣጫ ያስባቸውን ድካም ስመሸፈን አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት በዓመት ብዙ ኮንፍራንሶችን ያዘጋጃሉ። ከውጪ ተጋብዞ የሚመጣው ሰባኪ ሕዝቡ ምን ዓይነት መንፈሳዊ ምግብ እንደሚያስፈልገው ስለማያውቅ፥ ስሜታቸውን ቀስቅሶ ትንሽ ሞቅ አድርጓቸው ይሄዳል። ኮንፍራንሱ ሲያልቅ፥ ቀድሞ ወደነበሩበት መንፈሳዊ ደረጃ ይመለሳሉ።

*(3) ቤተ ክርስቲያን ከምትሰጠው አገልግሎቶች ውስጥ ሦስተኛው፤ ቤተ ክርስቲያንን ማስፋፋት (ማሳደግ) ነው።* አዳዲስ ነፍሳት ሲድኑና ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲጨመሩ፥ አገልግሎት ይሰፋል፤ የማምለኪያ ሥፍራ ይጠባል። አንዳንድ የአገልግሎት ጥሪ ያላቸው የሚመስሉትን አማኞች፣ አስፈላጊውን ዝግጅት እንዲያደርጉ ዕርዳታ ከሰጡ በኋላ፣ ወደ ሌላ ሥፍራ ሄደው ቤተ ክርስቲያን እንዲተክሉ፣ ቤተ ክርስቲያን ማደፋፈር አለባት። ራዕይ ያላቸው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች፥ በዕድገት ምክንያት የሚከሰቱትን አንዳንድ ችግሮች ቢፈጠሩ፣ ችግሩን ስመፍታት፣ የምዕመናኑን አንድነት ስመጠበቅ የተስያየ ዕቅድ ማውጣት አለባቸው።



## 5.2. የቤተ ክርስቲያን ግቢ (Goal) ምንድነው?

"ግብ" የወደፊቱን (የረጅም ጊዜ) ሁኔታ የሚያሳይ ወይም የሚገልጽ ስዕል እንደ ሆነ ቀደም ሲል ገልጸናል። *"ግብ"፥ ቤተ ክርስቲያን ያላትን "ዓላማ" የምትፈጽምበትና የምትለካበት ነው።* አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከሚታይባቸው ድካሞች አንደኛው ስግል ሕይወታቸውም ሆነ ስቤተ ክርስቲያናቸው ምንም ዓይነት ግብ የሌላቸው መሆናቸው ነው። *የቤተ ክርስቲያኒቱ "ዓላማ" የሚለዋወጥ ሳይሆን ሁልጊዜ አንድ ዓይነት ሲሆን "ግብ" ግን በየጊዜው ሊለዋወጥ ይችላል።* "ግብ" ያደረግነው፥ ወይም "ሥርተን ስመጨረስ የወሰንነው፥ እንዲህ ዓይነት ውጤት ስማምጣት ነው" የሚል፤ ሊለካ የሚችል "ግብ" ማበጀት፣ ስቤተ ክርስቲያን ዕድገት ጠቃሚ ነው። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ስግል ሕይወታቸውም ሆነ ስሚመሩት ቤተ ክርስቲያን ግብ ሊኖራቸው ይገባል። ስምሳሌ አንድ የቤተ ክርስቲያን መጋቢ፥ *"በዚህ ጊዜ ውስጥ ይህን ያህል መጽሐፍ አነባለሁ... ስቤተ ክርስቲያን መጋቢዎች በሚዘጋጀው ቤሚናር አካፈላለሁ... ሕዝቡን ለማስተማር የሚረዳኝን በመጽሐፍ መልክ አዘጋጅቼ አወጣለሁ..."* ቢል፤ እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉት የግል የሆኑ "ግቦቹ" ናቸው። እነዚህ ከላይ የዘረዘርናቸው የመጋቢው የግል "ግቦች" ቢሆንም፥ በሌላ በኩል ስቤተ ክርስቲያኒቱ ዕድገት ጠቃሚነት ያላቸው ናቸው። የቤተ ክርስቲያን "ግብ" ደግሞ፥ የቤተ ክርስቲያኒቷን ዕድገት የሚመለከት ነው። ቤተ ክርስቲያኒቱ ያወጣችው "ግብ" ካለ፥ በዚያ አማካኝነት ካወጣችው ግብ ውስጥ ምን ያህሉቹን እንደፈጸመቻቸው መስካት ወይም መመዘን ይቻላል። እንዲሁም ካወጣቻቸው ግቦች መድረስ ካቃታት፣ ችግሯ ምን እንደሆነ በቀላሉ ማወቅ ይቻላል።

እነዚህ ከላይ የዘረዘርናቸው የቤተ ክርስቲያኒቱ "ግቦች" ከሆኑ፥ እነዚህን ግቦች ተፈጽመው ስማየት ልዩ ልዩ ፕሮግራሞችን የቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢ ዕቅድ ማውጣት አለበት። አዳዲስ ነፍሳት የሚድኑትን ቁጥር ስመጨመር፥ የምስክርነት ጓድ፥ ጌታን የማያውቁት ሰዎች ስመድረስ ልዩ ልዩ ፕሮግራሞች ማዘጋጀት አለበት። እንዲሁም አማኞች የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎቻቸውን አውቀው በልዩ ልዩ አገልግሎት ውስጥ እየገቡ እንዲያገስግሉ ማስተማርና ማነቃቃት አለበት። በዓመቱ መጨረሻ፥ ካቀዱት ውስጥ ምን ያህሉን እንዳቀዱት መፈጸማቸውን መመርመር አለባቸው።

## 5.3. የቤተ ክርስቲያን ቅደም ተከተል (Priority) ምንድነው?

መሪዎች፥ በአመራራቸው ጥሩ ውጤት ስማግኘት፥ ስሚያደርጉት ነገር ቅደም ተከተል ሊኖራቸው ይገባል። የሚከተሉት (የሚያወጡት) ቅደም ተከተል፥ የሚሠሩት ሥራ የትኛው መቅደም፥ የትኛው መከተል እንዳስበት ይወስናል። ሥራዎቹ መቼና

እንዲሁም ለምን መሠራት እንዳለበት ይገልጸል። መሪ ካቀደው ግብ ለመድረስ ወዲያው መሠራት ያለባቸው አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች የትኞቹ እንደሆኑ፥ የትኞቹ መከተል እንዳለባቸው ይወስናል። እንዳንድ መሪዎች አንዳንድ ጊዜ ሊደርሱበት የሚፈልጉት ብዙ "ግቦች" ይኖራቸዋል። ለዚህ ነው የግድ "ቅደም ተከተል" ማውጣት ያለባቸው። "የመሥራት ሱስ" ያለባቸው መሪዎች፥ ለራሳቸውም ሆነ አብረዋቸው ለሚሠሩት ብዙ "ግቦችን" የማውጣት ዝንባሌ አላቸው። አልፎ አልፎ ከሰው አቅም በላይ የሆነ ሥራ እንዲሠራ ከሌሎችም ሆነ ከራሳቸው ይጠብቃሉ። "ቅደም ተከተል" ለማውጣት፥ መሪው ሊፈጽማቸው ያሰባቸውን ሥራዎች ወይም አገልግሎቶችን በሦስት መክፈሉ፥ ይኸውም *1ኛ፥ በጣም አስፈላጊ የሆኑ፥ 2ኛ፥ በመካከለኛ ደረጃ አስፈላጊ የሆኑ፥ እንዲሁም 3ኛ፥ በጣም አስፈላጊ ያልሆኑ ነገሮች በማለት መከፋፈል ይጠቅማል።* ቀጥሎ እነዚህ ሥራዎች መቼ ተሠርተው ማለቅ እንዳለባቸው የጊዜ ገደብ መወሰን አስፈላጊ ነው። ቀጥሎ ሥራዎቹ ተጠናቅቀው ለማለቅ ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድ መተመን ያስፈልጋል። በዚህ ዓይነት በጣም አስፈላጊ ናቸው ከሚባሉት ጀምሮ ሥራዎቹን መሥራት ነው። መሪ በሚያወጣው ቅደም ተከተል ስመጠቀም፥ በጣም አስፈላጊ ወይም በቅድሚያ መሠራት ያለባቸው ሥራዎችን፥ በሌላ ጊዜ ሊሠሩ የሚችሉትን ሥራዎች ለይቶ ማወቅ አለበት። ቅድሚያ ሰጥቶት ሥራውን በመሥራት ላይ እያለ፥ ሌላ አዲስ ነገር ቢያጋጥመው፥ ያጋጠመው አዲስ ነገር "ምን ያህል አስፈላጊና አስቸኳይ ነው? በሌላ ጊዜ ሊሠራ ይችላል ወይ?" ብሎ ራሱን መጠየቅና መወሰን አለበት።

## 5.4. የዕቅድ ዓይነቶች

አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሦስት ዓይነት "ዕቅዶች" እንዳሏት የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ምሁራን ይገልጻሉ።[39] ሦስቱም ዓይነቶች ዕቅዶች አስፈላጊ የሆኑበት ዋና ምክንያት ቤተ ክርስቲያን ለመፈጸም ያሰበችውን ዓላማ ለማሳካት ነው።

### 1ኛ/ "የአጭር ጊዜ ዕቅድ" (Short-Range Planning)

"የአጭር ጊዜ ዕቅድ" የሚታቀድበት ምክንያት፣ "የረጅም ጊዜ ዕቅድን" ስኬታማ ለማድረግ ነው። "የአጭር ጊዜ ዕቅድ" ከአንድ እስከ ሦስት ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ ሊሠራ የታሰበውን ዓላማ ለመፈጸም ነው። ለምሳሌ፥

*(1) በዚህ ዓመት... ነፍሳት ድነው ወደ ቤተ ክርስቲያናችን እንዲጨመሩ፥*

*(2) በዚህ ዓመት ከቤተ ክርስቲያን አባላት... አማኞች በልዩ ልዩ አገልግሎት እንዲሳተፉ ማድረግ፥*

[39] Charles H. Morris.



*(3) በዚህ ዓመት... አዳዲስ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች እንዲቋቋሙ ማድረግ፥*

*(4) በዚህ ዓመት ጥሩ የሕጻናት የሰንበት ትምህርት ማቀናጀት፥*

### 2ኛ/ "የረጅም ጊዜ "ዕቅድ" (Long-Range Planning)

የረጅም ጊዜ ዕቅድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ያልጠበቁት ሁኔታ ደርሶ ከመደናገጥ ይልቅ፥ አስቀድመው እንዲዘጋጁ ያደርጋቸዋል። የአምስት ወይም የአሥር ዓመት ዕቅድ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ፥

(1) ስቤተ ክርስቲያኒቱ ... የሙሉ ጊዜ አገልጋይ መቅጠር፥

(2) ቤተ ክርስቲያን በሌለበት ሥፍራ፥ ከቤተ ክርስቲያን አባላት መካከል ጥሪ ያለውን ሰው በመላክ አዲስ ቤተ ክርስቲያንን መትከል።

"የረጅም ጊዜ ዕቅድ ትዕግሥትን ይጠይቃል። በወቅቱ በሚፈጠሩት አንዳንድ ዕንቅፋቶች በመደናገጥ ፈንታ ከታሰበበት ግብ ለመድረስ መታገስን ይጠይቃል። "የረጅም ጊዜ ግብ" ወቅታዊ ለሆነው እንቅስቃሴ ምሪትን ይሰጣል። "የረጅም ጊዜ ግብ" የረጅም ዓመታት ዕቅድ ነው። አንዳንድ መሪዎች "የረጅም ጊዜ ግብ" ለ5 ወይም ለ10 ዓመት ያወጣሉ። ከአምስት ዓመት ወይም ከአስር ዓመት በኋላ እንደ ገና ለሚቀጥሉት 5 — 10 ዓመታት ሌላ ግብ ያወጣሉ። በነዚህ ዓመታት ካሰቡበት "ግብ" መድረስ ካልቻሉ፥ በተለይ ሊደረስበት የሚቻል "ግብ" ከሆነ፥ በአሠራራቸው ላይ አንድ ልክ ያልሆነ ነገር ይኖራልና የግድ አሠራራቸውን መለወጥ አለባቸው። የአጭር ጊዜ "ግብ" ለሳምንት፥ ለወር ወይም ለዓመት የሚወጣ "ግብ" ሊሆን ይችላል። ምናልባት ከላይ የጠቀስናቸው ጊዜዎችን ሁሉ መጠቀም ያስፈልግ ይሆናል። "በሳምንቱ፥ በወሩ መጨረሻ ላይ እነዚህን ተግባሮች መፈጸም አለብኝ..." ብለን እናቅዳለን። ፍሬያማ የሆኑ መንፈሳዊ መሪዎች "እናደርጋለን" ያሉትን ነገሮች ምን ያህሉን ማድረግ እንደቻሉ በየጊዜው ይገመግማሉ። ካሰቡበት "ግብ" ካልደረሱ፥ ምክንያቶቹን ለመረዳት ጥረት ያደርጋሉ። በትክክል ያልተሠራ ነገር ካለ ለማስተካከል ይሞክራሉ። አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ለሚሰጡት አገልግሎት ቢያንስ ቢያንስ የአንድ ዓመት ግብ ሊኖራቸው ይገባል።

### 3ኛ/ ዕለታዊ እንቅስቃሴ ዕቅድ (Operational Planning)

ዕለታዊ እንቅስቃሴን በሚመለከት ጉዳይ ላይ ዕቅድ ማውጣት የመሪው ኃላፊነት ነው። አገልግሎቱን እንደሚገባ መፈጸም የሚፈልግ የቤተ ክርስቲያን መጋቢ፣ መሥራት የሚፈልጋቸው ሥራዎች ብዙ ስለሆኑ፣ ጊዜውን በአግባቡ ለመጠቀም እንዲችል ዕለታዊ የሆነ ዕቅድ እንዲኖረው ያስፈልገዋል። በዛሬው ቀን "ይህንና ያንን ማድረግ አለብኝ"

በማለት ከቀኑ መጀመሪያ ላይ ዕቅድ ማውጣት አለበት። ወቅታዊ የሆነ የእንቅስቃሴ ዕቅድ፥

*(1) የቀኑን ልዩ ሥራዎችን ለመሥራት ማቀድ፥*

*(2) ሳምንታዊ፣ ወራዊ፣ በየሦስት ወሩ የሚካሄዱ ስብሰባዎችን ማቀድ፥*

*(3) የተወሰነው ግብ ላይ ለመድረስ የተፈጸሙትን ድርጊቶችንና እንቅስቃሴዎችን በየጊዜው መገምገም፥*

*(4) የወጣው በጀት ምን ዓይነት አቋም ላይ እንዳለ መከታተልን ያካተተ ነው።*

ከዚህ በላይ "ዕቅድ" ለማውጣት አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች በመጠኑም ቢሆን ተመልክተናል። "ዕቅድ" ለማውጣት ከወሰንን፥ አስፈላጊውን "ዕቅድ" እናውጣ። መንፈሳዊ መሪው (መጋቢው) ከሽማግሌዎች ጋር በመተባበር "ዕቅድ" ካወጣ በኋላ፥ የሚመለከታቸው ሁሉ በሚረዱትና በሚገባቸው ዓይነት ተዘርዝሮ እንዲቀርብ ማድረግ አለበት። በዚህ ዓይነት የሚመለከታቸው ሁሉ "ዕቅዱን" ካወቁ፥ መንፈሳዊው መሪ (መጋቢ) "ዕቅዱን" በተግባር ላይ ለማዋል በጣም ቀላል ይሆንለታል። ይሄ የወጣው "ዕቅድ" የቤተ ክርስቲያኒቱን አባል ጥያቄና ፍላጎት ሁሉ መልስ ይሰጣል ወይም ያሟላል ማለት አይደለም። አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን አባሎችን ደስ ለማሰኘት ብቻ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያኑ ካቀደው ውጪ ለመሥራት መንፈሳዊ መሪው ምንም ዓይነት እርምጃ መውሰድ የለበትም። ትክክል ያልሆነ ነገር ሠርቶ እግዚአብሔርን ቅር ከማሰኘት፥ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውን ሠርቶ ሰውን ማስከፋት ይሻላል። ቤተ ክርስቲያኒቱ ባወጣችው ዕቅድ ውስጥ አባላቱ ሁሉ ተሳታፊ እንዲሆኑ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከፍተኛ ጥረት ማድረግ አለባቸው። አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሊኖራት የሚያስፈልጉ ዕቅዶች ምን ዓይነቶች ይሆኑ? ዕቅዶቹ እንደየአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ይለያያል እንጂ፣ የሁሉም አንድ ዓይነት አይሆንም።

ቀደም ባሉት ንዑስ ክፍሎች እንደጠቀስነው፣ ዕቅድ በማውጣት ውስጥ ያለው ትልቁ ፍርሃት፥ (1) የሰው ዕቅድ እግዚአብሔር ሊሠራው ላሰበው ነገር እንቅፋት ይሆናል፥ (2) የሰው ዕቅድ የመንፈስ ቅዱስ ሥራን መተካት ይሆናል፥ (3) ሰው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ችላ ብሎ ራሱ የሚፈልገውን ነገር ለመሥራት ዕድል ይሰጣል የሚል ፍርሃት ነው። ሌላው ትልቅ ችግር፥ ዕቅዱን በተግባር ለማዋል የቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት ሁሉ እንዲሳተፉበት በማድረግ ፈንታ፥ ጥቂት መሪዎችና ደጋፊዎቻቸው ብቻ የሚሳተፉበት ሲሆን ነው። የዕቅዳችን ዋና ዓላማ በጣም ጥሩ የሆነ፣ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውን አገልግሎት ለመስጠት መሆን አለበት። አገልግሎታችን እጅግ በጣም ጥሩ እንዲሆን የምንፈልግበት ምክንያት፣ ራሳችንን አተልቀን ለማሳየት ወይም ሌሎችን ለመማረክ መሆን የለበትም። ያማረና ጥሩ የሆነ ነገር መሥራት እግዚአብሔርን ያስከብራል እንጂ አያሳፍ



ርም። ሰብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር ሙሴን እንዲሠራ ያዘዘው ቤተ መቅደስ ምን ዓይነት የሚያስደንቅ ውበት እንደነበረው መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ያማረ ነገር ለመሥራት የምንፈልገው፣ ከሌሎች በልጦ ለመታየት ሳይሆን፥ እግዚአብሔር የሰጠንን ስጦታ ለክብሩ ጥሩ አድርገን እንድንጠቀምበት ነው።

መንፈሳዊ መሪው በሚያወጣው ዕቅድ ውስጥ በእግዚአብሔር ዘንድ ተጠያቂነት እንዳለበት ማሰብ አለበት። የሚያወጣው ዕቅድ፥ የሚሠራው ያማረ ሥራ የራሱን ፍላጎት ለማሟላት፥ "ትልቅ አገልጋይ" ለመባል ነው? ወይስ ለእግዚአብሔር ክብር ነው? እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ መሪው ራሱን በጥንቃቄ መመርመር አለበት። ሰዎችን ለመጠቀም ዕቅድ ሲያወጣ፥ ዕቅዱ ብዙ ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያኑ እንዲጨመሩ ቢያደርግ ሥራው በእሳት የሚፈተንበት የፍርድ ቀን እንደሚመጣ ማወቅ አለበት። ***"...አንድ ጊዜ ከተመሠረተው መሠረት በቀር ማንም ሌላ መሠረት መጣል አይችልም፤ ይህም መሠረት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በዚህ መሠረት ላይ በወርቅ ወይም በብር በክቡር ድንጋይ ወይም በእንጨት፥ በሣር ወይም በገለባ የሚገነባ ቢኖር፥ እያንዳንዱ በምን እንደሠራ የሚገለጥበት የፍርድ ቀን ይመጣል፤ በዚያን ቀን የእያንዳንዱ ሰው ሥራ በምን እንደተሠራ በእሳት ተፈትኖ ይገለጣል"*** (1 ቆሮ. 3፥11-13)። ሰዎችን ወደ ክርስቶስ የማይሰበስብ፥ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ግንኙነት የማያጠናክር፥ ለአገልግሎት የማያዘጋጅ፥ እግዚአብሔር እንዲሆኑ የሚፈልግባቸውን እንዲሆኑ የማያደርግ ከሆነ፥ ዕቅዳችን ዋጋ የለውም። አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መጋቢዎች የራሳቸውን የግል ዕድገት ለማጠናከር በሰዎች የመጠቀም ዝንባሌ አላቸው። አንዳንድ መንፈሳዊ መሪዎች፣ "በማንም ሰው ዘንድ ተጠያቂነት የለብኝም" ብለው ያስቡ እንጂ፥ ከእግዚአብሔር ዘንድ ተጠያቂነት እንዳለባቸው ማወቅ ይገባቸዋል።

"ዕቅድ" ማውጣታችን እግዚአብሔርን ደስ እንዳናሰኝ እንቅፋት ይሆንብን ይሆን? ዕቅድ በእግዚአብሔር ዓላማና መመሪያ ሥር ሆኖ ከተሠራ፥ እግዚአብሔርን የበለጠ ደስ ለማሰኘት ይቀሰቅሳል። "ዕቅድ" የጸሎት ሕይወታችንን ያሳድጋል። ይኸውም፥ ስለምን መጸለይ እንዳለብን መመሪያ ይሰጠናል። ላወጣነው ዕቅድ ስንጸልይና እግዚአብሔር ለጸሎታችን መልስ ሲሰጠን ስናይ፥ እምነታችን እያደገ ይመጣል። "ዕቅድ" ቢኖር በዕቅዱ ተሳታፊ የሆኑት፥ ያቀዱትን ተግባራዊ ለማድረግ ስለሚጥሩ፥ ኃይላቸው የታደሰ ይሆናል። ዕቅድ ማውጣት የዕቅዱ ተካፋዮች ለአንድ ዓላማ እንዲሠሩ ስለሚያደርጋቸው፥ ምንም ያህል የተለያየ ባሕሪ ቢኖራቸውም ሕብረታቸውንና አንድነታቸውን ያጠናክራል። እርግጥ ነው በዕቅዳችን የምንተማመን ከሆነ፥ በእግዚአብሔር ላይ ያለንን መደገፍ ሊቀንስ ይችላል። ይሁን እንጂ፥ የእኛ "ዕቅድ" እግዚአብሔር መሥራት ያለበትን ሥራ መተካት ይችላል ማለት አይደለም። "ዕቅድ" በሙሴ፥ በኢያሱ፥ በነህምያና እንዲሁም በጳውሎስ ውስጥ እንቅፋትን አልፈጠረባቸውም። የሚያሰደንቀን ነገር ቢኖር፥ በዕቅድ ማውጣት ሂደት ውስጥ መሆን፥ ከኃያሉ እግዚአብሔር ዓላማና ፈቃድ ጋር የምንተ

ባበርበት መንገድ መሆኑ ነው። በእኛ ውስን በሆነው ሰዎች ሥራ የእርሱ ፈቃድ ሲፈጸም ከማየት የበለጠ ትልቅ ነገር ይኖር ይሆን? ስለዚህ የዕቅድ ማውጣት ሂደት ውስጥ ስንሆን፥ ራሳችንን ለእግዚአብሔር መሉ በሙሉ ካስገዛን፥ ፈቃዱ ሲፈጸም ማየት እንች ላለን። ቤተ ክርስቲያን ከሚኖራት ዕቅድ ውስጥ አንደኛው ምዕመናኑን ለተለያየ አገልግ ሎት ማብቃት ነው።

መንፈሳዊ መሪዎች እግዚአብሔር በጠራቸው አገልግሎት ውስጥ ፍሬያማ ለመሆን ያላቸው ራዕይና እንዲሁም ለአገልግሎት ያላቸው የልብ ቅናት ብቻ በቂ አይደለም። ይህንን በመረዳት ለቤተ ክርስቲያን አባሎቻቸው ጠቃሚ የሆነ ሥልጠና በመስጠት ለአገልግሎት ብቁ እንዲሆኑ ማዘጋጀት ያስፈልጋቸዋል። አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት፥ ብዙዎቹ ለምዕመናኖቻቸው አስፈላጊ የሆኑ እውነቶችን፥ የክርስትና እምነት ዶክትሪኖ ችን በማስተማር ትጋት ያሳያሉ ወይ? የቤተ ክርስቲያናቸው መዋቅር የተሠራው፥ የአባላቱን መንፈሳዊ ጥያቄ ለማሟላት ነው? የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፥ የአዳር ጸሎት፥ የወጣቶችና ያላገቡ ሰዎች አገልግሎቶችና ልዩ ልዩ ፕሮግራሞች ይካሄዳሉ? መሠረታዊ የሕዝቡ ፍላጎት በሞላ ጎደል የተሟላ ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ፥ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ከዚህ ሁሉ በላይ መሆን አለበት። ቤተ ክርስቲያን እምነው የዳኑትን ክርስ ቲያኖች እስተምራ ለልዩ ልዩ አገልግሎት ማብቃት አለባት። መጋቢዎችን፥ አስተማሪ ዎችን፥ እንዲሁም ወንጌላውያንን ማፍራት አለባት። ይሄም የመንፈሳዊው መሪ ወይም መጋቢ ኃላፊነት ነው።

## ምዕራፍ ፲፱

# ሚዛናዊ ውሳኔ

*"ማስተዋል የጎደላቸው ሰዎች ሁልጊዜ ትክክል የሆኑ ይመስላቸዋል፤ ጠቢባን ግን መልካም ምክርን ይቀበላሉ።"*
*(ምሳሌ 12፥15)*

ሁላችንም በሕይወት ዘመናችን ብዙ የተለያዩ ውሳኔዎችን አስተላልፈናል። እነዚህ በተለያየ ጊዜ የወሰንናቸው ውሳኔዎች፣ በሕይወታችን አሁን ያለንን አቋም እንዲኖረን፣ እንዲሁም በኑሯችን አሁን ከደረስንበት የኑሮ ደረጃ እንድንደርስ ምክንያት ሆነውናል። ዛሬ ያለንበት ሁኔታ ጥሩም ሆነ መጥፎ፣ እነዚያ በተለያየ ጊዜ ያስተላለፍናቸው የውሳኔዎ ቻችን ውጤቶች (ምክንያቶች) ናቸው። ያለምርጫችን፣ ያለፈቃዳችንና ያለውሳኔያችን እግዚአብሔር እንዲሁ ብድግ አድርጎ አሁን ካለንበት ሥፍራም ሆነ የኑሮ ደረጃ እንዳላስ ቀመጠን እርግጠኞች ነን። ከማንኛውም ነገር የበለጠ በውሳኔ አሰጣጣችን የእኔና የእና ንተ እውነተኛው "ገጸባህሪያችን" (character) የበለጠ ይታወቃል። እርግጥ ነው በሕይ ወታችን የወሰንናቸው ውሳኔዎች ሁሉ፣ በተለይ በዕድሜም ሆነ በእዕምሮ ባልበሰልንበት ዘመናችን የወሰንናቸው ውሳኔዎች ሁሉ በቀጥታ ከእኛ የመጡ ላይሆኑ ይችላሉ። አውቀ ንም ሆነ ሳናውቅ ፈቅደን ጓደኞቻችን፣ ወላጆቻችን የወሰኑልን አንዳንድ ውሳኔዎች ይኖ

ራሉ። ጥቂቶቹ ሲጠቅሙን፣ ብዙዎቹ ግን ሳይጎዱን እንዳልቀረ እንገምታለን። በሌላ በኩል ደግሞ እኛ ራሳችን ብቻ ውሳኔ የሰጠንባቸው ወይም የወሰንናቸው ውሳኔዎች አሉ። ከነዚያ ውስጥ ዋነኛውና ትልቁ ከእግዚአብሔር ጋር እንዲኖረን የፈልግነው ግንኙነት፣ እንዲሁም መንፈሳዊ ሕይወታችን መያዝ ያለበትን አቅጣጫ በንመርጥ የወሰነው ውሳኔ ነው። ከዚህ በፊት በሕይወታችን ከወሰንናቸው ውሳኔዎች ውስጥ የጠቀሙን ብቻ ሳይሆን የጎዱንም አሉ። ጉዳታችን አንዳንዶቹ ቀላልና ጊዜያዊ ሲሆኑ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ለረጅም ጊዜ የጎዱን፣ አሁንም እየጎዱን ያሉ ይሆናሉ። ከዚህ በፊት የኖርነውን ኑሮ እንደ ገና የመኖር ዕድል ቢሰጠን፣ አንዳንዶቻችን ከዚህ በፊት የወሰንናቸውን ውሳኔዎች አብዛኛዎቹን እንለውጣቸው ነበር።

የግል ሕይወታቸውን ብቻ ሳይሆን የሌሎችንም ሕይወት የሚነካ ውሳኔዎችን የሚያስተላልፉ ብዙዎች አሉ። ለምሳሌ ልጆቻቸውን በማሳደግ ላይ ያሉ ወላጆች፣ በየ ቀኑ የሚወስኑት ውሳኔ የልጆቻቸውን የሕይወት አቅጣጫ የመቀየስ ኃይል እንዳለው፣ እንዲሁም መንፈሳዊ መሪዎች በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚወስኗቸው የተለያዩ ውሳኔዎች፣ የምዕመናኑን የግል ሕይወት በበጎም ሆነ በክፉ ሊነካ እንደሚችል የታወቀ ነው። መንፈሳዊ መሪዎች ያለባቸውን ትልቅ ኃላፊነት በመረዳት፣ በተለይ በውሳኔ አሰጣጣቸው እግዚአብሔር አስፈላጊውን ጥበብንና ማስተዋልን እንዲሰጣቸው ሁልጊዜ መጸለይ አለባቸው። መንፈሳዊ መሪዎች ትክክል ያልሆነ ውሳኔ በመወሰናቸው፣ እንዲሁም ውሳኔ መወሰን ባለባቸው ጉዳይ ላይ በፍርሃትም ሆነ በማመንታት አስፈላጊውን ውሳኔ ባለመስጠታቸው ምክንያት በሚመሯቸው ሰዎች ሕይወት ላይ አንዳንድ በጎ ያልሆኑ ነገሮች ቢደርሱ፣ በእግዚአብሔር ዘንድ ተጠያቂ እንደሚሆኑ ማወቅ አለባቸው። መንፈሳዊ መሪዎች በውሳኔ አሰጣጣቸው ሊረዱቸው የሚችሉ ነገሮች ምንድናቸው? ትክክል ያልሆነ ውሳኔ ከመወሰን ራሳቸውን መጠበቅ የሚችሉትስ እንዴት ነው? በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ለነዚህና እነዚህን በመሳሰሉ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ሞክረናል።

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ካለባቸው ኃላፊነት ውስጥ አንደኛው ቤተ ክርስቲያንን በሚመለከት ልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ መስጠት ነው። ውሳኔ ከመስጠታቸው በፊት ግን ያላቸውን የስልጣን ድንበር አስቀድመው ለይተው ማወቅ አለባቸው። *"በዚህ ጉዳይ ላይ ውሳኔ ለመስጠት ስልጣን አለኝ ወይ?"* በማለት ራሳቸውን መጠየቅ ይኖርባቸዋል። በአመራራቸው ውስጥ ችግር ሊፈጥር የሚችለው፣ እንዲሁም ከሚመሩት ሕዝብም ሆነ አብረዋቸው ከሚሠሩት ሰዎች ጋር ግጭትን ወይም አለመስማማትን ሊፈጥርባቸው የሚችለው፣ ትክክለኛ ያልሆነ ውሳኔ መስጠታቸው ብቻ ሳይሆን፣ ከስልጣናቸው ውጪ በሆነ ጉዳይ ላይ ውሳኔ ስመስጠት ሲሞክሩ ነው። የቤተ ክርስቲያንን ዕድገት ወደ ኋላ ከሚጎትቱ ምክንያቶች አንደኛው፣ መሪዎች ትክክለኛ ያልሆነ ውሳኔ ሲወስኑ ብቻ ሳይሆን፣ በትክክለኛው ጊዜ አስፈላጊውን ውሳኔ አለማድረጋቸውም ጭምር ነው። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምንም ያህል ጥሩ ራዕይ ያላቸው ቢሆኑ፣ ራዕያቸውን በተግባር ላይ



ለማዋል ውሳኔ ማድረግ ካልቻሉ፣ ራዕያቸው ተራ አሳብ ወይም ምኞት ብቻ ሆኖ ይቀራል። ለመሆኑ "ውሳኔ" ማለት ምን ማለት ነው? *ውሳኔ (Decision)* የሚለውን ቃል የእንግሊዝኛው መዝገበ ቃላት፣ *"...አከራካሪ ወይም እርግጠኛነቱ ያልታወቀ ነገር መፍትሄ ማስጠት"* ይለዋል። እንዲሁም የተለያዩ ጸሀፊዎች "ውሳኔ" የሚለውን ቃል በተለያየ ሁኔታ ይገልጹታል፡

*አንዱ "የሚያከራክር፣ ወይም እርግጠኛነታቸው አጠያያቂ የሆኑ ነገሮች ሲያጋጥሙ፣ ከመፍትሄ መድረስ" ሲለው፡*

*ሌላው ደግሞ፡ "ለውሳኔ ከቀረቡት አማራጭ ነገሮች ውስጥ መዝኖ ጠቃሚውን ወይም የተሻለውን መምረጥ" ይለዋል።*

*ሌላው ደግሞ፡ "...አንድን ነገር በተሳካ ሁኔታ ለመስራት ይጠቅማሉ ተብለው የቀረቡትን አማራጭ ነገሮችን መዝኖ መወሰን..." ይለዋል።*

በየትኛውም ዓይነት ድርጅት ውስጥ "ጥሩ ውሳኔ" መስጠት የጥሩ አመራር ምልክት እንደሆነ ምሁራን ይናገራሉ። መንፈሳዊ መሪ በሚወስናቸው ውሳኔዎች፣ የሚመራውን ሕዝብ በአንድም ሆነ በሌላ ወደ አንድ ያልታወቀ አቅጣጫ ሊመራ የሚችል መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ከፍተኛ ጉዳት ሳይም ሊጥል ይችላል። ምንም ያህል ተጠንቅቆና አስቦ ቢወስንም፣ አንዳንድ ጊዜ ውሳኔው ትክክል ላይሆን ይችላል። ውሳኔው ጥሩ ውጤት ካስገኘ፣ ሕዝቡ መሪውን ማመስገን ይጀምራል (ዘጽ. 14፡31)። ነገር ግን "ውሳኔው" የተጠበቀውን ዓይነት መልካም ውጤት ካላስገኘ፣ በመሪው ላይ የሕዝብ ተቃውሞ ሊያስነሳበት ይችላል (ዘጸ. 16፡2-3)። መንፈሳዊ መሪ በሚወስናቸው ትክክል ባልሆኑ ውሳኔዎች ምክንያት ለሚፈጠሩት ችግሮች ሁሉ "ተጠያቂነት አለብኝ" ብሎ ስለሚያስብ፣ ብዙ ጊዜ ውሳኔ ለመወሰን ይፈራል፤ ወይም ያመነታል። ውሳኔ ማስተላለፍ ትልቅ ኃላፊነት ስላለበት፣ በመሪው ሕይወት ውስጥ ከፍተኛ የስሜት ግፊት ወይም ውጥረት (pressure) ሊያመጡበት ከሚችሉት ምክንያቶች መካከል አንደኛው ነው።

በውሳኔ አሰጣጥ ውስጥ ሁልጊዜ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ አማራጭ ነገሮች ይኖራሉ። ውሳኔ ሰጪው ...ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሁኔታዎችን፣ ...ሰዎችን፣ ...አማራጭ ነገሮችን ይመለከታል። ለምሳሌ በአንድ ነገር ላይ ውሳኔ ለመስጠት፣ የቀረቡለትን አማራጭ ነገሮች በጥንቃቄ ከመረመረ በኋላ አንደኛውን መርጦ ሲወስድ፣ ሌሎች ያልመረጣቸውን ግን ይተዋል። መሪው ውሳኔ ለመስጠት በጣም አስቸጋሪ የሚሆንበት፣ ለምርጫ የቀረቡት ሁሉም በይዞታቸው በጣም ተቀራራቢነት ወይም ተመሳሳይነት ያላቸው እንደሆነ ነው። የጥሩ አመራር ዋና ቁልፍ፣ ጊዜውን የጠበቀ ውሳኔ መወሰን መቻል፣ ያለማመንታትና ያለፍርሃት ከውሳኔ መድረስ ነው። በተለይ አሳሳቢነት ያለውን ማንኛውንም ዓይነት ውሳኔ ለመወሰን፣ መሪው ደፋርና ቆራጥ መሆን አለበት። ደፋርና

ቆራጥ መሆን ብቻ ሳይሆን፣ ውሳኔው የተጠበቀውን ዓይነት ጥሩ ውጤት ባያስገኝ፣ ኃላፊነቱን ለመቀበል ፈቃደኛ መሆን አለበት። መንፈሳዊ መሪዎች በውሳኔ አሰጣጣቸው ከዓለማውያን መሪዎች የሚለዩበት፣ ለሚያስተላልፏቸው ውሳኔዎች ሁሉ የእግዚአብሔርን ፈቃድ፣ የመንፈስ ቅዱስ ምሪትን መጠየቅ የሚችሉ መሆናቸው ነው። ጳውሎስ ስለ ውሳኔ አሰጣጡ ሲናገር፣ *"ወደ መቄዶንያ ስሄድ እግረ መንገዴን ልጎበኛችሁና ከመቄዶንያም በእናንተ በኩል ተመልሼ ወደ ይሁዳ ስሄድ በጉዞዬ እንድትረዱኝ አቅጄ ነበር። ይህን ሳደርግ በሚገባ ሳላስብ ያደረግሁት ይመስላችኋልን? ወይስ በዓለማዊ ልማድ እንደ 'አዎን፣ አዎን' ወዲያው ደግሞ፣ 'አይደለም፣ አይደለም' የምል ይመስላችኋል..."* (2 ቆሮ. 1፥16-19) ይላል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሪዎች የሚሰጡት አገልግሎት፣ የሚወስኑት ውሳኔ፣ በበጎም ሆነ በክፉ የሌሎችን ሕይወት የመንካት ኃይል እንዳለው በማወቅ፣ የሚያገለግሉት ሕዝብ በመጠቀም ፈንታ እንዳይጎዳ፣ ውሳኔ አሰጣጣቸው ጥበብና ማስተዋል የጎደለው እንዳይሆን መጠንቀቅ አለባቸው። በግዴለሽነት የሚወስኗቸው ውሳኔዎች የእግዚአብሔርን ሕዝብ ቢጎዳ፣ በጌታ ዘንድ ተጠያቂዎች እንደሚሆኑ መዘንጋት የለባቸውም። መንፈሳዊ መሪዎች በአገልግሎታቸው እግዚአብሔርን የሚያከብሩ፣ እንዲሁም የሚያገለግሏቸውን ሰዎች እግዚአብሔር እንደሚወዳቸው የሚወዱ ከሆነ፣ በውሳኔ አሰጣጣቸው እግዚአብሔር እንዲረዳቸው፣ ጥበብንና ማስተዋልንም እንዲሰጣቸው ቢጠይቁ፣ በገባላቸው ተስፋ *መሠረት* ይሰጣቸዋል (*ያዕ.* 1፥5)።

### 1. *መሪዎች በሚወስኑት ውሳኔ የመሪነት ችሎታቸው ይመዘናል*

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ካለባቸው ከፍተኛ ኃላፊነት ውስጥ አንደኛውና ትልቁ፣ *"ውሳኔ መወሰን"* እንደሆነ ቢያውቁትም፣ አንዳንዶቹ ውሳኔ መስጠት የማይደፍሩ ወይም የሚያመነቱ ሲሆኑ፣ አንዳንዶች ግን አስፈላጊውን ጥንቃቄ ሳይደርጉ በችኮላ የሚወስኑ ናቸው። እንደነዚህ ዓይነቶቹ ጥሩ መሪ የመሆን ችሎታ (ዝንባሌ) የሌላቸው ናቸው። መንፈሳዊ መሪዎች አንድ ዓይነት ውሳኔ ከማስተላለፋቸው በፊት፣ ትክክለኛ ውሳኔ መወሰን እንዲችሉ፣ በቅድሚያ ውሳኔ ሊሰጡበት በሚፈልጉበት ጉዳይ ላይ በቂ ዕውቀት አላቸው ብለው ከሚያስቧቸው ሰዎች ጠቃሚ የሆነ ሀሳብ መሰብሰብ፣ እንዲሁም በአካባቢያቸው ካሉት ሰዎች፣ አብረዋቸው ከሚሠሩት ሠራተኞች አስተያየትም ሆነ ምክር መጠየቅ፣ ትክክለኛ የሆነ ውሳኔ ለመወሰን ይረዳቸዋል። መጨረሻ ላይ ግን ውሳኔ መስጠት ኃላፊነቱ የራሳቸው ነው። ለመወሰን ፈቃደኞች ካልሆኑ፣ መሪነታቸውንና ሥልጣናቸውን በራሳቸው ፈቃድ መተዋቸው (መልቀቃቸው) እንደሆነ ሊያውቁት ይገባል። ውሳኔ ለመወሰን ድፍረት የሌለውን መሪ መከተል የሚፈልግ ሰው የለም። መሪዎቻቸው ውሳኔ ለመወሰን ብቃትና ማስተዋል የሌላቸው መሆናቸውን የሚከተሏቸው ሰዎች ካወቁ፥ እነርሱን እንደ መሪዎቻቸው አድርገው መቀበል ያቅታቸዋል። አንዳንድ መሪዎች ውሳኔ ለመወሰን የሚያመነቱት ወይም የሚፈሩት ለምን ይሆን? ብለን መጠየቃችን አይቀርም።



ከምክንያቶቻቸው መካከል አንደኛው "ምናልባት ልክ ያልሆነ ወይም የተሳሳተ ውሳኔ እወስን ይሆናል" ብለው በመፍራት ነው። እዚህ ላይ ማወቅ ያለብን እውነት ቢኖር፣ ሁልጊዜ ትክክለኛ የሆነ ውሳኔ ለመወሰን የሚያስችል አንድ ዓይነት መመሪያ ወይም ቀላል ዘዴ የሌለ መሆኑ ነው። ትክክለኛ የሆነ ውሳኔ ለመወሰን አቋራጭ የሆነ መንገድ፣ ወይም ቀመር (ፎርሙላ) ቢኖር፣ በግል ሕይወታችንም ሆነ በቤተ ክርስቲያናችን የምናስተላልፋቸው ውሳኔዎች ሁሉ ከማንኛውም ዓይነት ስሁተት ነጻ ይሆኑ ነበር። ይሁን እንጂ እንዲህ ዓይነቱ መመሪያ ስለሌለን፣ እግዚአብሔር ሁልጊዜ እንዲረዳን፣ ጥበብና ማስተዋልን እንዲሰጠን መጠየቅ፣ እንዲሁም በውሳኔ አሰጣጣችን ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አለብን።

በዓለም ውስጥ ታላላቅ ውሳኔዎችን ያስተላለፉ ታላላቅ የታሪክ ሰዎች እንደነበሩ፣ ዛሬም እንዳሉ የታወቀ ነው። ከብዙዎቹ መካከል፥ ሐዋርያው ጳውሎስ፣ ማርቲን ሉተር፣ አብርሃም ሊንከን፣ ማሀተመ ጋንዲ፣ ወዘተ. ይገኙበታል። እነዚህ ታላላቅ ሰዎች ውሳኔያቸው በሰዎች ልጆች ሕይወት ላይ ያመጣውን በጎ ነገር እናውቃለን።

ታሪክ ፈጽሞ የማይረሳቸው እነ ሂትለር፣ ካርል ማርክስ፣ ስታሊን፣ ሞሶሎኒም ታላላቅ ውሳኔዎችን የወሰኑ ናቸው። እነዚህም የወሰኗቸው ውሳኔዎች በሰዎች ሕይወት ላይ ያደረሰውን ታላቅ ጥፋት እናውቃለን።

እኔና እናንተም በሕይወታችን "ተቀዳሚ" በምናደርጋቸው ነገሮችና በምንወስናቸው ውሳኔዎች እውነተኛው ማንነታችን ተለይቶ ይታወቃል። ትክክል ያልሆነ ቅደም ተከተል መንፈሳዊ ሕይወታችንን የሚጎዳውን ያህል ትክክል ያልሆነ ውሳኔ የሰጠን እንደሆነ ይጎዳል። መንፈሳዊ መሪዎች የሚወስኑት ውሳኔ ራሳቸውን ብቻ ሳይሆን የሚመሩትን ሕዝብና ቤተ ክርስቲያንን፣ እንዲሁም በመንፈሳዊ ድርጅት ውስጥ ያለውንም አገልግሎትና አገልጋዮችንም ይጎዳል። እውነተኛነቱ የማያጠያይቅ መረጃዎችን ከሰበሰቡ በኋላ ፈጣንና ግልጽ የሆኑ ውሳኔዎችን ማስተላለፍ የእውነተኛ መሪዎች ኃላፊነት ነው። በተፈጥሮአቸው ሊሆን የሚችለውን ነገር አስቀድሞ የማየት ችሎታ (ስጦታ) ያላቸው ሰዎች፣ ብዙ ጊዜ ለሌሎች ግልጽ ሆኖ የማይታየው ነገር ለእነርሱ ግልጽ ሆኖ ይታያቸዋል። በዚህ ዓይነት በዙሪያቸው ያሉትን ሁኔታዎች መርምረውና አጥንተው ውሳኔ መስጠት የሚችሉ መሪዎች ከሌሉ፣ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን እንደሚገባው ማደግ እንደማትችል ግልጽ ነው። በስሜታቸው ችኩሎች (ስሜታውያን) የሆኑ ሰዎች፣ እንደሚገባው ጊዜ ወስደው ሳያጠኑ፣ "እንዲህ መሆን አለበት" በማለት እርምጃ የሚወስዱ አሉ። እውነተኛ መሪዎች ግን መረጃዎችን ከሰበሰቡና ካመዛዘኑ በኋላ መልካም ነው የሚሉትን ውሳኔ ያስተላልፋሉ። መንፈሳዊ መ[illegible] የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን እርግጠኛ ከሆኑ፣ ምንም ዓይነት ነገር ሳይፈሩ ውሳኔ ይሰጣሉ። እውነተኛ የሆኑ መንፈሳዊ መሪዎች የተነሱበትን ዓላማ (ግብ) ለመፈጸም ወደ ፊት ይገፋሉ እንጂ፣ ሁኔታዎች ልክ

ካልመጡ በማለት ሌላ ማምለጫ ዘዴዎችን (መንገዶችን) አስቀድመው አያዘጋጁም። እንዲሁም የታቀደው ነገር እንደታሰበው ባይሆን፣ ያልተሳካበትን ምክንያት ሌሎች ሰዎችን በማድረግ ራሳቸውን ከተጠያቂነት ነጻ አያደርጉም።

በውሳኔ አሰጣጣቸው እንደ ምሳሌ ከምንጠቅሳቸው መንፈሳዊ አባቶች (መሪዎች) መካከል አንደኛው አብርሃም ነው። አብርሃምና ሎጥ እስከተወሰነ ጊዜ ድረስ በሰላም አብረው ይኖሩ ነበር። ንብረታቸው እጅግ ሲበዛ ግን ሥፍራው አልበቃ ስላላቸው፣ በአብርሃምና በሎጥ እረኞች መካከል ጠብ መፈጠር ጀመረ። ይሄን ሁኔታ የተመለከተው አብርሃም ዝምድናቸው የበለጠ እንዳይበላሽ ፈጣን እርምጃ መውሰድ እንዳለበት ተገንዝቦ፣ አብርሃም ሎጥን *"እኛ ወንድማማቾች ነንና በአንተና በእኔ ወይም በእረኞቻችን መካከል ጠብ ሊኖር አይገባም። ይኸው እንደምታየው አገሩ ሰፊ ነው፤ ብንለያይ ይሻላል። አንተ ግራውን ብትመርጥ፣ እኔ ወደ ቀኝ እሄዳለሁ፤ አንተ ቀኙን ብትመርጥ፣ እኔ ወደ ግራ እመራለሁ"* (ዘፍ. 13፥9) በማለት የፈለገውን እንዲመርጥ መጀመሪያ ዕድሉን ለሎጥ ሰጠው። ፈጣን የሆነው የአብርሃም ውሳኔ በሁለቱ መካከል የነበረው የወንድማማችነት መንፈስ እንዲቀጥል፣ በእርሱና በሎጥ እረኞች መካከል ሊፈጠር የነበረው ግጭት ቶሎ እንዲረግብ አደረገ። በሌላ ጊዜ ደግሞ በዚያው በሰዶም ውስጥ የውጪ ወራሪዎች (ጠላቶች) መጥተው በሰዶምና በጎሞር ያገኙትን ሀብትና ምግብ ሁሉ ዘርፈው ሲሄዱ፣ ሎጥና ቤተሰቡንም ማርከው ንብረቱንም ዘርፈው ሄዱ (ዘፍጥረት 14)። ሎጥንና ቤተሰቡን ለማዳን አብርሃም ፈጣን የሆነ ውሳኔ (እርምጃ) በመውሰዱ፣ ጠላቶቹ ብርቱና ኃይለኞች ቢሆኑም፣ ጠላቶቹን አሳዶ የወንድሙን ልጅ ሎጥን፣ ንብረቱን እንዲሁም ቤቶችንና ሌሎችን ምርኮኞች አስመለሰ። ይሄም በጣም አስፈላጊና አሳሳቢ በሆነበት ጊዜ አብርሃም የወሰደው ፈጣን የእምነት ውሳኔ ነበር።

ሙሴም የውሳኔ ሰው ነበር። በወቅቱ በፈርኦን ቤተ መንግሥት ውስጥ ተዝናንቶና ተመችቶት መኖር ሲችል፣ በአንዳንድ ሰዎች ዘንድ "ሞኝ" የሚያሰኘውን ዓይነት ውሳኔ ወሰነ። *"ሙሴ ካደገ በኋላ የፈርዖን የልጅ ልጅ መባልን በእምነት እምቢ አለ። ለጥቂት ጊዜ በኃጢአት ከሚገኝ ደስታ ይልቅ፣ ከእግዚአብሔር ጋር መከራን መቀበል መረጠ። ከግብፅ ሀብት ይልቅ ስለ ክርስቶስ መከራን መቀበል እጅግ የሚበልጥ ሀብት መሆኑን ተገነዘበ፤ ወደ ፊት የሚቀበለውን ብድራት ከሩቅ ተመልክቷልና"* ይላል (ዕብ. 11፥24-26)። ዕብራውያን ምዕራፍ 11፣ ታላላቅ መንፈሳዊ አባቶች በሕይወታቸው የወሰዱትን እርምጃዎችንና ውሳኔዎችን ይዘረዝራል። እነዚህ ታላላቅ የእምነት ሰዎች፣ በሌሎች ያልታያቸው፣ ለእነርሱ ግን የታያቸው በመሆኑ፣ ከፍተኛ ዋጋ እንደሚያስከፍላቸው እያወቁ የተጠሩበትን ዓላማ ለመፈጸም፣ የራሳቸውን ውሳኔ የወሰኑ ናቸው። ከሐዋርያት በኋላም በዘመናት ለወንጌል ተልኮ ራሳቸውን የሰጡ፣ ታሪክ ያደነቃቸው፣ የውሳኔ ሰዎች ነበሩ። እነዚህም የእግዚአብሔርን ድምጽ (ጥሪ) ሰምተው፣ በቆራጥነትና በድፍረት ታላላቅ ውሳኔዎችን የወሰኑ የወንጌል መልዕክተኞች (ሚሲዮናውያን) ናቸው። ዛሬ ወንጌል ለብዙዎቻ



ችን ሊደርሰን የቻለው፣ እነዚህ ቆራጥና ደፋር የሆኑ ሰዎች ትክክለኛ የሆነ ውሳኔ በመወሰናቸው ነው። ዊሊያም ኬሪ ከእግዚአብሔር ራዕይን ሲቀበል፣ ውሳኔው ብዙ ዋጋ እንደሚያስከፍለውና አስቸጋሪ ሁኔታ ላይ ሊጥለው እንደሚችል ቢያውቅም፣ ሕንድ አገር ሄዶ ወንጌል ለመስበክ ወሰነ። እንዲሁም ዴቪድ ሊቪንግስተንም ከእግዚአብሔር ጥሪ ሲደርሰው፣ በወቅቱ ልዩ ልዩ እንቅፋቶች ቢያጋጥሙትም፣ የወንጌልን ሥራ ለመፈንጠቅ፣ አገሩንና ወገኖቹን ትቶ ወደ አፍሪካ ለመሄድ ወሰነ። እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ብርቱ የሆኑ መንፈሳዊ መሪዎች፣ በመንገዳቸው ላይ ያጋጠሟቸው አንዳንድ እንቅፋቶች ወይም ችግሮች ዓላማቸውን ሳያስለውጧቸው፣ በጨለማ ውስጥ ለነበሩት የወንጌል ብርሃን ለብዙዎች ማዳረስ ቻሉ።

## 2. የውሳኔ ሰው ለመሆን ድፍረትን (Courage) ይጠይቃል

መንፈሳዊ መሪ እግዚአብሔርን ለማክበርና ለማስከበር መልካም *"ገጸ ባሕሪ" (character)* ያለው ሰው መሆን አለበት። ሰውን መልካም *"ገጸባሕሪ"* እንዳለው ከሚያሳዩት ነገሮች መካከል አንደኛውና ትልቁ "ድፍረት" ወይም ቆራጥነት ነው። በሚያምንበት ሀሳብ ላይ ጸንቶ ለመቆም ድፍረት (ወኔ) ያለው፣ ብርቱ ሰው ነው። "ብርቱ" ሰው፣ "እውነት ነው" ብሎ አምኖ የተቀበለውን አሳብ፣ ምንም ዓይነት ከፍተኛ ዋጋ የሚያስከፍለው ቢሆንም፣ ወደ ፊት ይገፋበታል እንጂ ወደ ኋላ አያፈገፍግም። ብርቱ የሆነ እውነተኛ መንፈሳዊ መሪ፣ እርሱ ራሱ ያመነበትን እንጂ በሰው አሳብ በመሳብ (በመገፋት) ውሳኔ አይወስንም። ቀላል ወይም አቋራጭ የሆነ መንገድ ፈልጎ ከውሳኔ አይደርስም። ውሳኔው በሐቀኝነት፣ *"በአጠቃላይ እውነት" (Principle)* ላይ የተመሠረተ እንጂ፣ ሁኔታው ወዴት እንደሚያደላ ወይም ምን ዓይነት አቅጣጫ እንደሚይዝ አይቶ አይደለም። የሰዎች ማስፈራራት፣ ግፊትም ሆነ የሚሰጡት አስተያየት በውሳኔው ላይ ተጽዕኖ እንዲያደርጉበት አይፈቅድም። ጥቅም አገኝበታለሁ በማለት፣ ለመታወቅና ሥልጣን ለማግኘት ሲል፣ ሌላው ቀርቶ "ተወዳጅ ልሁን" በማለት፣ እንዲሁም የሰዎችን ነቀፋና ተቃውሞ በመፍራት እንኳን ውሳኔ አይወስንም፤ እንዲሁም የወሰነውን ውሳኔ አይለውጥም። በጣም የሚያሳስበው ነገር ቢኖር የሚመራቸው ሰዎች በጎነትና መንፈሳዊ ዕድገት እንጂ፣ የሚወረወርበት ነቀፋ አይደለም። ሰዎች እንዲያመሰግኑት ሲል ብቻ፣ የሚመራቸውን ሕዝቦች የሚጎዳ መሆኑን እያወቀ ምንም ዓይነት ውሳኔ አያስተላልፍም። ቤተ ክርስቲያን ደፋርና ቆራጥ የሆኑ መንፈሳዊ መሪዎች ያስፈልጓታል። ደፋር ስንል የሥጋ ድፍረት ብቻ ሳይሆን "የሞራል ድፍረትንም" ያካትታል።

"ፍርሃት" ከሰው ተፈጥሯዊ ባሕሪ አንደኛው ቢሆንም፣ በድፍረታቸው ታሪክ የሚያስታውሳቸው ታላላቅ መሪዎች በዓለም ውስጥ መጥተው ሄደዋል። ከብዙዎቹ መካከል አንደኛው ሐዋርያው ጳውሎስ ነው። ጳውሎስ በድፍረቱ የታወቀ ሰው ይሁን እንጂ፣ በተለያየ ሁኔታ ውስጥ ሲያልፍ የነበረበትን ፍርሃት አልሸሸገም። ለቆሮንቶስ

አማኞች በጻፈው በሁለተኛው መልዕክቱ "ወደ እናንተ ስመጣ በትልቅ ፍርሃትና መንቀጥቀጥ ነው" ይላቸዋል (2 ቆሮ. 2፥3)። ዝቅ ብሎ 2 ቆሮ. 7፥5 ላይ ደግሞ "...ወደ መቄዶንያ በመጣን ጊዜ ከየአቅጣጫው መከራ ደረሰብን እንጂ ለሥጋችን ዕረፍት አላገኘንም፤ ከውጭ ጠብ ከውስጥ ደግሞ ፍርሃት ነበረብን" ይላቸዋል። ጳውሎስ ይህን የመሰለ ፍርሃት የነበረበት ይሁን እንጂ፣ ጌታውን ለማገልገል የወሰነውን ውሳኔ እንዲለውጥ አላደረገውም። በድፍረታቸው በጣም ከታወቁት ታላላቅ መንፈሳዊ መሪዎች መካከል ሌላው ሰው በመካከለኛው ዘመን የተሃድሶ መሪ የነበረው ማርቲን ሉተር ነበር። በወቅቱ የነበረውን የቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት በመቃወሙ ምክንያት ተፈጥሮ በነበረው ችግር፣ ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች ፊት ቀርቦ የተቃወመበትን ምክንያት እንዲያስረዳ ጥሪ ሲቀርብለት፣ ምንም ዓይነት ፍርሃት አይታይበትም ነበር። "ስለ እኔ የፈለጋችሁትን ነገር ማሰብ ትችላላችሁ፤ ፈርቼ ግን ከተናገርኩት ቃል አንዱንም አላጥፍም። አንዷን ቃሌን ማጠፍ ወይም መካድ ቀርቶ ሽሽቼ የትም አልሄድም" አለ። በጠላቶቹ እጅ ይሞታል ብለው የፈሩ አንዳንድ ወዳጆቹ፣ ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች ፊት ቀርቦ ተቃውሞውን እንዲያበግ ሲጠሩ፣ እንዳይሄድ አጥብቀው ለምነውት ነበር። ሉተር ግን "ፊት ለፊት ቀርቤ አቋሜን ገልጬ እናገራለሁ እንጂ፣ በምንም ዓይነት ሽሽቼ የትም አልሄድም" አለ። በመጨረሻም ንጉሡ ቻርለስ 5ኛው ፊት በቀረበበት ጊዜ፣ ቤተ ክርስቲያን ታስተምረው የነበረውን ትምህርት ተቃውሞ የጻፋቸውን ጽሁፎች ጠረጴዛው ላይ ቆልለው ካሳዩት በኋላ፣ "እነዚህን ጽሁፎች በመጻፌ ተሳስቻለሁ" ብሎ እንዲናገርና ይቅርታ እንዲጠይቅ ትዕዛዝ ተሰጠው። ማርቲን ሉተር ግን በድፍረት፣ "መጽሐፍ ቅዱስን እየጠቀሰ መሳሳቴን የሚያሳየኝና የሚያሳምነኝ ሰው ካልመጣ በስተቀር፣ እውነት ነው ብዬ አምኜ ከጻፍኩት ውስጥ፣ አንድም ቃል ለመሰረዝ ሀሳቤ እሺ አይለኝም" የሚል መልስ ከሰጠ በኋላ፣ "እነሆ ቆሜአለሁ! ከዚህ ሌላ ምንም ማድረግ አልችልም! እግዚአብሔር ሆይ! እርዳኝ! አሜን!" በማለት ንግግሩን ደመደመ። ማርቲን ሉተር በዓለም የተመደበለትን ዘመን ጨርሶ ሊሞት ጥቂት ቀን ሲቀረው፣ በንጉሡ በቻርለስ 5ኛ ፊት የቀረበበትን ጊዜ አስታውሶ፣ "በዚያን ወቅት ምንም ዓይነት ፍርሃት በውስጤ አልነበረም። አስፈሪ በሆነ ሁኔታ ውስጥ እግዚአብሔር ፍጹም የሆነ ድፍረትን ይሰጣል" አለ።

አማኝ ሁሉ ሉተር የነበረውን ዓይነት ድፍረት ይኖረዋል ማለት አይደለም። ይሁን እንጂ፣ መንፈሳዊ መሪ በውሳኔ አሰጣጡ ደፋር እንዲሆን ይጠበቅበታል። በተፈጥሯችን ሁላችንም ፍርሃት ያለብን በመሆናችን፣ ፍርሃታችንን የሚያግዝ ኃይል ያስፈልገናል። ይህንን የሚያውቀው እግዚአብሔር በኃይል እንድንሞላ መንፈስ ቅዱስን ያፈስልናል። መንፈስ ቅዱስም ወደ ልባችን ሲገባ፣ ፍርሃታችን ጠፍቶ በድፍረት የተሞላን እንሆናለን። ደቀ መዛሙርቱ በፍርሃት የተዋጡበት ጊዜ ነበር። በሌላ ጊዜ ደግሞ ብዙዎች እስኪደነቁ ድረስ በድፍረት የተሞሉበት ጊዜ እንደነበር እናስታውሳለን። "በዚያው ዕለት፣ በሳምንቱ መጀመሪያ ቀን በምሽት፣ ደቀ መዛሙርቱ አይሁድን በመፍራት በሮቹን ቆልፈው ተሰብስበው ሳሉ፣ ኢየሱስ መጣና በመካከላቸው ቆሞ፣ 'ሰላም ለእናንተ ይሁን' አላቸው" ይላል (የዮሐ. 20፥19)። በሌላ ጊዜ ደግሞ "ካህናቱም ጴጥሮስና ዮሐንስ እንዲህ በድፍረት ሲናገሩ ባዩአቸው ጊዜ..." ይላል (የሐዋ. 4፥13)። ደቀ መዛሙርቱ በሁለቱም ጊዜ ያጋጠማቸው ተቃውሞ አንድ ዓይነት ቢሆንም፣ ሁለቱንም ጊዜ ተቃውሞውን ያስተናገዱት በአንድ ዓይነት ሁኔታ እንዳልነበረ ተመልክተናል። ምስጢሩ፣ በሁለተኛው ተቃውሞ ጊዜ ያልፈሩት በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ በመሆናቸው ነበር (የሐዋ. 2፥4)። እውነተኛ መንፈሳዊ መሪዎች ተቃውሞ ቢደርስባቸውም፣ በአደጋ የተከበቡ ቢሆኑም፣ እንዲሁም ውሳኔያቸው በሌሎች ተቀባይነት የሌለው ቢሆንም፣ ምን ጊዜም ከውሳኔያቸው ወደ ኋላ ማፈግፈግ የለባቸውም።



## 3. ትክክለኛ ያልሆነ ውሳኔ ከመወሰን መዳን እንዴት ይቻላል?

ትክክለኛ የሆነ ውሳኔ መወሰን በጣም ቀላል አይደለም። አርቆ አሳቢነትና ማስተዋልን ይጠይቃል። ትክክል ያልሆነ ውሳኔ መወሰን ደግሞ፣ ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል። ስለዚህ፣ መንፈሳዊ መሪ ትክክለኛ ያልሆነ ውሳኔ በመወሰን በራሱና በሚመራቸው ሕዝቦች ላይ ሊደርስ ከሚችለው ጉዳት ለማምለጥ፣ ትክክለኛ የሆነ ውሳኔ እንዴት መወሰን እንደሚቻል ማወቅ ያስፈልገዋል። ትክክል ያልሆነ ውሳኔ ከመወሰን መዳን የሚቻልበትን መንገድ ለማወቅ ብዙ ጥረትን ስለሚጠይቅ፣ በመንፈሳዊ መሪው ላይ ከፍተኛ ሥጋትና ጭንቀት እንደሚጨምርበት የታወቀ ነው። ሞርሊ የተባሉ ጸሐፊ፣

> "ትክክለኛ የሆነ ውሳኔ ለመወሰን ዋስትናው፣ ትክክል ያልሆነ ውሳኔ ላለመወሰን የሚቻልበትን መንገድ ማወቅ ነው" አሉ።[40]

አንዳንድ መንፈሳዊ መሪዎች ውሳኔ ለመስጠት የሚያመነቱበት አንደኛው ምክንያት ትክክል ያልሆነ ውሳኔ ቢወስኑ፣ ጉዳት ላይ የሚወድቁት እነርሱ ራሱ ብቻ ሳይሆኑ፣ የሚመሯቸው ሰዎችም ጭምር መሆናቸውን ስለሚያውቁ ነው። ትክክል ያልሆነ ውሳኔ በማስተላለፋቸው፣ ቤተ ክርስቲያናቸውን ጉዳት ላይ የጣሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ብዙ ናቸው።

የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት የተሰማሩበትን የወንጌልን አደራ እንደሚገባው መፈጸም እንዲችሉ፣ ኢየሱስ በቃል ብቻ ሳይሆን፣ የግል ሕይወቱን አያዩ እንዲማሩ ዕድል በጥቷቸው ነበር። "እንዲህ ሁኑ..." ማለት ብቻ ሳይሆን፣ ራሱ በተግባር ያሳያቸው ነበር። ይሰጣቸው የነበረው ትምህርት፣ ተማሪ ክፍል ውስጥ ቁጭ ብሎ ከሚስተማረው እንደሚ

[40] Patrick Morley. The Man In The Mirror, Wolgemuth & Hyatt, Publishers, Brentwood, TN, 1989.

ማረው ትምህርት ሳይሆን፣ በአገልግሎት ላይ እንዲሰለፉ ዕድል በመስጠት እያገለገሉ እንዲማሩ ያደርግ ነበር። አንድ ጊዜ ኢየሱስ ሰባ ሁለቱን መርጦ፣ ሁለት ሁለት አድርጎ የምስራቹን ቃል እንዲሰብኩ፣ በሽተኞችን እንዲፈውሱ ሙሉ ሥልጣን ሰጥቶ እንደላካቸው እናስታውሳለን (የሉቃ. 10፥1-24)። በተሰለፉበት አገልግሎት ጥሩ ውጤት ያገኙበት ጊዜ፣ እንዲሁም የተሰጣቸውን ሥልጣን በደንብ መጠቀም አቅቷቸው የተሸነፉበት ጊዜም እንደነበረ እናስታውሳለን (ማር. 9፥14-29)። እኛም ስለ አገልግሎት ማወቅ የሚገባንን ሁሉ አውቀን ስላልጨረስን፣ ስናገለግል ያለማንበት ጊዜ ብቻ ሳይሆን፣ ያበላሸንበት ጊዜም እንደነበረ እናውቃለን። ያለፈውን መለወጥ ስለማንችል፣ መጨነቅና ማሰብ ያለብን "ትላንት" ስለ ሠራነው ስህተት ሳይሆን፣ ትላንት የሠራነውን ዓይነት ስህተት ዛሬም ደግመን እንዳንሠራ መሆን አለበት።

አንዳንድ መንፈሳዊ መሪዎች ከሌላው ሰው የበለጠ ነገርን በጥልቀት ቶሎ የመረዳት፣ ሁኔታዎችን በርቀት ወይም አስቀድሞ የመመልከት ችሎታ አላቸው። ዛሬ የሚወስኑት ውሳኔ ወደ ፊት ምን ዓይነት ውጤት እንደሚኖረው አስቀድመው ይረዳሉ። ጥሩ ነገር ይወጣዋል ተብሎ ከማይታመንበትና ከማይጠበቅበት ሁኔታ ውስጥ መልካም ነገር እንዳለበት ይታያቸዋል። ሌሎች *"መጥፎ ነው…ዋጋ የለውም …ምንም ተስፋ የለውም"* ካሉት ውስጥ፣ ወደ ፊት በጎ ነገር እንደሚወጣበት የማየት ችሎታ አላቸው። እንዲህ ዓይነት የተፈጥሮ ችሎታ ያላቸው፣ ትክክል የሆኑ ውሳኔዎችን ለማስተላለፍ ከባድ አይሆንባቸውም። ሁኔታዎችን ብቻ ሳይሆን በሰው ውስጥ ያለውንም ብቃትና አቅም የማወቅም ችሎታ አላቸው። ከሚያገለግሉት ሕዝብ መካከል፣ ሌሎች "ዋጋ የላቸውም" ብለው ሲንቋቸው፣ እነርሱ ግን ወደ ፊት ጥሩ መንፈሳዊ መሪ እንደሚወጣቸው ያያሉ። አንዳንድ መንፈሳዊ መሪዎች ይህን ዓይነት ችሎታ እንዲኖራቸው የሆነበት ምክንያት "የማስተዳደር" ስጦታ ስላላቸው ይሆን?

## 4. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ውሳኔ ሰጪው ማን ነው?

አንዳንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት በግልጽ አይታይ እንጂ፣ የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪ (መጋቢ) ውሳኔ ለማስተላለፍ ሥልጣን ወይም ኃይል ያለው አይደለም። እንዲህ የሆነበት ምክንያት ምን ይሆን? ስተለይ በኢትዮጵያውያን አብያተ ክርስቲያናት መጋቢው ምንም ያህል የመምራትና የማስተዳደር ችሎታ ወይም ብቃት ያለው ቢሆንም፣ ውሳኔ ለመወሰን ምንም ዓይነት ሥልጣን የለውም። ይህንን አሳብ በመጀመሪያው መጽሐፌ ላይ ምዕራፍ 8 ላይ በሰፊው የተጠቀሰ በመሆኑ ያንን መመልከቱ ይጠቅማል።[41] አብዛኛው አብያተ ክርስቲያናት ለመጋቢው ምንም ዓይነት ሥልጣን የማይሰጡት፣

[41] መለሰ ወጉ፣ የዘመናችን ቤተ ክርስቲያንና አገልጋዮቿ (ክፍል አንድ)



እምባገነን ከሆኑ፣ የአመራርና የአስተዳደር ብቃት ከሌላቸው መሪዎች ራሳቸውን ለመጠበቅ ብለው ነው። በዚህ ምክንያት መንፈሳዊ መሪው (መጋቢው) በአመራር ውስጥ እንዳይታይ ሆኗል። ሥልጣን ኖሮት ማገልገልን ከእምባ ገነንነት ጋራ አንድ አድርገው የሚያዩት ይመስላሉ። መጋቢው ውሳኔ ለመወሰን ሥልጣን ቢሰጠው፣ "እምባገነን ይሆናል" ብለው የሚፈሩ አሉ። ፍርሃታቸው አንድ ሰው ሥልጣን ከተሰጠው "እምባ ገነን ይሆናል" የሚል ይሁን እንጂ ቤተ ክርስቲያንን ከእምባ ገነኖች ማዳን አይችሉም። መጋቢው ሥልጣን ከሌለው፣ እንግዲያውስ ሥልጣን የሚኖረው ማን ይሆናል? በጠቅላላው ሽማግሌዎች ናቸው? የሽማግሌዎች ሰብሳቢው ወይም ሲቀ መንበሩ ይሆን? እነዚህ አሁን የጠቀስናቸው ከሆኑ፣ እነርሱን እምባገነን እንዳይሆኑ የሚከለክላቸው ምንድነው? ስለዚህ ለመጋቢው ሥልጣንን መከልከል፣ ቤተ ክርስቲያንን በአስተዳደር ምክንያት ከሚመጣው ችግር አያድናትም። ይህንን በመፍራት ቤተ ክርስቲያንን በቦርድ ማስተዳደር የሚሞክሩ አብያተ ክርስቲያናት አሉ። ሄነሪ ክሎፕ ልምምዳቸውን ሲናገሩ፤

> *"እኔ መጋቢ ሆኜ በማገለግልበት ቤተ ክርስቲያን የአባሉ ቁጥር 150 ሲሆን፥ ቤተ ክርስቲያኒቱን እንዲያስተዳድሩ የተመረጡት የቦርድ አባሎች 74 ሰዎች ነበሩ"* አሉ።[42]

በዚህ ዓይነት አንድ ዓይነት ውሳኔ ለማስተላለፍ ሰባ አራቱም ሰዎች መሰብሰብ አለባቸው ማለት ነው። ሁኔታው የሚያስቅና የሚያስገርም ነው። በዚህ ዓይነት መጋቢው ዕቅድ አውጥቶ ለመሥራት ቢቸገር፣ ይህን ያህል አይደንቀንም።

ቤተ ክርስቲያናቸው በዲሞክራሲ (Democracy) (በሕዝብ የሚመራ) ከሆነ፣ ማንኛውንም ዓይነት ውሳኔ የሚወስነው ጉባኤው ነው። ምዕመኑ እጅ በማውጣት ወይም በሌላ መንገድ ድምጽ ሰጥቶ፣ ብዙ ሰው የመረጠው ውሳኔ ይጸናል። ድምጽ ከመስጠታቸው በፊት በሁለቱም ወገን ያሉት እነርሱ የሚደግፉትን ውሳኔ ሌሎች እንዲቀበሉት ለማሳመን ከፍተኛ ጥረት ማድረግ አለባቸው። በዚህ መካከል በውሳኔ አሰጣጣቸው ከእነርሱ የተለየ ሀሳብ ያላቸው ሰዎች ቢገኙ፣ እነዚያን ሰዎች መቀየምና መጥላት ይጀምራሉ። በዚህ ምክንያት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተለያዩ ቡድኖች ይፈጠሩና እርስ በርሳቸው መጋጨት፣ ጥርስ መሳበር ይጀምራሉ። ቤተ ክርስቲያን በዲሞክራሲ መመራቷን የሚመርጡ ከሆነ፣ እግዚአብሔር ፈቃዱን እንዲያሳያቸው መጸም፣ መጸለይ አያስፈልጋቸውም። በድምጽ ብልጫ ብቻ ውሳኔያቸውን ያስተላልፋሉ። ቤተ ክርስቲያኒቷ መጋቢ ቢኖራት፣ መጋቢው ከእግዚአብሔር በተቀበለው ራዕይ መሠረት ቤተ ክርስቲያኒቱ የምታድግበትንና የምትታነጽበትን ነገር ለመሥራት ቢነሳ፣ ምዕመኑ ወይም የቤተ ክርስቲ

[42] Klopp, Henry. The Leadership Playbook, Baker Books, Grand Rapids, MI, 2004

ያኒቱ ቦርዱ ድምጽ ሰጥቶበት አብዛኛው ሕዝብ ካልተቀበለው ሀሳቡ ውድቅ ሊሆን እንደሚችል ግልጽ ነው።

ቤተ ክርስቲያን እንደ ቤተሰብ ናት። ቤተሰብም እንደ ቤተ ክርስቲያን በየጊዜው የምታስተላልፈው የራሷ የሆኑ የተለያዩ ውሳኔዎች አሏት። አንድ ቤተሰብ ውስጥ ለምሳሌ ሁለት ወላጆች፣ አራት ልጆች ያሉበት ቤተሰብ፣ "የምንመራው በዲሞክራሲ ነው" በማለት፣ የሚያስተላልፏቸው ውሳኔዎች ሁሉ በድምጽ ብልጫ ቢሆን፣ የልጆቹ ቁጥር ከወላጆቹ ቁጥር ስለሚበልጥ፣ ውሳኔው ሁልጊዜ ልጆቹን የሚደግፍ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ *"ምን ያህል ሰዓት፣ ምን ያህል ቀን ቤታችን ውስጥ ቴሌቪዥን ይከፈት?"* የሚል ጥያቄ ተነስቶ በጉዳዩ ላይ በደንብ ጊዜ ወስደው ከተወያዩበት በኋላ ድምጽ ቢሰጥበት፣ ማን እንደሚያሸንፍ ማወቅ ከባድ አይሆንብንም። ልጆች ገና የዳበረ እዕምሮ ስለሌላቸው፣ ብዙ ሰዓት ቴሌቪዥን ማየት የሚያስከትለውን ጉዳት ስለማያውቁ፣ *"ጓደኞቻችን እንዳይነኩ፣ በፈለግነው ጊዜ ማየት እንድንችል የጊዜ ገደብ አይኑር"* የሚል ውሳኔ ማስተላለፋቸው እንደማይቀር እርግጠኞች ነን። ቤተ ክርስቲያንም እንደ ቤተሰብ ከሆነች፣ የበሰሉ ብቻ ሳይሆን፣ ብዙ በመንፈሳዊውም ሆነ በእዕምሮ ያልበሰሉ ክርስቲያኖችም ሊኖሩ እንደሚችሉ የታወቀ ነው። ለምሳሌ በአብዛኛው ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች የሚመረጡት በምዕመናን ነው። የድምጽ ብልጫ ያገኙ ሰዎች ሽማግሌ ሆነው ይመረጣሉ። እንደ ፖለቲካው ውድድር "እኔን ምረጡኝ" እያሉ በግልጽ ጥያቄያቸው ባያቀርቡም፣ በተዘዋዋሪ መራጮችን የሚቀሰቅሱ እንደሚኖሩ የታወቀ ነው። አንድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በተለይ አንድ ሰው ሁልጊዜ ሽማግሌ ሆኖ ይመረጣል። ምክንያቱ ምንድ ነው? ብዬ ስጠይቅ፣ ሚስቱ "ካምፔን (የመራጭ ቅስቀሳ) እያደረገች ነው" አሉኝ። ጥያቄዬ በመቀጠል "ቅስቀሳ የምታደርገው እንዴት ነው?" ብዬ ስጠይቅ፣ "ምዕመናኑን ሁሉ በመዳፏ ሥር አድርጋለች፤ ሠርግ ቢኖር ደጋሿ እርሷ ነች... ሀዘን (ለቅሶ) ቢኖር ምግብ አቅራቢዋ፣ አሳላፊዋ እርሷ ነች... እርሷ የማትደርስበት፣ እርሷ የማትነካው ነገር የለም" አሉኝ። እንግዲህ በግል ቤታችን ውስጥ በምንወስነው ውሳኔ፣ ልጆቻችን እንዲመርጡ የማናደርግ ከሆነ፣ በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ገና ያላደጉትን፣ ቤተ ክርስቲያን እንዴት መመራት እንዳለባት የማያውቁትን ምዕመናን "ቤተ ክርስቲያንን የሚመሩ ሽማግሌዎችን እንዴት ምረጡ እንላቸዋለን?" ይሄ በግሌ ጥያቄ ይሆንብኛል። እንግዲያውስ ሽማግሌዎችን መምረጥ ያለበት ማን ነው? ስለዚህ ሀሳብ በመጀመሪያው መጽሐፌ ላይ የጠቀስኩት ስለሆነ፣ በዚህ ነጥብ ላይ እሳቤን እዚሁ ላይ እቋጫለሁ።

ብዙ አብያተ ክርስቲያናት በዲሞክራሲ (Democracy) ወይም በምዕመናን ጉባኤ የሚመሩ ነው። ይህን ዓይነቱን አመራር መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንደሆነ አድርገው የተቀበሉት ይመስላል። በዓለሙ ፖለቲክ ውስጥ አንደኛው ክፍል ከመጠን በላይ ሥልጣን እንዳይዝ መቆጣጠር የሚቻልበት ዘዴ ወይም ብልሃት (Check & Balance) ተቀይሯል። ብዙሃኑ (አብላጫው) ይግዛ (Majority rule) የሚለው እሳቤ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንደሆነ አድርጎ በመቀበል፣ ይህንን የአመራር ሥልት ቤተ ክርስቲያን እንድትመራበት ማድረግ ትክክል ነው ወይ? የብሉይንም ሆነ የአዲስ ኪዳንን ታሪክ ስናነብ ብዙ ጊዜ ብዙሃኑ ስሁተት ላይ ይወድቅ እንደነበረ እናስታውሳለን። በድምጽ ብልጫ ቢሆን ኖሮ፣ ለመሆኑ እስራኤላውያን ከግብጽ ባርነት ነጻ መሆን ይችሉ ነበር? ከወጡም በኋላ ብዙ ጊዜ ወደ መጡበት ወደ ግብጽ ለመመለስ የመረጡበት ጊዜ እንደነበረ ታሪካቸውን እናነባለን። ሙሴና አሮን የሕዝቡን ድምጽ በመቀበል ፈንታ በውሳኔያቸው ጸንተው በመቆም ሕዝቡን እግዚአብሔር ከወሰነላቸው ሥፍራ ያደረሱ መሆናቸውን እናውቃለን። የአዲስ ኪዳን ታሪክም ከዚህ የተለየ አልነበረም።



## 5. የውሳኔ ዓይነቶች

መንፈሳዊ መሪዎች ካለባቸው ኃላፊነት ወይም ተግባራት ውስጥ አንደኛው፣ ለተለያዩ ነገሮች ውሳኔ መስጠት እንደሆነ ቀደም ሲል ገልጸናል። የአገልግሎቱ ዕድገትም ሆነ ወደ ኋላ መቅረት ምክንያት ከሚሆኑት ነገሮችም መካከል መሪው የሚሰጠው ወይም የሚያስተላልፈው ውሳኔ ነው። ቻርለስ ኤች. ሞረስ ስለ ክርስቲያን መሪ በጻፉት መጽሐፋቸው ላይ ሦስት የውሳኔ ዓይነቶችን ጠቅሰዋል።

- *1ኛ/ መደበኛ ወይም ተደጋጋሚ የሆነ ውሳኔ (Routine) – መንፈሳዊ መሪ፣ ተደጋጋሚ ወይም መደበኛ የሆነ ውሳኔ የሚያስተላልፍበት ጊዜ አለ። ተደጋግሞ የሚመጣ በመሆኑ፣ ይህን ዓይነቱን ውሳኔ ለማስተላለፍ ለመሪው ይህን ያህል ከባድ አይሆንበትም። ለምሳሌ፣ ለድርጅቱ የሚያስፈልገውን ዕቃ ለመግዛት፣ የተለመደውን የአምልኮት ፕሮግራም ማካሄድ፣ ወዘተ. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሚወስኑት ውሳኔዎች ናቸው። እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉትን ውሳኔዎች መወሰን ከባድ አይደለም።*
- *2ኛ/ በአስቸጋሪ (በአስጊ) ሁኔታ ወቅት የሚወሰኑ ውሳኔዎች (Crisis) – ሳይታሰቡ ድንገት የሚመጡ ወይም የሚፈጠሩ አሳሳቢ ሁኔታዎች ላይ፣ አስቸኳይ የሆነ ውሳኔ የሚያስፈልግበት ጊዜ አለ። ያልተጠበቁ አሳሳቢ ሁኔታዎች ሁል ጊዜ ስለሚፈጠሩ፣ የመሪውን ጊዜ የሚሻሙ ቢሆኑም፣ ፈጣን የሆነ ውሳኔ የሚያስፈልጋቸው ናቸው።*
- *3ኛ/ የፈጠራ ችሎታን የሚጠይቁ ውሳኔዎች (Creative) – ...እንዲሁ እንደ ድንገት ሳይታሰቡ የሚሆኑ ሳይሆኑ በአንዳንድ ሁኔታዎች ምክንያት የሚፈጠሩ ሁኔታዎች አሉ። መሪው ራሱ የፈጠራቸው በመሆናቸው፣ ውሳኔ ሊሰጥባቸው ይገባል። ለምሳሌ አዲስ ፕሮግራም (አገልግሎት) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መጀ*

*መር፣ የመንታቂያ ፕሮግራም ማዘጋጀት፣ ምዕመኑን ለአገልግሎት ማዘጋጀት ወዘተ. ሊሆን ይችላል። ለእንደነዚህ ዓይነቶቹ ውሳኔ ለማስተላለፍ መሪው እነዚህን ሦስት ጥያቄዎች መጠየቅ አለበት። ይኸውም፤ 1ኛ፥ ለዚህ ዓይነቱ ነገር ውሳኔ መስጠት ኃላፊነት ያለበት ማን ነው? 2ኛ፥ ውሳኔ ያስፈለገበት ምክንያት ጉዳዩ ምን ያህል አስፈላጊ ቢሆን ነው? 3ኛ፥ ሊደረግ የታሰበው ነገር ምን ያህል አስቸኳይ ነው? ወይም ውሳኔው በተግባር ላይ ከመዋሉ በፊት ምን ያህል ጊዜ አለ?... ለእነዚህ ሦስት ጥያቄዎች የሚያገኘው መልስ፣ የውሳኔውን ዓይነት ይገልጻል።*[43]

መንፈሳዊ መሪዎች ውሳኔ ለመወሰን እንዲያመነቱ ከሚያደርጋቸው ልዩ ልዩ ምክንያቶች መካከል አንደኛው፣ ኃላፊነትን ወይም ተጠያቂነትን፣ እንዲሁም ጉዳት ያመጣ ይሆን? ብለው በለሚያስቡ እንደሆን ግልጽ ነው።

## 5.1. ውሳኔ መወሰን፥ በመሪው ላይ ሊያደርስበት የሚችሉ ችግሮች

- ***በውሳኔ አሰጣጡ ሊሳሳት ይችላል፤*** ...ትንሽም ሆነ ትልቅ ውሳኔ መወሰን ኃላፊነትና ተጠያቂነት ያለበት ነው። መሪው ትክክለኛ ያልሆነ ውሳኔ በመወሰኑ በራሱ ላይ ብቻ ሳይሆን በሌላውም ሰው ላይ ሊደርስ የሚችል ጉዳት አለ። በቂ መረጃ ሳያገኝ፣ ቸኩሎ የሚወስነው ውሳኔ ከስሁተት ላይ ሊጥለው ይችላል።
- ***ፈሪ ሊያደርገው ይችላል፤*** ...ውሳኔ ለመወሰን ትልቅ ድፍረትን ይጠይቃል። በሥሩ ያሉት ሰዎች አንድ ነገር ከማድረጋቸው በፊት የመሪውን ውሳኔ ይጠብቃሉ። የሚሰጠው ውሳኔ የብዙዎችን ሕይወት በጥሩም ሆነ በመጥፎ ሊነካ በለሚችል መሪው ሊፈራ ይችላል። መሪው ደፋርና ቆራጥ ካልሆነ፣ ወቅታዊ የሆነ ውሳኔ ለመወሰን ይፈራል።
- ***መጠላትን ሊያመጣበት ይችላል፤*** ...ማንኛውም ውሳኔ ሁሉንም ሰው ላያስደሰት እንደሚችል የታወቀ ነው። ውሳኔው እነርሱ በሚፈልጉት ሁኔታ ላይ ከሆነ ደስ የሚላቸው ይኖራሉ። እንዲሁም ውሳኔው እነርሱ እንደሚፈልጉት ያልሆነላቸው ደግሞ ቅር ይሰኙበታል። በለዚህ መሪው በሚወስናቸው ውሳኔዎች ሁሉንም እኩል ማስደሰት በለማይችል፣ በአንዳንድ ሰዎች ዘንድ መጠላት ሊደርስበት እንደሚችል የታወቀ ነው።
- ***ብቸኛ ሊያደርገው ይችላል፤*** ...ውሳኔ የሚወሰነው ሰው፣ በሚወሰነው ውሳኔ ምክንያት ውሳኔው ያላስደሰታቸው ሰዎች ስለሚሸሹት ብቸኛ መሆን ይችላል።

[43] Morris, H. Charles. The Christian Leader: Leadership Role, Baptist Theological Seminary, Penang, Malysia.



- ***ተጠያቂ ያደርገዋል፤*** ...መሪ በወሰነው ውሳኔ ላይ ጸንቶ መቆም አለበት። ውሳኔው ትክክል ባይሆን፣ ሊያስተካክለው ወይም ሊለውጠው የሚችለው እርሱ ብቻ ነው። የውሳኔው ውጤት እንደተጠበቀው ጥሩ ባይሆን፣ ከተጠያቂነት ነጻ መሆን እንደማይችል ማወቅ አለበት።
- ***በውሳኔ አሰጣጡ የሚያመነታ ሊያደርገው ይችላል፥*** ...መሪ በውሳኔው ምክንያት የሚደርሰውን ጉዳት በማሰብ መወሰን የሚቸገርበት ጊዜ አለ። ስሁተትን በመፍራት ውሳኔ አለማድረግ መሪውን በውሳኔ አሰጣጡ አመንቺ ሊያደርገው ይችላል።

መንፈሳዊ መሪን በአመራሩ ፍሬያማ እንዳይሆን ምክንያት ከሚሆኑበት ነገሮች መካከል አንደኛው በውሳኔ አሰጣጡ የሚያመነታ ሲሆን፣ ወይም ፈጣን የሆነ ውሳኔ መወሰን ሲያቅተው እንደሆነ ካላይ ተመልክተናል። ብዙ መንፈሳዊ አገልግሎቶች ለማደግ ዕንቅፋት ከሚሆኑባቸው ምክንያቶች መካከል አንደኛውና ትልቁ፣ መሪው በውሳኔ አሰጣጡ የሚያመነታ በመሆኑ ነው። መሪው ማስተዋል ያለበት ነገር ቢኖር፣ የውሳኔ ሰው ለመሆን ቀላል ወይም አቋራጭ መንገድ የሌለ መሆኑን ነው።

## 5.2. መሪዎች በውሳኔ አሰጣጣቸው የሚያመነቱበት ምክንያት

- ***ሰውን ለማስደሰት መፈለግ፦*** በአመራር ውስጥ ሰውን ሁሉ ለማስደሰት ዋና ዓላማ ማድረግ፣ ውሳኔ አሰጣጥን በንካላ ያደርጋል። አንዳንድ መንፈሳዊ መሪዎች፣ ውሳኔያቸው ሰዎችን ቅር የሚያሰኝ ከመሰላቸው፣ ውሳኔ ለመወሰን ይቸገራሉ። መንፈሳዊ መሪዎች አንዳንድ ጊዜ ሰዎች የማይወዱትን ዓይነት ውሳኔ መወሰናቸው ስለማይቀር፣ "የምሰጠው ውሳኔ ሰዎችን ቅር ያሰኝ ይሆን?" በማለት ማሰብና መጨነቅ የለባቸውም። ልጆቹን የሚጠቅም መሆኑን የተረዳ አባት፥ የሚወስነው ውሳኔ ልጆቹን ባያስደስታቸውም፣ በውሳኔው መጽናት እንዳለበት ሁሉ፣ መንፈሳዊ መሪም ውሳኔው እግዚአብሔርን የሚያከብርና የሚያስደስት እንዲሁም የሚያገለግለውን ሕዝብ የሚጠቅም ከሆነ፥ "ሰዎች ይቀየሙኝ ይሆናል" ወይም "ይጠሉኝ ይሆናል" ብሎ በመፍራት ብቻ በውሳኔ አሰጣጡ ማመንታት የለበትም። መንፈሳዊ መሪዎች በውሳኔ አሰጣጣቸው የሚያመነቱ ከሆነ፥ የሚያገለግሉትን ሕዝብና እንዲሁም አገልግሎታቸውን የሚጎዱ መሆናቸውን ማወቅ አለባቸው።
- ***ግጭትን መፍራት፦*** "ውሳኔያችን ከበው ጋር ያጋጨን ይሆን?" ብለው የሚፈሩ መሪዎች፣ እነርሱ ራሳቸው መወሰን ሲገባቸው፣ ኃላፊነቱን ለሌሎች አሳልፈው ይሰጣሉ። "ውሳኔው ትክክል ነው ወይስ ትክክል አይደለም?" በሚለው አሳብ የሚፈጠረውን ውስጣዊ ግጭት መስመር ማስያዝ (ማስታረቅ) አለመቻል፣ ውሳኔ የመወሰን ጉልበትን ያሳጣል። ልክ እንደዚሁ በተወሰነው ውሳኔ ምክንያት

የሚደርሰውን ጥሩም ሆነ መጥፎ ውጤት ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆን አሁንም የመወሰን ችሎታን ደካማ ያደርጋል።

- *የማመዛዘን ችሎታ ማነስ፦* ...ውሳኔ ለመወሰን ከቀረቡት ወይም ካሉት ምርጫዎች ውስጥ ጠቃሚውንና ጎጂውን የማመዛዘን ችሎታ ማነስ፣ ውሳኔን የሚጎትት መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ምንም ዓይነት ውሳኔ በጊዜው መወሰን እንዳይቻል ያደርጋል።
- *ስህተትን መፍራት፦* ቢሳሳቱ ዓለም በእነርሱ ላይ የተደፋባቸው መስሎ የሚሰማቸው አንዳንድ ሰዎች አሉ። "ፍጹምነትን" ከራስ መጠበቅ ያለመብሰል ምልክት እንደሆነ ምሁራን ይገልጻሉ። ሰው በተፈጥሮው "ፍጹምነት" ያለው ስላልሆነ፣ ኃላፊነት ውስዶ ከሠራ፣ በሚሠራው ሥራ ውስጥ ስህተት ሊገኝበት እንደሚችል መረዳት፣ ውሳኔ ለመወሰን ከመፍራት ይጠብቀዋል። "እሳሳት ይሆናል" የሚል ፍርሃት ያለው መሪ፣ ኃላፊነቱን እንደሚገባው መወጣት አይችልም።
- *በራስ ችሎታ እምነት ማጣት፦* ውሳኔ ለመወሰን ሁልጊዜ በሌላው ሰው የሚደገፍ ወይም ሁልጊዜ ሌላ ሰው የሚወስንለት ከሆነ፣ የራሱን ውሳኔ ለማስተላለፍ ድፍረት ያጣል። የዚህ ትልቁ ምክንያት የችሎታ ማነስ ነው። በተለይ ከዚህ በፊት በውሳኔ አሰጣጡ ተሳስቶ ከሆነ፣ ደግሜ እሳሳት ይሆናል ብሎ በመፍራት ውሳኔ ለመወሰን ይቸገራል።

መንፈሳዊ መሪ ጊዜውን የጠበቀና እንዲሁም ጥንቃቄ የሞላበት ውሳኔ መወሰን ሲችል፣ አገልግሎቱ ፍሬያማ ይሆናል። አርቆ የሚያስብ መሪ ውሳኔ ለመስጠት አያመነታም። ስሜቱን ብቻ ተከትሎ የሚሄድ መሪ ለመወሰን ይቸኩላል፤ ጥሩ መሪ ግን ከውሳኔው በፊት ሁኔታዎችን በጥንቃቄ ይመዝናል። የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን ካረጋገጠ፣ የሚያስከትለውን ሳይፈራ ውሳኔ ያደርጋል። ውሳኔው በዓላማና በግብ ላይ የተመሠረተ ስለሆነ፣ በመካከሉ ይሆናሉ ብሎ ያልጠበቃቸው አንዳንድ እንቅፋቶች ቢያጋጥሙት ወደ ፊት ይገፋል እንጂ ከሁኔታው የሚወጣበትን (የሚሸሽበትን) መንገድና ዘዴ አይፈልግም። እውነተኛ መንፈሳዊ መሪ የውሳኔው ውጤት እንደጠበቀው ሆኖ ባያገኘው፣ ሌሎችን ምክንያት በማድረግ ከተጠያቂነት ራሱን ነጻ ለማድረግ አይሞክርም።

## 5.3. ኢየሱስ ውሳኔ የሚሰጠው እንዴት ነበር?

ፓትሪክ ሞርሊ የተባሉ ጸሐፊ፣ በምድራዊ አገልግሎቱ ኢየሱስ እንዴት ውሳኔ ይሰጥ እንደነበረ ለማስረዳት በማቴዎስ ወንጌል 4፥1-11 ያለውን ክፍል መሠረት በማድረግ፣ ሰይጣን ያቀረበለትን ፈተና ለማሸነፍ ኢየሱስ የወሰዳቸውን እርምጃዎች



ጠቅሰዋል።[44] ኢየሱስ በሦስት ዓመት ተኩል የአገልግሎት ዘመኑ ብዙ ውሳኔዎችን አስተላልፏል። ውሳኔ አሰጣጡ በቅርብ የሚከተሉትን ብቻ ሳይሆን፣ ተቃዋሚዎቹን፣ በተንኮል ሊያጠምዱት የሚፈልጉትን ሁሉ ያስደንቃቸው ነበር። ተቃዋሚዎቹ አንድ ጊዜ በእርሱ ላይ ተቃውሞ ለማስነሳት አስበው "ለቄሳር ቀረጥ መክፈል ተገቢ ነው ወይ?" ብለው ሲጠይቁት የሰጣቸውን መልስ እናስታውሳለን። የሰጠው መልስ እኛን ብቻ ሳይሆን፣ ጠላቶቹንም አስደንቋቸዋል።

ኢየሱስ ምድራዊ አገልግሎቱን ከመጀመሩ በፊት ሰይጣን ወደ በረሃ ውስዶ በፈተነው ወቅት፣ ሦስት ዓይነት ውሳኔዎችን እንዳስተላለፈ እናውቃለን። ኢየሱስ 40 ቀን ጾሞ በጣም መራቡን ያውቅ ነበር። ይህንን መልካም አጋጣሚ በመጠቀም ሰይጣን የኢየሱስን አቅጣጫ ለማስቀየር መጣ። የኢየሱስን ውሳኔ ለማስቀየር ሰይጣን ያደረገው ነገር፣ የወሰደው እርምጃ፣ የተጠቀመባቸው ቋንቋዎች በጣም የሚያስደንቁና ኃይለኞች ነበሩ። ኢየሱስ ሰይጣን ሲፈትነው ልክ ያልሆነ ውሳኔ ቢወስን ኖሮ ምን ዓይነት አደጋ ሊያስከትል እንደሚችል ተገንዝበን ይሆን? ሰይጣን ውሳኔውን ቢያስለውጠው ኖሮ፣ ኢየሱስ እንደ እኔና እንደ እናንተ ኃጢአተኛ ሰው ይሆን ነበር። ኃጢአታችንን የሚያስተሰርይልን እንከን የሌለበት "የእግዚአብሔር በግ" መሆን አይችልም ነበር። እኛም ለኃጢአት ፈተና እጁን የሚሰጥ፣ ሰይጣንን ለማሸነፍ አቅም የሌለው መሲህ ስለማንፈልግ፣ የግድ ሌላ መሲህ እንጠብቅ ነበር። ደስ የሚለን ኢየሱስ ትክክለኛ ውሳኔ በመወሰን ሰይጣንን ድል ያደረገ መሆኑ ነው። እንዲህ ባይሆን ኖሮ፣ *"ከድካማችን የማይራራልን ሊቀ ካህናት የለንምና፤ ነገር ግን እንደ እኛ በማንኛውም ነገር የተፈተነ ሊቀ ካህናት አለን። ይሁን እንጂ ምንም ኃጢአት አልሠራም"* (ዕብ. 4፥15) ብለን ማለት አንችልም ነበር። መንፈሳዊ መሪ ከኢየሱስ ውሳኔ አሰጣጥ ሰፊ ትምህርትም ሆነ መመሪያ ማግኘት ፈቃደኛ መሆን አለበት። ኢየሱስ በሰይጣን በተፈተነበት ወቅት የቀረቡለትን ፈተናዎች ለመወጣት የወሰዳቸው እርምጃዎች (ውሳኔዎች) ምን ዓይነት ነበሩ?

### (ሀ) ውሳኔው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነበር

ሰይጣን የመጀመሪያውን ፈተና ሲያቀርብለት፣ በመጀመሪያዎቹ ሰዎች፣ ማለትም በአዳምና በሔዋን ላይ የተጠቀመበትን ዘዴ (መንገድ) በሁለተኛውም ሰው (ኢየሱስ) ላይ በመጠቀም እንደሆነ እናያለን። እርባ ቀን መራቡን ያወቀው ሰይጣን፣ ኢየሱስን በምግብ አባብሎ ሊጥለው ሞክሮ ነበር። *"የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ እነዚህን ድንጋዮች እንጀራ እንዲሆኑ እዘዝ"* አለው። ኢየሱስ ለሰይጣን የሰጠው መልስ፣ ማንኛውም አማኝም ሆነ መንፈሳዊ መሪ ለውሳኔ አሰጣጡ እንደ "መመሪያ" አድርጎ ሊይዘው ይገባል። ይህም

[44] Patrick M. Morley. The Man In The Mirror, Wolgemuth & Hyatt, Publishers, Brentwood, TN. 1989.

"ተጽፏል" የሚለው አሳብ ነው። ኢየሱስ ለሰይጣን *"ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣው ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም ተብሎ ተጽፎአል"* የሚል መልስ ሰጠው (ማቴ. 4፥4)። መንፈሳዊ መሪ በግል ሕይወቱም ሆነ የሚመራውን ሕዝብ በሚመለከት ጉዳይ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆኑን፣ ወይም መጽሐፍ ቅዱስን የማይቃረን መሆኑን እርግጠኛ መሆን አለበት። ውሳኔው ምንም ያህል ጥሩ ውጤት የሚያመጣ ቢመስልም፣ የውሳኔው ውጤት መጽሐፍ ቅዱስን የሚቃረን ከሆነ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ መሆኑን ማወቅ አለበት።

### (ለ) ውሳኔው እግዚአብሔርን ፈታኝ አልነበረም

ሁለተኛው ውሳኔ፣ ከከተማ ጫፍ ላይ ሆኖ ራስን ወደ መሬት በመወርወር ላይ ያረፈ ነበር። ሰይጣን *"የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ ራስህን ወደ መሬት ወርውር'* ለሚለው ሀሳብ ኢየሱስ መልስ ለመስጠት ነበር። ይህንን ዓይነቱን ፈተና የዘረጋው የራሱንና የእግዚአብሔርን ኃይል ለመፈተን ነበር። መንፈሳዊ መሪ ራሱንም ሆነ የሚመራውን ሕዝብ ችግር ውስጥ ከትቶ እግዚአብሔር ፈጥኖ ደራሽ መሆኑን መፈተን ትክክል እንዳልሆነ መረዳት አለበት። ሰይጣን ይህንን ፈተና ለኢየሱስ ሲያቀርብለት የእግዚአብሔርን ቃል ጠቅሶ ነው። *"...እግርህ በድንጋይ እንዳይሰናከል፣ በእጃቸው ያነሡህ ዘንድ፣ መላእክቱን ስለ አንተ ያዝዝላል...ተብሎ ተጽፎአልና..."* አለው (የማቴ. 4፥6)። መንፈሳዊ መሪ ለውሳኔ አሰጣጡ እንደ ሁለተኛ መመሪያ አድርጎ መያዝ ያለበት፣ *ተአምር በመጠበቅ፣ እግዚአብሔርን አጣብቂኝ (ፈታኝ) የሆነ ነገር ውስጥ መክተት እንደሌለበት ነው።* ሰይጣን እነዚህን ሁለት ፈተናዎች ሲያቀርብ ለኢየሱስ ያሰበ መሰሎ እንደሆነ መዘንጋት የለብንም።

### (ሐ) ውሳኔው እግዚአብሔርን የሚያከብር ነበር

ሦስተኛው ውሳኔ፥ ለሰይጣን መስገድን በሚመለከት ነጥብ ላይ ነበር። *"...ዲያብሎስ ኢየሱስን እጅግ ከፍ ወዳለ ተራራ አወጣው፤ የዓለምንም መንግሥታት ክብራቸው አሳየውና፣ 'ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ'* አለው" (ማቴ. 4፥9)። ኢየሱስ በቀረበለት በሦስተኛው ፈተናም አልተሸነፈም። ኢየሱስ ሰይጣንን *"...አንተ ሰይጣን ከፊቴ ራቅ! ለአምላክህ ለእግዚአብሔር ስገድ፤ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፎአልና"* አለው (ማቴ. 4፥10)። መንፈሳዊ መሪ በየጊዜው የሚፈተንባቸው የራሱ የሆኑ የተለያዩ ፈተናዎች ይቀርቡለታል። ገንዘብ... ዝና... ሹመት ወዘተ. በውሳኔው ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ሊያሳድሩበት ይችላሉ። *መንፈሳዊ መሪ ለውሳኔ አሰጣጡ እንደ ሦስተኛ መመሪያ አድርጎ መያዝ ያለበት፣ እግዚአብሔርን የማያከብርና የማያስከብር ምንም ዓይነት ውሳኔ መወሰን እንደሌለበት ነው።* እነዚህን ሦስት እውነቶች በውሳኔ አሰጣጣችን እንዲረዱን እነዚህን ሦስት እውነቶች እንደ መመሪያ አድርገን ልንጠቀምባቸው ይገባል።



## 6. መንፈሳዊ መሪዎች ውሳኔ ከመወሰናቸው በፊት ማድረግ ያለባቸው

መንፈሳዊ መሪ የሚወስነው ውሳኔ፣ ራሱን ብቻ ሳይሆን፣ በቤተ ክርስቲያንና በብዙዎች ሰዎች ሕይወት ውስጥ ተጽዕኖ ወይም ጉዳት ሊያደርስ ስለሚችል፣ በውሳኔ አሰጣጡ እንዲረዳው መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ መመሪያ ሊኖረው ይገባዋል። መንፈሳዊ መሪ በውሳኔ አሰጣጡ ራሱን ከስህተት ለመጠበቅ፥

### 6.1. የመንፈስ ቅዱስ ምሪትን መፈለግ አለበት

መንፈሳዊ መሪ አንድ ውሳኔ ለመወሰን፣ የሚደገፍባቸው ሁለት ዓይነት ምርጫዎች ይኖሩታል። አንደኛው በራሱ ግንዛቤ (ማስተዋል) መደገፍ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ በውሳኔ አሰጣጡ የእግዚአብሔርን ጥበብ መፈለግ ነው። ብዙ ጊዜ ሰዎች እግዚአብሔር እንደሚያስበው በለማያስቡ የሚመርጡት ሰው የሚከተለውን መንገድ ነው። ዓለማዊ የሆነ መሪ በውሳኔ አሰጣጡ የሰውን መመሪያና ሀሳብ የሚከተል በመሆኑ፣ ይጠቅማሉ ብሎ የገመታቸውን መረጃዎች ሁሉ ሰብስቦ፣ ጉዳቱንና ጥቅሙን ካመዛዘነ በኋላ የተሻለ መስሎ የተሰማውን ውሳኔ ይወስናል። መንፈሳዊ መሪ በዚህ ዓይነት መንገድ የሚወሰን ከሆነ፣ የሚመራውን ሕዝብ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ ሊወስደው እንደሚችል የታወቀ ነው። ሰሎሞን *"ለሰው ቀና መስሎ የሚታይ መንገድ አለ፤ በመጨረሻ ግን ወደ ሞት ያደርሳል"* ይላል (ምሳሌ 14፥12)። መንፈሳዊ መሪዎች በራሳቸው ጥበብና ማስተዋል ብቻ ተደግፈው፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሳይጠይቁና ሳይመረምሩ ጥሩ መስሎ የታያቸውን ውሳኔ እንዲያደርጉ እግዚአብሔር አይፈልግም። ምክንያቱም የሰው ማመዛዘንና የአዕምሮ ችሎታ ምንም ያህል ትልቅ ቢሆን፣ ትክክለኛውን የመለየት ችሎታው በጣም የተወሰነ በመሆኑ ነው። የእርሱን ፈቃድ ከልባቸው ለሚፈልጉ መንፈሳዊ መሪዎች በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት እግዚአብሔር መልካም የሆነውን ይገልጽላቸዋል። መንፈስ ቅዱስ ምሪትን የሚሰጣቸው እንዴት ነው?

### 1ኛ/ መንፈስ ቅዱስ በጸሎት ውስጥ ምሪትን ይሰጣል

እግዚአብሔር *"ወደ እኔ ጩኽ፤ እኔም እመልስልሃለሁ፤ አንተም የማታውቀውን ታላቅና የማይመረመር ነገር እገልጥልሃለሁ"* (ኤር. 33፥3) የሚል ተስፋ ሰጥቶናል። ጸሎት ስንል፣ የሃይማኖት ሥርዓት ወይም ደንብ ለመፈጸም ሲባል ብቻ የሚደረግ ከው

ስጥ ያልመነጨ ጩኸት አይደለም። መንፈሳዊ መሪ ምንም ዓይነት ውሳኔ ከማስተላለፉ በፊት ሁልጊዜ ጊዜ ወስዶ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በጸሎት መጠየቅ አለበት። መንፈሳዊ መሪዎች ችግር ሲያጋጥማቸው ብቻ ሳይሆን፣ በየቀኑ እግዚአብሔር በውሳኔ አሰጣጣቸው እንዲረዳቸው በፊቱ በጸሎት መውደቅ አለባቸው። ጸሎትን ችላ ማለት፣ *"የእግዚአብሔርን አሳብ ወይም ፍላጎት አውቃለሁ፤" ወይም "ጸሎትን የምጠቀመው የራሴን መንገድ ሁሉ ምክሬ ካልሠራልኝ ብቻ ነው"* ማለት ይመስላል። የእግዚአብሔርን ምሪት በጸሎት መጠየቅ ያለባቸው የቤተ ክርስቲያንና የመንፈሳዊ ድርጅት መሪዎች ብቻ ሳይሆኑ ክርስቲያን ነጋዴዎችም ሆኑ፣ በአገር አመራር ውስጥ ያሉ ባለሥልጣናትም ሊጠቀሙበት ይገባል። የእግዚአብሔር ጥበብና ምሪት የማያስፈልገው ማንም የለም። እግዚአብሔር በውሳኔ አሰጣጣቸው የሚያስከብሩትን ምሪት ለመስጠት ደስ ይለዋል። ጸሎት፣ መንፈሳዊ መሪዎች እግዚአብሔርን ሊያስከብር የሚችለውን ውሳኔ እንዲወስኑ ይመራቸዋል። የሚያሳዝነው፣ መንፈሳዊ መሪዎች ዕለታዊ ተግባራቸውን ለመፈጸም ወደ ላይና ወደ ታች ሲሉ፣ ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኙበት በቂ ጊዜ የሚያጡ መሆናቸው ነው። ዳንኤል በባቢሎን የመንግሥት አስተዳደር ውስጥ ከፍተኛ ኃላፊነት የነበረበት ሰው ቢሆንም፣ ከእግዚአብሔር ጋር በጸሎት መገናኘቱን ችላ አላለም። ዳንኤል እንዳይጸልይ የሚያደርገው ፈተና ቢያጋጥመውም፣ ቀደም ሲል እንደሚያደርገው ጸሎቱን አላቋረጠም ነበር። ታማኝነቱንም የሚያውቅ አምላክ ከአንበሶች አፍ በማዳን በጠላቶቹ ላይ ድልን ሰጠው።

## 2ኛ/ መንፈስ ቅዱስ በቃሉ ውስጥ ምሪትን ይሰጣል

መንፈሳዊ መሪ ምክርም ሆነ አስተያየት ከሰዎች ሲሰጠው፣ የተሰጠውን ምክርም ሆነ አስተያየት ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ማመሳከር አለበት። እንዲሁም በጸሎቱ መካከልም ሆነ በሌላ ጊዜ አዲስ አሳብ ከእግዚአብሔር ያገኘ ሲመስለው፣ ያ አሳብ የእግዚአብሔርን ቃል የማይቃረን መሆኑን መመርመር አለበት። ችግሩ ግን ብዙ መንፈሳዊ መሪዎች የእግዚአብሔርን ቃል እንደሚገባው አለማወቃቸው ነው። የእግዚአብሔር ቃል ምን እንደሚል ካላወቁ፣ በቃሉ ሊመሩ አይችሉም። በየቀኑ ስለማያነቡት፣ አስተሳሰባቸውን ሲለውጥ፣ እንዲሁም መመሪያ ሊሆናቸው አይችልም። ትልቅ ውሳኔ መወሰን በሚኖርባቸው ወቅት፣ በቃሉ መደገፍ ስለማይችሉ፣ የቀረቡላቸውን አማራጭ መንገዶችን ተመልክተው "የተሻለ ነው" ብለው የሚያስቡትን መርጠው ይወስናሉ። እውነተኛ የሆኑ መንፈሳዊ መሪዎች ግን የሚታመኑበት በእግዚአብሔር ቃል ስለሆነ፣ በየጊዜው ልባቸውንና አዕምሯቸውን ወደ ቃሉ ያነሳሉ። መንፈሳዊ መሪዎች አዕምሯቸው በቃሉ ከተሞላ፣ አስተሳሰባቸው፣ ምርጫቸውና ውሳኔያቸው እግዚአብሔርን የሚያከብርና የሚያስከብር ይሆናል። አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሲሆኑ፣ ያልጠበቁት ነገር ሲደርስባቸው፣ መንፈስ ቅዱስ አስፈላጊውን ቃል ወደ አዕምሯቸው ያመጣል። ውሳኔ ለመወሰን ሲዘጋጁ መንፈስ ቅዱስ ከቃሉ ውስጥ ተገቢ የሆነውን መመሪያ ወደ አዕምሯቸው ያመጣል።



## 3ኛ/ መንፈስ ቅዱስ በሌሎች አማኞች አማካኝነት ምሪትን ይሰጣል

ትክክለኛ የሆነውን ምርጫ መምረጥ ባለመቻል ለሰው ሊደርስበት የሚችለውን ጉዳት መጽሐፈ ምሳሌ ይዘረዝራል። መጽሐፈ ምሳሌ ትክክል ያልሆነ ውሳኔ እንዳንወስን ጠቃሚ የሆኑ ምክሮችን ይሰጠናል። ከሚሰጠን ልዩ ልዩ መመሪያዎች መካከል አንደኛው ጠቃሚ የሆነውን ምክር አስተዋይ ከሆኑ ሰዎች እንድንሻ ነው። *"በአመራር ጉድለት መንግሥት ይወድቃል፤ የመካሮች ብዛት ግን ድልን እርግጠኛ ያደርጋል"* ይላል (ምሳሌ 11፥14)። ቀጥሎ *"ምክር ሲጎድል ዕቅድ ይፋለሳል፤ በብዙ አማካሪዎች ግን ይሳካል"* ይላል (ምሳሌ 15፥22)። ጥሩ ምክር ማግኘት፣ መንፈሳዊ መሪዎችን ትክክል ያልሆነ ውሳኔ ከመወሰን ይጠብቃቸዋል። ከሰዎች የሚያገኙት ምክር ሁሉ ጠቃሚ ስላልሆነ፣ አስተዋይ የሆኑ መንፈሳዊ መሪዎች አማካሪዎቻቸውን በጥንቃቄ ይመርጣሉ። መንፈሳዊ መሪ መካሪዎቹ ችሎታ ያላቸው ብቻ ሳይሆኑ፣ ከእግዚአብሔር ጋር የተቀራረበ ግንኙነት ያላቸው፣ የእምነት ሰዎች፣ በመንፈስ ቅዱስ የሚመሩ፣ ታማኞችና ሀቀኞች መሆናቸውን መመርመር አለበት። አስተዋይ የሆኑ አማካሪዎችን ማግኘት፣ መንፈሳዊ መሪዎች ሞኝነት ያለበትን ውሳኔ ከመወሰን ይጠብቃቸዋል።

## 4ኛ/ መንፈስ ቅዱስ በሁኔታዎች (Circumstances) ውስጥ ምሪትን ይሰጣቸዋል

መንፈሳዊ መሪዎች የእግዚአብሔርን አሳብና ፈቃድ የሚያውቁበት መንገዶች አሏቸው። ከላይ እንዳየነው እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት፣ በጸሎት፣ በቃሉ ውስጥ፣ እንዲሁም በአማኞች ሕይወት ውስጥ እንደሚናገረው ሁሉ፣ ከእነርሱ ውጪ በሆኑ በአንዳንድ ሁኔታዎችና እንቅስቃሴዎች ውስጥም ፈቃዱን ይገልጻል። ውሳኔውን እግዚአብሔር የማይደግፈው ከሆነ፣ መንፈሳዊ መሪ ሊወስዳቸው ያሰባቸው እርምጃዎች ሁሉ እንዲጨናገፉ ያደርጋል። ክፍት የመሰሉት በሮች ሁሉ ይዘጋሉ። ይሄን ዓይነት ሁኔታ ሲፈጠር፣ መሪው ተስፋ በመቁረጥ ፈንታ፣ "እግዚአብሔር ምን እየተናገረኝ ነው?" ብሎ ራሱን መጠየቅ አለበት። አስተዋይ መሪዎች በሁኔታዎች መጠቀም ብቻ ሳይሆን፣ ትክክለኛ መሆናቸውን፣ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዳለባቸው፣ የእግዚአብሔርን ቃል የማይቃረን መሆኑን በጥንቃቄ ይመረምራሉ። እውነተኛ የሆኑ መንፈሳዊ መሪዎች የሚያጋጥሟቸው አንዳንድ ሁኔታዎች፣ የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆንናቸውን ወይም አለመሆናቸውን ለይተው እንዲያውቁ መንፈስ ቅዱስ አዕምሯቸውን ብሩህ ያደርጋል።

## 6.2. መንፈሳዊ መሪዎች ከሌሎች ለመማር ፈቃደኞች መሆን አለባቸው

የእግዚአብሔርን ምሪት የሚፈልጉ መንፈሳዊ መሪዎች፣ መንፈስ ቅዱስ ከላይ በገለጽነው ሁኔታ እግዚአብሔር ፈቃዱን ይገልጽላቸዋል። እግዚአብሔር የሚሰጣቸውን ምሪት መከተል የመንፈሳዊ መሪዎች ኃላፊነት ነው። መንፈሳዊ መሪ ትክክለኛ የሆነ ውሳኔ ለመወሰን የሚያስችለው አንደኛው መንገድ፣ መሪው የመማር ፍላጎት ሲኖረው ብቻ ነው። ምክር የሚፈልግ መንፈሳዊ መሪ፣ እርሱ ያልደረሰበትን እውነት ከሌሎች አማኞች ለመማር ፈቃደኛ የማይሆንበት ምክንያት የለውም። መማር የማይፈልጉ መንፈሳዊ መሪዎች፣ በግልጽ "ምክር አንፈልግም" አይሉም። ነገር ግን፣ ሌሎች እንዳይ ናገሩ፣ ወይም አስተያየት እንዳይሰጡ ዕድል በመከልከል ነው። በውይይቱ መካከል አንዳንድ መሪዎች፣ *"እኔ ያቀረብኩትን ሃሳብ የማይደግፍ የሚኖር አይመስለኝም"* ብሎ ውይይቱን ለመደምደም ይሞክራሉ። መሪው ይህን ሲል፣ በተዘዋዋሪ *"እኔ የሰጠሁትን ሐሳብ ማንም ሰው እንዳይቃወም"* ማለቱ እንደሆነ አይረዳም። ሌሎች አስተያየት እንዳይ ሰጡ የሚፈልግ መሪ፣ በውይይቱ ውስጥ ተናጋሪው እርሱ ብቻ ይሆናል። መንፈሳዊ መሪው የውይይቱን ጊዜ ሁሉንም እርሱ ከተጠቀመበት፣ "ማንም ሰው ከእኔ አሳብ ውጪ እንዳይናገር፤ ያልኩትን ሁሉ "አሜን!" ብሎ ይቀበል" የሚል መልዕክት ማስተላለፉ እንደሆነ የሚረዳው አይመስልም። የሌሎችን ተጨማሪ አሳብና አስተያየት መስማት የሚፈልግ መሪ፣ ሌሎች እንዲናገሩ ዕድል ይሰጣል። የውይይቱ ተካፋዮች ጥያቄ ሲሰነ ዝሩ፣ የሚቆጡ፣ ወይም ክርክር የሚከፍቱ መንፈሳዊ መሪዎች ከሌሎች ለመማር ፈቃደ ኞች አለመሆናቸውን ይገልጻል።

## 6.3. በእግዚአብሔር ዘንድ ተጠያቂነት እንዳለባቸው ማወቅ ይገባቸዋል

ዓለማውያን የፖለቲካ መሪዎች ግብረ ገብ የጎደለው ተግባር ቢፈጽሙ፣ የዓለም ጋዜጦች ለሕዝቡ ድርጊታቸውን ገልጸው ያሳያሉ። ስለዚህ በሥልጣን ላይ ያሉት ሁሉ በተቻላቸው መጠን ተጠንቅቀው ይሄዳሉ። በግል ሕይወታቸው ለተው ቢገኙ ገበናቸ ውን ለዓለም ገላልጠው ያሳያሉ። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን የአሜሪካ ፕሬዚደንት የነበ ረው ክሊንተን ነው። ጋዜጠኞችን በመፍራት የፖለቲካ መሪዎች አስፈላጊውን ጥንቃቄ ያደርጋሉ። በግል ሕይወታቸው አንዳንድ ጉድፍ የሚመስል ነገር ያለባቸው ደግሞ የፖ ለቲካ መሪ ለመሆን ደፍረው ውድድር ውስጥ አይገቡም። መንፈሳዊ መሪዎችም በተለይ በአሜሪካን አገር የግል ሕይወታቸው ለጋዜጠኞች የተጋለጠ ነው። እንዲያውም ክርስቲ ያኖች በኃጢአት ሲወድቁ ማጋለጥ ደስ ይላቸዋል። በቅርቡ በዝሙት የወደቁት ታላቅ መንፈሳዊ መሪ የነበሩት ቴድ ሃጋርድ አንዱ ምሳሌ ናቸው። መንፈሳዊ መሪዎች በውሳኔ አሰጣጣቸው "ሁሉን አውቃለሁ... ማንም አይመክረኝም... የፈለግሁትን ለማድረግ መብ



ትና ስልጣን አለኝ፤... ለማንም ተጠያቂ አይደለሁም..." የሚል እምነት በውስጣቸው ሊኖር አይገባም። ጳውሎስ *"...እያንዳንዱ በሥጋው ባደረገው ክፉም ሆነ ደግ ነገር እንደ የሥራው ብድራቱን ለመቀበል ሁላችንም በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት መቅረብ አለ ብን"* ይላል (2 ቆሮ. 5፥10)። ጳውሎስ ይህንን አሳብ ለሮሜ አማኞች በጻፈው መልዕክቱ ላይ እንዲህ ሲል ገልጾታል። *"ታዲያ አንዱ በሌላው ሰው ላይ ለምን ይፈርዳል? አንዱስ ሌላውን ለምን ይንቃል? ሁላችንም እኮ በእግዚአብሔር የፍርድ ወንበር ፊት እንቀር ባለን። ምክንያቱም እኔ ሕያው ነኝ ይላል እግዚአብሔር፣ ሰው ሁሉ በጉልበቱ በእኔ ፊት ይንበረከካል፤ በምላሱም እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ይመሰክራል ተብሎ ተጽፎአል። ስለዚህ እያንዳንዱ ስለ ራሳችን ሥራ በእግዚአብሔር ፊት ቀርበን መልስ እንሰጣለን"* ይላል (ሮሜ 14፥9-12)። እንደ ጳውሎስ አነጋገር በእግዚአብሔር የፍርድ ወንበር ፊት የሚቀር ቡት የማያምኑት ብቻ ሳይሆኑ፣ አማኞችም ተጠያቂነት አለባቸው። ስለዚህ መንፈሳዊ መሪዎች ለሚያደርጉት ድርጊትም ሆነ ለሚወስኑት ውሳኔ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ቀር በው ተጠያቂዎች እንደሚሆኑ ተረድተው በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ ኃላፊነታቸውን መወጣት አለባቸው።

## 6.4. የመንፈሳዊ መሪ "ጽኑ አቋም" (Integrity) ለውሳኔ አሰጣጡ መሠረት ነው

መንፈሳዊ መሪ ጌታን ሲያገለግል፣ ያለው *"ጽኑ አቋም"* ለውሳኔ አሰጣጡ መመሪያ ይሆንለታል። ማንኛውም መንፈሳዊ አገልጋይ *"አሁን የማደርገውን ነገር ለምን አደርጋ ለሁ? ዋናው ምክንያቴ ምንድነው?"* ብሎ ራሱን መጠየቅና መመርመር አለበት። መንፈ ሳዊ መሪ በሚያደርገው ነገር ሁሉ እግዚአብሔርን ማክበርና ማስከበርን ቅድሚያ ሊሰ ጠው ይገባል። በሚያደርገው ነገር ሁሉ እግዚአብሔርን ለማክበር የሚፈልገውን መንፈ ሳዊ መሪ፣ እግዚአብሔርም አመራሩን፣ አገልግሎቱን እንዲሁም የግል ሕይወቱን ይባር ክለታል። ሊመቸውና ደስ ሲለው ብቻ ሳይሆን፤ ሁልጊዜ እግዚአብሔርን በሚያደርገው ነገር ሁሉ ለማክበር የሚሞክረውን መሪ እግዚአብሔርም መለኮታዊ በረከትን ያፈስለ ታል። እግዚአብሔርን የማያስከብር፣ አቋራጭ የሆነ መንገድ መርጦ ቢወስድ፣ በገጸ- ባሕሪው ላይ የኃጢአት ጉድፍ ያለበት መሆኑን መንፈስ ቅዱስ ሲያሳስበውና ሲናገረው የማይታዘዝ መንፈሳዊ መሪ፥ከእግዚአብሔር በረከትን አገኛለሁ ብሎ መጠበቅ የለበትም። ስለዚህ መንፈሳዊ መሪ ውሳኔ በሚወስንበት ጊዜ ሁሉ፣ "ውሳኔዬ እግዚአብሔርን የሚያከ ብር ነው ወይ?" ብሎ ራሱን መጠየቅ አለበት። *"...እኔ የሚያከብሩኝን አከብራለሁ፤ የሚ ንቁኝንም አዋርዳለሁ"* (1 ሳሙ. 2፥30) የሚለውን የጌታን ቃል መዘንጋት የለበትም።

ለምሳሌ አንድ የቤተ ክርስቲያን መጋቢ፣ ለቤተ ክርስቲያን መገልገያ የሚሆን አንድ ዓይነት ዕቃ አዝዞ ቢያስመጣ፣ ያ የታዘዘው ዕቃ ይሆናል ብሎ ያሰበውን ዓይነት ሆኖ ባያገኘው፣ ሻጩን ደውሎ "ዕቃውን እልፈልገውምና ውሰድ" ቢለውና፣ ሻጩም "ያዘዝ

ክኙን አቅርቤልሃለሁና ሂሳቡን መክፈል አለብህ" ቢለውና መጋቢውም "አልከፍልም" ቢል በመካከላቸው ግጭት መፈጠሩ እንደማይቀር ግልጽ ነው። በዚህ ሁኔታ ላይ ሂሳቡን ለመክፈልም ሆነ ላለመክፈል የቤተ ክርስቲያኑ መጋቢ ውሳኔ መወሰን አለበት። ለውሳኔ አሰጣጡ መመሪያ አድርጎ የሚጠቀምበት ምን ሊኖረው ይችላል? "ላልተጠቀምኩበት ዕቃ ላለመክፈል መብቴ ነው" ብሎ መከራከር አለበት ወይስ የለበትም? የቤተ ክርስቲያኑ መጋቢ ፍላጎቱ በማንኛውም ነገር ጌታን ማክበርና ማስከበር ከሆነ፥ *"አልከፍልም ብዬ ብከራከር ቤተ ክርስቲያን ትተቻለች፤ ሁኔታውን የሰሙ ሰዎች ሁሉ በመንፈሳዊ አቋማ ችን ላይ ጥያቄ እንዲኖርባቸው ምክንያት እንሆናለን። በዚህ ምክንያት ምስክርነታችን ይበላሻል፤ ይሄም ጌታን አያስከብረውም፤ እርሱን የማያስከብረው ከሚሆን ገንዘቡን መክፈል አለብን"* በማለት መወሰኑ አይቀርም።

እግዚአብሔር በዓለም ውስጥ እንደ ውድ ዕቃ የሚያየው አንድ ነገር ነው። ያም እንደ ራሱ አድርጎ የፈጠረውን ሰው ነው። እግዚአብሔር የፈጠረውን ሕዝብ የሚያየው እንደ ተራ ዕቃ ሳይሆን፣ እንደ ዓይኑ ብሌን እንደ ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። መንፈሳዊ መሪ ይህንን እውነት ተረድቶ የሚያገለግላቸውንም ሆነ ሌሎችን ሰዎች የሚያያቸው እግዚአብሔር ስሚያያቸው ዓይን ከሆነ፣ የሚሰጠው ውሳኔ ለሰዎች በጎነት መሆኑን አስቀድሞ ይመዝናል። አንድ የንግድ ኮርፖሬሽን መሪ፣ እንደ ዋና ዓላማው አድርጎ የሚይዘው፣ ለአክሲዮኑ ማኅበረተኞቹ (Share Holders) ትልቅ ትርፍ ማስ ገኘት ነው። የሠራተኛው ደስ መሰኘት ለሠራተኛው ጤናማ የሆነ የሥራ ሁኔታ መፍ ጠር፣ ለሠራተኛው ከፍተኛ ደሞዝ ማስገኘት እንዳልሆነ የታወቀ ነው። ኩባንያው ትርፍ እስካስገኘ ድረስ፣ ሠራተኛው ቢመቸው ባይመቸው፣ የሥራው ሁኔታ ቢስማማው ባይስ ማማው ግድ የለውም። ሠራተኛ በመቀነስ አበር ሰው የሚሠራውን ሥራ ሁለት ሰዎች ብቻ እንዲሠሩት በማድረግ የተቀነሱትን ሠራተኞች ከሥራ ቢያባርር፣ ለኩባንያው ትርፍ እስካስገኘ ድረስ ፈጽሞ ግድ የለውም። "ሠራተኞችን ብቀንስ፣ የተቀነሱትም ሠራተኞች ሌላ ሥራ ባያገኙ፣ የእነዚያ ሠራተኞች ቤተሰቦች ምን ይበላሉ? እንዴት መኖር ይች ላሉ?" ብሎ አይጨነቅም። መንፈሳዊ መሪ ግን እንደ ትርፉ የሚያየው የሰዎችን ደህንነ ትንና በጎ ሕይወትን ነው። ይህንን እውነት ያልተረዳ የቤተ ክርስቲያን መሪ ለምዕመናኑ ግድ የሌለው ቢሆን፣ የእግዚአብሔርን ፍላጎት ለማሟላት፣ ፈቃዱን ለመፈጸም የተቀ ሠመጠ እውነተኛ መሪ እንዳልሆነ እናውቃለን። የሕዝቡ ቁጥር እስከ ጨመረ፣ የአስራቱና የምጽዋዕቱ ገቢ እስካደገ ድረስ፣ የሕዝቡ መንፈሳዊ ጉስቁልና፣ እንዲሁም በመንፈሳዊ ረሀብ መንገላታት የማይቆረቁረው ከሆነ፣ ውሳኔው እግዚአብሔርን ቢያከብር፣ ወይም ባያከብር ግድ የለውም። ይሁን እንጂ፣ እግዚአብሔር ራሱ የወደዳቸውን የማይወዱ፣ እግዚአብሔር ራሱ ለተጨነቀላቸው ለምች የማይጨነቁትን፣ እውነተኛ የሆነ የፍቅር ልብ የሌላቸውን፣ ከፍቅሩ የተነሳ አንድ ልጁን መሰዋዕት ላደረገላቸው ሕዝቦች ግድ የሌላቸውን፣ የራሳቸውን ፍላጎትና ፈቃድ ብቻ የሚከተሉትን አንድ ቀን በፍርድ ወንበር ፊት እንደሚያቆማቸውና እንደ ዋጋቸውም እንደሚከፍላቸው የታወቀ ነው።

# ፩ኛ ምዕራፍ ፲፫ ፯ኛ

# ሥልጣንና ኃላፊነት

*"ጌታ ስለ ሰጠን ሥልጣን በጣም ብመካም አላፍርበትም፤*
*ምክንያቱም ይህ ሥልጣን የተሰጠን እናንተን*
*ለማነጽ እንጂ ለማፍረስ አይደለም" ይላል።*
(2 ቆሮ. 10፥8)

እንደ ማንኛውም ዓለማዊ ድርጅትና ማኅበር፣ የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያንም የምትከተለው የራሷ የሆነ የአመራር ስልት አላት። ጥንትም ሆነ በአሁኑ ዘመን፥ በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሚፈጠሩት አንዳንድ ግጭቶችና እንዲሁም በምዕመናን መካከል ለሚሆነው መከፋፈል፣ ቤተ ክርስቲያን የምትከተለው የአመራር ወይም የአስተዳደር ስልት ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳለው የቤተ ክርስቲያን ምሁራን ይናገ ራሉ። በምዕመናን መካከል የሚፈጠረው ግጭትና መለያየት ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት ትልቅ እንቅፋት መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ የመወደቅ ዝንባሌም እንዳለው የታወቀ ነው። ኢየ ሱስ፣ *"አንድ መንግሥት ተከፋፍሎ እርስ በርሱ የሚጋጭ ከሆነ ያ መንግሥት ይወድ ቃል፤ እንዲሁም አንድ ከተማ ወይም አንድ ቤተሰብ እርስ በርሱ ከተለያየ ጸንቶ መኖር ሊቆም አይችልም"* (የማቴ. 12፥25) አለ። ኢየሱስ ይህን ቃል የተናገረው፣ ቤተ ክርስቲያን ህል ውናዋ ተጠብቆ ማደግ እንድትችል፣ አማኞች እርስ በርሳቸው እንደሚገባው መያያዝ እንዳለባቸው ለማሳሰብ ነው። ቤተ ክርስቲያን፣ በክርስቶስ አማካኝነት በእግዚአብሔር አብ የተቤዡ፣ በመንፈስ ቅዱስ አንድ ላይ የተባሉ ሰዎች ኅብረት ነው። ሰዎች በአንድ

ላይ ሲገኙ፣ ለአንድ ዓላማ ሲሰበሰቡ የግድ ትዕዛዝ ሰጪና ትዕዛዝ ተቀባይ፣ መሪና ተመሪ መኖር አለበት። የታወቁት የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁር የሆኑት ዊልያም ባርክሊይ፡

> *"የበላይ የሆነ (ሥልጣን ያለው) ሰው የሌለበት ኅብረት የማይኖር መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ራስን ሥልጣን ላለው ሰው ሳያስገዙ በአንድነት መኖር በጣም አስቸጋሪ ነው። "ሥልጣን" የሌለበት ማኅበረሰብ አንድነቱን ጠብቆ መኖር አይችልም። በአንድ ላይ ለመኖር የኅብረቱ አባላት ሁሉ ራሳቸውን መሪ እንዲሆን ሥልጣን ለተሰጠው ሰው ማስገዛት አለባቸው። ይህ ካልሆነ ግን በአንድ ላይ መኖር አይቻሉም" ሲሉ "በማን ሥልጣን?" (By What Authority)* በሚለው መጽሐፋቸው ላይ ገለጹ።[45]

ቤተ ክርስቲያን እንደ እግዚአብሔር ከተማ፥ እንደ እግዚአብሔር መንግሥት፥ እንደ እግዚአብሔር ቤት የምትታይ ስትሆን፥ በምትከተለው የአስተዳደር ስልት ምክንያት አንዳንድ ጊዜ የምትከፋፈልበት፣ እንዲሁም አንድነቷ የሚደፈርስበት ጊዜ እንዳለ ከላይ ገልጸናል። የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን፥ ያለማቋረጥ የሚዋጋትን የሰይጣን ኃይል መቋቋም ከባድ የሚሆንባት አንደኛውና ትልቁ ምክንያት፣ አማኞች በአንድነት ጠላታቸውን ዲያብሎስን በመቃወም ወይም በመዋጋት ፋንታ እርስ በርሳቸው የሚጋጩ ወይም የሚከፋፈሉ በመሆናቸው እንደሆነ ይታወቃል። ይህንን የተረዳው የቤተ ክርስቲያን ዋና ጠላት የሆነው ሰይጣን፣ በምዕመናን መካከል መለያየትና መከፋፈል እንዲፈጠር ሁል ጊዜ ጠብን ይጭራል። ሰይጣን ራሱ ሥርዓተ አልባ ወይም ከሕግ ውጪ የሚኖር በመሆኑ፥ ሥርዓት የሌለው ሕብረተሰብ እንዲፈጠር፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መከፋፈልን በመፍጠር፣ በአማኞች መካከል የእምነትና የመንፈስ አንድነት እንዳይኖር፣ ሥርዓት ያለውን አስተዳደር ሁልጊዜ መዋጋት ከተፈጥሮ ባሕሪው አንዱ ነው። ሰይጣን የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚቃወምበት አንደኛውና ትልቁ ምክንያት፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት አፍርሶ የራሱን መንግሥትና ሥልጣን ማቆም ስለሚፈልግ ነው። አማኞች ይህንን እውነት ተረድተው ሰይጣን የክርስቶስ አካል የሆነችውን ቤተ ክርስቲያን በመከፋፈል እንዳያዳክም፣ ሁልጊዜ አንድነታቸውን ጠብቀው መኖር ይገባቸዋል።

በሰለጠነውም ሆነ ባልሰለጠነው ዓለም ውስጥ የሚኖር ማንኛውም ቤተሰብ፣ ራሱን በራሱ የማስተዳደር፥ የመምራትና የመቆጣጠር መብትና ነጻነት አለው። አንዱ ቤተሰብ፥ በሌላው ቤተሰብ ላይ የበላይ ለመሆን፣ ወይም ሌላውን ቤተሰብ በቁጥጥሩ ሥር ለማድረግ ምንም ዓይነት ሥልጣንም ሆነ መብት የለውም። ይህም ማለት፥ አንድ ቤተሰብ ለየትኛውም ዓይነት ኃይል ወይም ባለሥልጣን ተጠያቂነት አይኖረውም፣ በሕብረተሰብ ውስጥ እንደፈለገ መሆን ይችላል ማለታችን ሳይሆን፥ ራሱን በራሱ ያስተዳድ

48 William Barclay, By What Authority? (Valley Forge, Pennsylvania: Judson Press, 1974.



ራል፣ ራሱን በገንዘብ ይደግፋል፣ እንዲሁም በመዋለድ ራሱን በራሱ ያባዛል ማለታችን ነው። አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንም ልክ እንደዚሁ የማንም ተጽዕኖ ሳይኖርባት ራሷን በራሷ ታስተዳድራለች፣ ራሷን በገንዘብ ትደግፋለች፣ እንዲሁም ራሷን በራሷ ታባዛለች። ይህንን እውነት ባለመረዳት ወይም ችላ በማለት አንዱ ቤተ ክርስቲያን በሌላው ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ላይ ጣልቃ በመግባት ኃይልና ሥልጣን ለመያዝ ቢሞክር፥ ትልቅ ግጭት እንደሚፈጠር የታወቀ ነው። ማንኛውም አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ካሉት የአስተዳደር ዓይነቶች መካከል የራሱን የአመራር ሥልት መርጦ ለመከተል ሙሉ መብትም ሆነ ነጻነት አለው።

## 1. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ የቤተ ክርስቲያን አመራር

ሥልጣን (authority) ማለት ምን ማለት ነው? *"ኤክሱሲያ" (Exousia)* ከሚለው የግሪክ ቃል የመጣ ሲሆን፥ ቀደም ሲል የያዘው ትርጉም *"ደስ ያለውን የማድረግ ነጻነት"* የሚለውን ነበር። በአሁኑ ጊዜ ግን "ሥልጣን" የሚለው ቃል፥ *"በቅድሚያ እርምጃ የመውሰድ ነጻነት ወይም መብት"* የሚል ትርጉም ይዟል። የመንፈሳዊ መሪ ሥልጣኑን የሚያገኘው መጀመሪያ ከእግዚአብሔር፥ ቀጥሎ ከሚመራቸው ሰዎች ነው። ከተሰጠው ሥልጣን በላይ ማንም ሥልጣን ያለው የለም። መንፈሳዊ መሪ የሚኖረው "ሥልጣን" ከእግዚአብሔር ዙፋን የሚወርድ፥ በፍቅር የተቀመመ ኃይልና ጉልበት ነው። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አባባል "ሥልጣን" (authority)፥ ሰው በሚኖረው ደረጃ ላይ የተመሠረተ ሳይሆን፥ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ከእግዚአብሔር የሚሰጥ የአገልግሎት ቦታ ነው። ሥልጣኑም በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት የሚያገኘው፥ መሪው ባለው ጥሪ፥ በተሰጠው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ፥ እንዲሁም ክርስቲያናዊ ባሕሪ በሕይወቱ ግልጽ ሆኖ ሲታይ ነው። የቤተ ክርስቲያን ራስ ወይም ዋና ኢየሱስ ክርስቶስ ቢሆንም፥ በቤተ ክርስቲያን አካል ውስጥ ከፍተኛ አገልግሎት የሚሰጡ፥ የመሪነት ስጦታ ያላቸው መሪዎች መኖራቸው በጣም አስፈላጊ ነው።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምዕመናኑን ማስታጠቅ ወይም ማዘጋጀት ያለበት አመራር መለማመድ እንዴት ይቻላል? የቤተ ክርስቲያን አካል የሆኑት ምዕመናን ሁሉ ሥጦታቸውን መጠቀም እንዲችሉ የሚያደርጋቸው የአመራር ስልት ይኖር ይሆን? በሥልጣንና በደረጃ የተከፋፈለ የአመራር (የአስተዳደር) ሞዴል፥ (hierarchical model) ሙሉ ኃይልና ሥልጣን የሚኖረው ወይም የሚይዘው መጋቢው ነው። በዚህ ዓይነት የአመራር ሥልት ውስጥ መጋቢው ወሰን የሌለው ሥልጣን ስለሚኖረው፥ መጋቢው ካልፈቀደ ማንም ሰው ምንም ዓይነት ነገር ማድረግ አይቻልም። ትዕዛዝና እንዲሁም ፈቃድ መስጠት የሚችለው መጋቢው ብቻ ነው። እርሱ "ይሁን" ካላለ ምንም ነገር ማድረግ አይቻልም። ቤተ ክርስቲያን ሕያው አካል ያላት ብትሆንም አንዳንዶቹ ድርጅታዊ የሆነ የአመራር ሞዴል የሚከተሉ ናቸው። መጋቢው የሚታየው እንደ ዋና ሥራ

አስኪያጅ ወይም ሥራ አስፈጻሚ ነው። በደረጃ የተከፋፈለ የአመራር (የአስተዳደር) ሞዴል፥ (hierarchical model) የቁጥጥሩ ሥርዓት ከላይ ወደታች ነው። እንደ አለቃ የሚታየው መጋቢ፥ እርሱ ሳያውቅና ሳይፈቅድ ምንም ዓይነት አገልግሎት ሊጀመርና ሊካሄድ አይችልም። እንዲህ የሚሆነው ሰዎችን ቅር የሚያሰኝ ወይም ደስ የማያሰኝ ነገር ይፈጠር ይሆናል በሚል ፍርሃት ነው። በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ባለው እንቅስቃሴ ሁሉ መጋቢው እጁን ማስገባት አለበት። እንዲህ ዓይነቱን አመራር የሚከተል መጋቢ፥ አገልጋይ (አሽከር) ሳይሆን፥ አለቃ ወይም ገዢ ነው።

በደረጃ የተከፋፈለ የአመራር (የአስተዳደር) ሞዴል፥ (hierarcbical model) ተጠያቂነት (accountability) የሚኖረው በደረጃ ከላይ ያለው ሳይሆን፥ እታች ያለው ብቻ ነው። የአመራርና የሥልጣን መዋቅሩ ከላይ ወደ ታች ነው። መሪው ለማንም ተጠያቂነት የለውም ማለት ነው። ስለሆነም፥ የፈለገውን ማድረግ ይችላል። ለምሳሌ "ደሞዝ እንሰኛል" ቢል፥ ለራሱ ደሞዝ መጨመር ይችላል። በዚህ ዓይነት አመራር ሥልት ውስጥ መሪ የሆነ ሰው ቤተ ክርስቲያኑን እንደ ራሱ ንብረት በለሚይዘው አደገኛ ነው። የራሱ ሀብት አድርጎ መያዙ ብቻ ሳይሆን "ቤተ ክርስቲያን እኔ ነኝ" ከማለት ደርጃ በለሚ ደርስ፥ እርሱ "ተናገረ" ማለት ቤተ ክርስቲያን ተናገረች ማለት ነው። ለምሳሌ እግዚአብሔር ራዕይ ሰጥቶኝ "የኢትዮጵያውያን የወንጌል አገልግሎትን" እቋቁሜ እየመራሁ ነው። እምባገነን መሪ ከሆንኩ፥ አገልግሎቱን እንደ ራቤ ንብረት መመልከቴ ብቻ ሳይሆን፥ "የኢትዮጵያውያን የወንጌል አገልግሎት" ማለት *"መለሰ ወጉ ማለት ነው"* ለማለት ይቃጣኝል። በዚህ ዓይነት "አገልጋይ-መሪ" መሆኔ ቀርቶ "እምባገነን አለቃ" መሆኔ ነው። መጋቢው "ቤተ ክርስቲያን እኔ ነኝ" ከማለት ደረጃ ከደረሰ፥ ደስ ያለውን ለማድ ረግ፥ እንደፈለገው ለመወሰን፥ እሱ የተናገረውና የወሰነው የመጨረሻ እንዲሆን መብ ትም ሆነ ሥልጣን ያለው ይመስለዋል። እርሱ የወሰነውን ውሳኔ "አሜን!" ብሎ ከመቀበል በስተቀር መቃወም አይቻልም ይላል። ሙሉ ኃይልና ሥልጣን ስላለው፥ ከእርሱ የተለየ አሳብ የሚያቀርበውን፥ ከአሳቡ ጋር የማይስማማ፥ ወይም የሚቃወመውን የመቅጣት ኃይል እንዳለው ያምናል። እንዲህ ዓይነቱ "ፈላጭ-ቆራጭ" (Authoritarian) መሪ ነው።

"ፈላጭ-ቆራጭ" የሆነ አመራር የሚከተል መሪ፥ ትኩረት የሚሰጠው፥ ሥራው መሠራቱንና፥ ፕሮግራሙ መካሄዱን ብቻ ነው። ለእርሱ ትልቁ ነገር ይኸው ነው። ፕሮግራሙ እስከተካሄደ ድረስ፥ እንዲሠራ የታቀደው ፕሮጀክት እንደታቀደው እስከተከናወነ ድረስ፥ የሰዎች ፍላጎት ቢሟላ፥ ባይሟላ ይህን ያህል ግድ የለውም። የሚፈልገውን ለማግኘት፥ በዙሪያው ያሉትን በሚችለው መንገድ ሁሉ ያግባባቸዋል። አስፈላጊ መስሎ ከታየው ደግሞ፥ "ጌታ ቀብቶ ያስቀመጠኝን በመቃወምህ ጌታ አይባርክህም.... ጌታ ይቀጣሃል..." በማለት ማስፈራራትን ይጠቀማል። ተቃዋሚ የመሰለውን ሁሉ ይነቅፋል፥ ያሳደባል። ሥልጣኑን "አሜን!" ብለው እንዲቀበሉ የተለያየ ዘዴና ብልሃት ይጠቀማል።



## 2. መንፈሳዊ "ሥልጣን" (Spirituai Authority)

በሰው ሕይወት ውስጥ አንዳንድ አስፈላጊ የማይመስሉ፥ ግን በጣም ጠቃም የሆኑ ነገሮች አሉ። ለምሳሌ፥ ልጆች የፈለጉትን እንዲሆኑ፥ ደስ ያላቸውን ሁሉ ማድረግ እንዲችሉ፥ ከበላይ ሆኖ *"ይህንን አድርግ፥ ያንን አታድርግ"* የሚላቸው ተቆጣጣሪ ባይኖርባቸው በጣም ደስ እንደሚላቸው የታወቀ ነው። ከሥርዓት ውጪ ሲሆኑ የሚቀጣቸው፥ ሲሳሳቱ የሚመልሳቸውና ወደ ትክክለኛው አቅጣጫ የሚመራቸው፥ በሕይወታቸው ሥልጣን ወይም ኃይል ያለው ሰው መኖሩ አስፈላጊ ላይመስላቸው ይችላል። መረዳት ያለባቸው ነገር ቢኖር ግን በሕይወታቸው ሥልጣን ያለው ሰው ማጣት፣ እርግማን እንጂ በረከት እንዳልሆነ ነው። እሁንም ሆነ ወደ ፊት በሕይወታቸው ደስተኛ ሆነው ለመኖር፥ ትክክለኛውን አቅጣጫ የሚያስይዛቸው፣ በተሳሳተ ጎዳና እንዳይሄዱ የሚመመክራቸውና የሚመራቸው፥ በእነርሱ ሕይወት ላይ ሙሉ ሥልጣን ያለው ሰው ያስፈልጋቸዋል። በአንድ "ሥልጣን" (autborlty) ሥር መኖር እግዚአብሔር የሚፈቅደው፣ እርሱ ራሱ የደነገገው በመሆኑ፥ ለሰው ልጅ በጣም አስፈላጊ ነው። ልጆች በወላጆቻቸው ይኸውም በአባታቸውና በእናታቸው ሥልጣን ሥር መኖር ይጠቅማቸዋል እንጂ አይጎዳቸውም። የወደፊቱ ሕይወታቸው ዕድገት ያለው፣ ደስታ የሞላበት እንዲሆን ምክንያት ይሆናቸዋል። ለጊዜው የፈለጉትን የማድረግ ነጻነት ይኑራቸው እንጂ፣ ከወላጆቻቸው ቁጥጥር ውጪ መኖርን የሚመርጡ ወጣቶች፣ ብዙ ጊዜ በብዙ ችግርና ጉዳት ውስጥ እንደሚያልፉ የታወቀ ነው። እግዚአብሔር ይህንን ስለሚያውቅ ነው ወላጆች በልጆቻቸው ሕይወት ውስጥ ሙሉ ሥልጣን እንዲኖራቸው የፈቀደው።

የማንኛውም አገር ዜጎች፥ በአገራቸው ውስጥ ሕዝቡን እንዲያስተዳድሩ ለተመረጡ (ለተመደቡት) ባለ ሥልጣናት ራሳቸውን ለማስገዛት ፈቃደኞች ሲሆኑ፣ ሕግ አክባሪዎች ሆነው በሥርዓት እንዲኖሩ ይረዳቸዋል። ለባለሥልጣናት "ሥልጣንን" የሚሰጥ እግዚአብሔር እንደ ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ጳውሎስ *"ማንኛውም ሥልጣን የሚገኘው በእግዚአብሔር ፈቃድ ስለሆነና አሁን ያሉትም ባለሥልጣኖች የተሾሙት በእግዚአብሔር ስለሆነ፥ ሰው ለመንግሥት ባለሥልጣን መታዘዝ አለበት። ስለዚህ ባለሥልጣንን የሚቃወም ሁሉ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ይቃወማል፤ የማይታዘዙም ሁሉ በራሱ ላይ የቅጣትን ፍርድ ያመጣል"* ይላል (ሮሜ 13፥1-2)። ማንኛውም ሥልጣን የሚገኘው ከእግዚአብሔር በመሆኑ፥ በብሉይ ኪዳን ዘመን ለባለሥልጣን አለመታዘዝ በሙሴ ሕግ የሞት ቅጣት ያስከትል እንደነበረ እናውቃለን። *"ጉዳያችሁንም ከሌዋውያን ወገን ካህናት ለሆኑትን በዚያን ጊዜ የበላይ አለቃ ለሆነው ፈራጅ አቅርቡ፤ ጉዳዩንም እነርሱ ይወስኑ። እነርሱም ከወሰኑላችሁ በኋላ እነርሱ ያዘዙአችሁን በትክክል ፈጽሙ። በሚሰጡአችሁ መመሪያና ውሳኔ መሠረት ሁሉን አድርጉ፤ ከዚያም ፈጽሞ ፈቀቅ አትበሉ። ዳኛውን ወይም በአገልግሎት ላይ ያለውን ካህን ባለመታዘዝ የሚዳፈር*

*ቢኖር በሞት ይቀጣ። በዚህም ዐይነት ሁኔታ እንደዚህ ያለውን ክፉ ነገር ሁሉ ከእስራኤል ታስወግዳላችሁ"*(ዘዳ. 17፥9-12)።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያለችውም ቤተ ክርስቲያን፣ የሚመራት መሪዎቿ ከጌታ ሥልጣን የተሰጣቸው ናቸው። እነዚህ ከጌታ ሥልጣን የተሰጣቸውን፣ "ገዢዎች" ወይም "አስተዳዳሪዎች" ተብለው ይጠራሉ። ሥልጣን የሚለውን ቃል፥ በግሪክ ቋንቋ "ኤክሶሲያ (exousia)፥ "ኤፒታጌ" (epitage)፥ "ሃይፐሮቼ" (hyperoche)" በማለት ተጠቅሰዋል (የማቴ. 21፥2፥ የሐዋ. 26፥12፥ 2 ቆር. 10፥8)።[46] ይህም ማለት ባለሥልጣናት፥ አንዳንድ ውሳኔዎችን ለማድረግ፥ ትዕዛዝ ለመስጠትና ለማስተዳደር (ለመግዛት) ፈቃድ (መብት) እንደተሰጣቸው ይገልጻል። ቲቶ ይህን ዓይነቱ ሥልጣን እንደተሰጠው ጳውሎስ ሲያስገነዝበው፥ *"እንግዲህ እነዚህን ነገሮች አስተምር፤ በሙሉ ሥልጣንም ምከር ገሥጻም፤ ማንም አይናቅህ"* ይለዋል (ቲቶ 2፥15)። ሥልጣን *"ከኃይል"* ጋር የተያያዘ ነው። ሥልጣን ተሰጥቶት ኃይል ከሌለው ዋጋ የለውም። ሥልጣን ያለው ማንኛውም ሰው፥ ትዕዛዝ ለመስጠትም ሆነ ለመቅጣት ኃይል ያለው መሆን አለበት። *"ኃይል"* የሚለው ቃል *"ዱናሚስ"* (dunamis) ከሚለው የግሪክ ቃል የወጣ ነው። *"ኃይል"* አንድን ነገር ለማድረግ ጉልበት ወይም ችሎታ ያለው ማለት ነው። ስለዚህ የኪንግ ጀምስ መጽሐፍ ቅዱስ *"ኤክሶሲያን"* ኃይል ወይም ሥልጣን ብሎ ይተረጉመዋል። "ሥልጣንና" እንዲሁም "ኃይል" ተመሳሳይነት አላቸው። የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ላሉት ምዕመናን ሁሉ ተሰጥቷል። መሪዎች ደግሞ መንፈስ ቅዱስ የሞላቸውን ምዕመናን እንዲመሩ፣ እንዲያስተዳድሩ ሥልጣን ወይም ኃይል ተሰጥቷቸዋል። ብዙ ጊዜ ችግር የሚፈጠረው፥ አንዳንድ አማኞች *"እኔ በመንፈስ ቅዱስ እንጂ በሰው አልመራም"* በማለት የራሳቸውን ፈቃድ ሲከተሉ ነው። እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ያልተረዱት እውነት ቢኖር፣ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ማለት "በራስ ፈቃድ መመራት" ራስን ከሌሎች አስበልጦ ማየት፥ እግዚአብሔር ቤቱን እንዲያስተዳድሩና እንዲመሩ ለመረጣቸው መሪዎች አለመታዘዝ ወይም ራስን አለማስገዛት እንዳልሆነ ነው።

## 3. ሥልጣንን አላግባብ መጠቀም ጎጂ ነው

*"ሥልጣን"* ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ነው። በእርሱ ፈቃድ የሕዝቡ መሪ እንዲሆኑ የተመረጡ ሰዎች፣ የመምራት ኃላፊነታቸውን መፈጸም እንዲችሉ የሚሰጣቸው ስጦታ እንደሆነ እናውቃለን። ይሁን እንጂ፥ ሥልጣን የተሰጣቸው አንዳንድ መሪዎች፥ የተሰጣቸውን ሥልጣን በአግባብ የማይጠቀሙበት ከሆነ፥ በሚመሯቸው ሰዎች ሕይወት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሲያደርሱ እንደሚችሉ የታወቀ ነው። ሥልጣን የተሰጣቸው መሪዎች ከመጠን በላይ ኃይለኞች ከሆኑ፥ ወይም የተሰጣቸውን ሥልጣን በአግባቡ ካልተጠቀሙበት፥ በሥራቸው ያሉትን ሰዎች በፍቅርና በርህራሄ ተሞልተው እየመሩ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው በማሳደግ ፈንታ "ጨፍልቀው" ሲገድሏቸው እንደሚችሉ ግልጽ ነው። አንዳንድ መንፈሳዊ መሪዎች ሥልጣናቸውን ያለአግባብ በመጠቀም የተከታዮቻቸውን አዕምሮ በመቆጣጠር፣ እንደ አምላክ እስከ መመለክ ደረጃ ለመድረስ የሞከሩ አሉ። መልካም የሆነውን፥ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የሰጠውን ስጦታ፥ አንዳንድ ሰዎች ያለአግባብ እንዲጠቀሙበት በመገፋፋት፣ ሰይጣን *"መንፈሳዊ ሥልጣንን"* የቤተ ክርስቲያን መጉጃ መሣሪያ አድርጎ ሲጠቀምበት ይታያል። ይኸውም፣ ሥልጣን ያላቸው አንዳንድ መሪዎች፥ ሥልጣናቸውን ያለአግባብ በመጠቀም የሚመሩትን ሕዝብ በማስጨነቅና በማስመረር ነው። በዚህ ዓይነት እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የሰጠው "መንፈሳዊ ሥልጣን" ለሕዝቡ ጥቅም እንዳይሆን ሰይጣን ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል። በሌላ በኩል ደግሞ ሰይጣን ሕዝቡን እንዲያስተዳድሩ እግዚአብሔር በመረጣቸው መሪዎች ላይ አንዳንድ ምዕመናን *"ለራሴ ብቁ ነኝ፤ ማንም አይመራኝም፤ ራሴን በራሴ መምራት እችላለሁ"* በማለት እንዲያምጹ ያደርጋል። ሰይጣን ይህን የሚያደርገው "መንፈሳዊ ሥልጣን" የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማስፋፋት አስፈላጊ መሆኑን ስለሚያውቅ ነው። በደስታ ራሳቸውን ለሚያስገዙትም ሆነ ለመምራት ኃላፊነት ለተሰጣቸው፣ "መንፈሳዊ ሥልጣን" ትልቅ በረከት ነው።



በብሉይ ኪዳን ዘመን፣ ከአይሁዳውያን መካከል መሪ እንዲሆኑ እግዚአብሔር ከጠራቸው ታላላቅ ሰዎች መካከል አንደኛው ሙሴ ነው። ይሁን እንጂ፥ በየጊዜው ሥልጣኑን የሚፈታተኑ ሰዎች ነበሩበት። *"የእስራኤል ሕዝብ ሙሴን 'በእኛ ላይ ገዥና ፈራጅ እንድትሆን ያደረገህ ማን ነው?' በማለት ተቃውመውት ነበር.."* (የሐዋ. 7፥35) ይላል። ለሙሴ በሕዝቡ ላይ ሥልጣንን የሰጠው ሰው ሳይሆን እግዚአብሔር ነው። ሥልጣኑ ከሰው እንዳልመጣ በልዩ ልዩ ምልክቶችና ድንቅ በሆኑ ነገሮች የተረጋገጠ ነው። ይሁን እንጂ፥ ሙሴ ሥልጣኑን የሚቀናቀኑ ሰዎች በዘመኑ ሁሉ አላጣም። በወቅቱ መረዳት ይሳናቸው እንጂ፣ በሙሴ ላይ ማጉረምረም ማለት፥ በመረጠው በእግዚአብሔር ላይ ማጉረምረማቸው እንደሆነ በደረሰባቸው ቅጣት ውስጥ ተገንዝበውታል። ስለዚህ ነው ሙሴ ሕዝቡን *"...በእኛ ላይ ስታጉረመርሙ እኮ በእግዚአብሔር ላይ ማጉረምረማችሁ ነው"* ያላቸው (ዘጸ. 16፥8)። እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ ከሰጣቸው ትእዛዛት ውስጥ *"በእግዚአብሔር ላይ የስድብ ቃል አትናገር፤ የሕዝብህንም መሪ አትስደብ"* የሚል ነበር (ዘጸ. 22፥28)። ይሁን እንጂ፥ ቆሬ ሕዝቡን በሙሴና በአሮን ላይ በማሳመጽ፣ ከፍ ዝቅ አድርጎ እንደሰደባቸው መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ቆሬ ሙሴን *"...እናንተ እኮ ከልክ አልፋችኋል! የዚህ ጉባኤ አባላት የሆኑት ሕዝብ ሁሉ ለእግዚአብሔር የተለዩ ናቸው፤ እግዚአብሔርም ከእኛ ሁሉ ጋር ነው፤ አንተ ሙሴ ታዲያ በእግዚአብሔር ጉባኤ ላይ ራስህን ከፍ ከፍ የምታደርገው ስለምንድነው?"* አለው (ዘኁ. 16፥3)።

[46] The Master Builder, Christian Equippers International, c1988.

የሙሴ እህት ሚርያም በሙሴ ላይ ቅሬታዋን ለማሰማት ፈልጋ "እግዚአብሔር የተናገረው በሙሴ አማካይነት ብቻ ነውን? በእኛስ አማካይነት ተናግሮ የለምን?" እንዳለች እናስታውሳለን (ዘኊ. 12፥2)። እርግጥ ነው እግዚአብሔር በሚርያምም በኩል ተናግሯል። ይሁን እንጂ፥ ሕዝቡን እንዲመራ እግዚአብሔር ሥልጣንን የሰጠው ለሙሴ ነበር። እንዲሁም በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉትም ምዕመናን በእግዚአብሔር ፊት ሁሉም ቅዱሳን ናቸው። እያንዳንዱ አማኝ የእግዚአብሔር ልጅ ነው። ይሁን እንጂ፥ እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ ሥልጣን እንዲኖራቸው አድርጎ የሚያስቀምጣቸው ሰዎች አሉ። ቤተ ክርስቲያን እንድትታነጽ ለብዙዎች የመንፈስ ቅዱስን ሥጦታ ሰጥቷል። ቢሆንም፥ በእነርሱ ላይ ሥልጣን ያላቸውን አንዳንድ ሰዎች ያስቀምጣል። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ መቀበል፥ "ለማንም ራሴን አላስገዛም! ለማንም ተጠያቂነት የለችም" ማለት የሚያስችል አይደለም። እሳት ያለቦታው የትም ተበትኖ ትልቅ ቃጠሎ እንዳያስነሳ፥ ምድጃው ውስጥ የሚቆሰቁሰው ሰው እንደሚያስፈልገው ሁሉ፥ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታቸውን በአግባቡና ስቦታው እንዲጠቀሙበት ሊረዳቸው የሚችል ሥልጣን ያለው ሰውም ያስፈልጋቸዋል። ዛሬ "የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ አለን" የሚሉ አንዳንድ አማኞች፥ "ማንም እኔን ዲሲፕሊን ሊያደርገኝ የሚችል የለም" በማለት የአምባገነንነት ጠባይ የሚያሳዩ አሉ። ይህን ዓይነቱ ባሕሪ ከመንፈስ ቅዱስ የሚመጣ ሳይሆን፥ የሥጋ ፍሬ ነው። "መንፈሳዊ ሥልጣን" አማኞችን የበለጠ ፍሬያማ ያደርጋቸዋል እንጂ፥ መንፈስ ቅዱስ በሰጣቸው ስጦታ እንዳይጠቀሙ አያደርጋቸውም።

ክርስቶስ በዓለም ውስጥ በነበረበት ዘመን፣ የእርሱንም "ሥልጣን" የተቃወሙ በዎች ነበሩ። ሥልጣን ከማን እንደሚሰጥ የሚያውቁ የሃይማኖት መሪዎችም ኢየሱስን "...በል እስቲ ንገረን! እነዚህን ነገሮች የምታደርገው በምን ሥልጣን ነው? ወይስ እነዚህን እንድታደርግ ሥልጣን የሰጠህ ማን ነው?" (የሉቃ. 20፥2) ብለው ይጠይቁት ነበር። መንፈሳዊ ሥልጣን የሚመጣው ከየት ነው? ሰይጣን ኢየሱስን በፈተነበት ወቅት ሲዋሽ፥ "...ይህን ሁሉ ሥልጣንና ክብር ለአንተ እሰጥሃለሁ! ይህ ሁሉ ለእኔ የተሰጠኝ ስለሆነ ለፈለግሁት መስጠት እችላለሁ" (የሉቃ. 4፥6) አለው። ይሄ እውነት ሳይሆን ውሸት ነው። ይህንን የሰይጣን ውሸት ያልተረዱ አንዳንድ በሥልጣን ላይ የተቀመጡ ሰዎች፣ የበለጠ ኃይልና ሥልጣን ለማግኘት ከሰይጣን ጋር ሲደራደሩ ወይም ሲዋዋሉ እናያለን። ኢየሱስ ሥልጣኑን ከየት እንዳገኘ ሲናገር፥ "...አብ ራሱ የሕይወት ምንጭ እንደሆነ፥ እንዲሁም ወልድን የሕይወት ምንጭ እንዲሆን አድርጎታል። የሰው ልጅ በመሆኑም ፍርድ እንዲፈርድ ሥልጣን ሰጥቶታል" ይላል (የዮሐ. 5፥26-27)። እንዲሁም የማቴ. 28፥18 ላይ "...ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጥቶኛል" አለ። ክርስቶስ የፈጸማቸውን ሁሉ ማድረግ የቻለው ከአብ ሥልጣን ስለተሰጠው ነው። ያስተማረው፥ እርኩሳንን መናፍስት ያስወጣው፥ ልዩ ልዩ ደዌ ያለባቸውን የፈወሰው፥ ከእግዚአብሔር ኃይልንና ሥልጣንን ስለተቀበለ ነው። ሥልጣኑን ሰው ስላልሰጠው፥ ሰው ሥልጣኑን ሊወስድበት አይችልም። ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱን ጥርቶ "...ርኩሳን መናፍስትን እንዲያወጡ፤ ደዌንና ሕማምን ሁሉ እንዲፈውሱ ሥልጣን ሰጣቸው" ይላል (የማቴ. 10፥1)። ሕዝቡን እንዲመራና እንዲያስተዳድር እግዚአብሔር ሥልጣን እንደሰጠው የሚያምን መሪ፣ ሰው ከሥልጣኔ ሊያባርረኝ ይችላል ብሎ መፍራት የለበትም።



በሐዋርያነት ሥልጣኑን የሚቀናቀኑ ሰዎች በጳውሎስም ላይ ተነስተውበት እንደነበረ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። "...እኔ ሐዋርያ አይደለሁምን? እኔ ጌታችንን ኢየሱስን አይቸው የለምን? እናንተስ በጌታ ኢየሱስ የሥራዬ ውጤት አይደላችሁምን? በጌታ የሐዋርያነቴ ማረጋገጫ ማኅተም እናንተ ስለሆናችሁ ለሌሎቹ እንኳ ሐዋርያ ባልሆን ለእናንተ ግን በእርግጥ ሐዋርያ ነኝ። የሐዋርያነት መብት የለህም ብለው የሚተቹኝ ቢኖሩ የምሰጠው መልስ ይህ ነው፤ እኔ ምግብና መጠጥ የማግኘት መብት የለኝምን? እንደ ሌሎች ሐዋርያትና እንደ ጌታ ኢየሱስ ወንድሞች እንደ ጴጥሮስም ክርስቲያን ሚስት አስከትዬ የመዞር መብት የሌለኝ እኔ ብቻ ነኝን?" አለ (1 ቆሮ. 9፥1-5)። የሐዋርያነት ሥልጣኑን የተቀበለው ከእግዚአብሔር በመሆኑ፣ ተቃዋሚዎች ቢነሱበትም፥ ጳውሎስ የሐዋርያነት አገልግሎቱን ከመስጠት ወደ ኋላ አላለም። ሥልጣኑን ከጌታ የተቀበለው በመሆኑ፥ በእርሱ እርዳታና ድጋፍ የተጠራበትን አገልግሎት እስከ መጨረሻው ድረስ መፈጸም ቻለ። እኛም ሥልጣን ከእግዚአብሔር እንደሚሰጥ አምነን ስንቀበል፥ የተሰጠንን ሥልጣንን በአግባቡ መጠቀም ስንችል፤ አገልግሎታችንን እስከ መጨረሻው ድረስ መፈጸም እንድንችል ኃይል እናገኛለን።

## 4. ሥልጣንን በአግባቡ ለመጠቀም መመሪያ የሚሆን

"ሥልጣን" ከእግዚአብሔር የሚሰጥም ቢሆን፥ አንዳንዶች የተሰጣቸውን "ሥልጣን" ያለአግባብ ሲጠቀሙበት ማየት በአሁኑ ጊዜ አዲስ ነገር አይደለም። እግዚአብሔር የሰጣቸውን ሥልጣን በአግባቡ ለመጠቀም፥ መሪዎች ሊከተሉት የሚገባ አንዳንድ መመሪያ ተሰጥቷቸዋል። ይኸውም፥

### 4.1. በገርነት ማቅናት

በመንፈሳዊ መሪዎች መታረም፥ ዲሲፕሊን መደረግ ለመንፈሳዊ ሕይወት ዕድገታችን ጠቃሚ ነው። በቤተሰብ ውስጥ ለሚያድጉ ሕጻናት፥ በሥራ ላይ ለተሰለፉ፥ እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ላሉ አማኞች ራሥን ሥልጣን በተሰጠው ሰው ሥር ማድረግ ጠቃሚነት አለው። በአግባቡ የሚፈጸም ዲሲፕሊን ዕድገትን ይጨምራል። "ልጆችን መገሠጽና መቅጣት ጥበብ እንዲያገኙ ያደርጋል፤ ልጅ ሰድ አደግ የሆነ እንደ ሆነ ግን እናቱን ያሳፍራል" ይላል (ምሳሌ 29፥15)። ልጆችን መገሠጽና መቅጣት አስፈላጊ

ይሁን እንጂ፥ ከአግባብ ውጪ ከሆነ ልጆችን ሊጎዳ እንደሚችል ማወቅ ይገባል። በምዕራቡ ዓለም አንዳንድ ወላጆች "ልጆቻችንን እንቀጣለን" በማለት በልጆቻቸው ላይ የአካልም ሆነ የሥነ ልቦና ጉዳት ሲያደርሱ በመንግሥት አስፈላጊው ቅጣት የሚፈጸምባቸው እንደሆነ እናውቃለን። "ቅጣት"፣ ዓላማውን የሳተውን፣ ከትክክለኛው መስመር ውጪ የወጣውን ሰው ለመመለስና ለማስተካከል እንጂ፥ ለመጉዳት አይደለም። ስለዚህ መንፈሳዊ ሥልጣን የተሰጣቸው ሰዎች፥ ምዕመናን ስቶ ሲገኝ፣ ከሥርዓት ውጪ ሲሆን በአግባቡ መገሠጽና መቅጣት ይገባቸዋል። ኃጢአት ሲለማመድ የሚያገኙትን አማኝ፥ አግባብ ያለውን ግሣጼና ቅጣት ሰጥተው በመመለስ ፈንታ፥ ከኅጢራሹ እንዳይገድሉት ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው።

- *"ወንድሞቼ ሆይ! ሰው ማናቸውንም ስሕተት አድርጎ ቢገኝ መንፈሳውያን የሆናችሁት እናንተ እንዲህ ዐይነቱን ሰው በገርነት አቅኑት፤ ነገር ግን አንተም በዚህ ዐይነት ፈተና እንዳትወድቅ ተጠንቀቅ" (ገላ. 6፥1)።*
- *"ለእንዲህ ዐይነቱ ሰው ከእናንተ አብዛኞዎቹ የፈረዱበት ቅጣት ይበቃዋል። ስለዚህ ይህ ሰው በጣም ከማዘኑ የተነሣ ተስፋ እንዳይቆርጥ ይልቅስ ይቅርታ እንድታደርጉለትና እንድታጽናኑት ይገባል። እንዲሁም እርሱ የምትወዱት መሆናችሁን ለማስረዳት እውነተኛ ፍቅራችሁን በሥራ አሳዩት" (2 ቆሮ. 2፥6-8) ይላል።*

እርግጥ ነው "ኃጢአት" ሳይታረም ማለፍ የለበትም። ኃጢአት ሳያድግና ሳይለመልም ቶሎ ቆርጦ መጣል ያስፈልጋል። ቆርጦ መጣል ስንል፥ ኃጢአትን እንጂ "ኃጢአተኛውን" ማለት አይደለም። ቆርጦ መጣል ያለበት ካንሰር የሆነውን "ኃጢአት" እንጂ፥ በካንሰር የተያዘውን በሽተኛ አይደለም። አንዳንድ መንፈሳዊ መሪዎች ይህንን ባለመረዳት *"በኃጢአት የደከመውን ወንድማቸውን"* ከኅብረቱ ቆርጠው ሲጥሉት ይታያሉ። ይሄም ማረምና ማስተካከል ሳይሆን፥ መግደል ነው። መንፈሳዊ መሪዎች ሲቀጡና ሲገስጹ በየዋህነትና በትህትና ሊያደርጉት ይገባል። ክፉና አደገኛ ሰው ቢሆንም፣ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ሊገድለው የሚያሳድደውን ሰው ማጥፋት ሲችል፣ ዳዊት በንጉሥ ሳኦል ላይ እጁን ማንሳት እንዳልፈለገ እናውቃለን። የዳዊት ዋና ምክንያት "እግዚአብሔር መርጦ ባስቀመጠው መሪ ላይ እጄን አላነሳም" በማለት ነው። መንፈሳዊ ሥልጣን ያላቸው መሪዎች ኃጢአተኛውን መገሰጽ ይችላሉ። ይሁን እንጂ፥ አግባብ ያልሆነ ፍርድና ቅጣት እንዳያስተላልፉ ግን ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው።

## 4.2. ፈዋሽ (ልዝብ) ምላስ ይኑራቸው

መንፈሳዊ ሥልጣን የተሰጣቸው መሪዎች ምላሳቸው የሚፈውስ እንጂ የሚገድል እንዳይሆን ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው። መንፈሳዊ መሪ ተደማጭነት ስላለው፥



ከአፉ የሚወጣው ቃል ለመስበርም ሆነ ለመጠገን ኃይል አለው። ስለዚህ ነው በዓለም ውስጥ ያሉ ትላልቅ ሥልጣን ያላቸው ሰዎች መግለጫም ሆነ አስፈላጊ ንግግር ሲያደርጉ በቅድሚያ ጽፈው ያዘጋጁትን በንባብ መልክ የሚያቀርቡት። ሰሚዎች የሰሙትን ነገር በፈለጉት አቅጣጫ ሊተረጉሙት ስለሚችሉ፣ መሪዎች ያልተናገሩትን እንደተናገሩ ሆኖ እንዳይቀርብ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው። መንፈሳዊ ሥልጣን ያላቸውም ሰዎች ንግግራቸው ጥንቃቄ የጎደለው መሆን የለበትም። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መልካምና ስለ ክፉ ምላስ ብዙ ይናገራል፥

- ***"የምትናገረው ሕይወትህን ሊያድን ወይም ሊያጠፋ ይችላል፤ ስለዚህ የንግግርህን ውጤት መቀበል ይኖርብሃል"*** (ምሳሌ 18፥21)።
- ***"ከመከራ ለማምለጥ ከፈለግህ ክፉ ከመናገር ተቆጠብ"*** (ምሳሌ 21፥23)።
- ***"ምላሱን ሳይቆጣጠር እግዚአብሔርን አመልካለሁ የሚል ሰው ራሱን ያታልላል፤ ሃይማኖቱም ከንቱ ነው"*** (ያዕ. 1፥26)።

መንፈሳዊ መሪ የሚመዘነው ተራ ንግግሩ ብቻ ሳይሆን፥ የሚሰጠው ምክር፥ መድረክ ላይ ሆኖ የሚሰብከው ስብከት፥ እንዲሁም *"የሠራዊት ጌታ እንዲህ ይላል"* ብሎ የሚተነብየውም ትንቢትም አንኳን በሚያዳምጡት ሰዎች ይመዘናል። የመንፈሳዊውን መሪ ቃል እንደ እግዚአብሔር ቃል አድርገው ስለሚወስዱ፥ አንዳንዶች በሕይወታቸው ትክክለኛ ያልሆነ ውሳኔ ወስደው ራሳቸውን ትልቅ ችግር ውስጥ የጣሉ ብዙዎች እንዳሉ እናውቃለን። እንዲሁም በአንዳንድ መንፈሳዊ መሪዎች ኃይለኛ ንግግር ምክንያት ከፍተኛ ጉዳት ደርሶባቸው ከክርስቶስ የተለዩ፥ ከክርስቲያን ሕብረት ሸሽተውና ርቀው የሚኖሩም እንዳሉ የታወቀ ነው። አንዳንድ መንፈሳዊ መሪዎች ጥረታቸው የእግዚአብሔርን ቤት ለማስተካከል እንጂ፥ ሆን ብለው ሌላውን ለመጉዳት እንዳልሆነ እርግጠኞች ነን። ይሁን እንጂ፥ ጥንቃቄ የጎደለው ንግግራቸው ከመጥቀም ይልቅ የበለጠ ጉዳት ሊያደርስ እንደሚችል ብዙ ጊዜ አይገነዘቡም። ስለዚህ መንፈሳዊ መሪዎች ብዙ ከመናገር ይልቅ ጥቂት ቃል አስበውና ተጠንቅቀው ቢናገሩ ይሻላል። ***"ጥቂት ቃል የሚናገር አዋቂ ነው፤ መንፈሱም ቀዝቃዛ የሆነ አስተዋይ ነው። ሰነፍ ዝም ቢል ጠቢብ ሆኖ ይቆጠራል፤ ከንፈሩንም የሚቆልፍ ባለ አዕምሮ ነው ይባላል"*** (ምሳሌ 17፥27-28) ይላል። *"እመክራለሁ፥ አስጠንቅቃለሁ"* ብሎ በራስ ተማምኖ፥ በሥልጣን ተመክቶ ከመናገር ይልቅ፥ ከሌላው መንፈሳዊ መሪ ጋር አስቀድሞ ስለ ሁኔታው መመካከሩ፥ ሌላውን ሰው ከመጉዳት ይጠብቃል። ሥልጣንን መከታ አድርጎ ያለጥንቃቄ መናገር ሌላውን ይጎዳል።

## 4.3. ጥሩ የሆነ ግንኙነት መፍጠር

"የመንፈሳዊ ሥልጣን" ጽኑ መሠረት፣ ጥሩ ግንኙነት የሚፈጥር እንጂ፥ *"በደረጃ መበላለጥ"* ምክንያት መለያየትን የሚያመጣ አይደለም። መንፈሳዊ መሪዎች የሚያስከብራቸው፣ ወይም ተቀባይነት የሚያስገኝላቸው የተለጣቸው "ሹመት" ሳይሆን፥ ከሕዝቡ ጋር የሚመሠርቱት ጥሩ ግንኙነት ነው። መንፈሳዊ መሪዎች፥ ከሚመሯቸው ወይም ከሚያስተዳድሯቸው ሰዎች ጋር ጥሩ ግንኙነት መመሥረት ትልቁ ኃላፊነታቸው ነው። አንዳንድ መንፈሳዊ መሪዎች ምዕመናኖቻቸውን በመጫን ወይም በማስጨነቅ ያላቸውን ደረጃ ወይም ሥልጣን ማስጠበቅ የሚችሉ ይመስላቸዋል። በዚህ ዓይነቱ መንፈስ ሌሎችን ዲሲፕሊን ለማድረግ ቢሞክሩ፥ የሚከተሏቸው ሰዎች ወደ እነርሱ በመቅረብ ፈንታ የበለጠ እንዲሸሿቸው ይሆናል። ማንኛውም አባት በልጆቹም ሆነ በሚስቱ ላይ ሥልጣን ሊኖረው የሚችለው ስለ እነርሱ በማሰብና በመጨነቅ እንጂ፥ ሥልጣንን በማሳየት ወይም እምባገነን በመሆን አይደለም። ልጆቹን በኃይል እያስጨነቀ እንዲታዘዙት ለማድረግ የሚሞክር አባት፥ ልጆቹ የበለጠ ይሸሹታል እንጂ አይቀርቡትም። የሚመራቸው ሰው ትክክለኛነቱን ካመኑበት፣ ብዙ ጊዜ ብዙዎች ምንም ያህል ዋጋ ቢያስከፍላቸውም፥ እግዚአብሔር ራዕይ የሰጠውን ሰው ተከትለው ለመሄድ ፈቃደኞች ናቸው። ያለአግባብ ሲገፉና ሲጨቆኑ ግን፣ ምንም ያህል ሥልጣን ያለው ሰው ቢሆን፣ "እሺ!" አይሉም። በኃይል ለመምራት ወይም ለማስተዳደር የሚሞክር መሪ የሚከተለው ሰው ማግኘት አይችልም። ከሰው ጋር ያለው ግንኙነት የተበላሸበት መሪ፣ ምንም ያህል ጥሩ ዓላማ፣ ከፍተኛ የሥራ ችሎታ ቢኖረውም፣ ተከታይ ስለማይኖረው ከሚፈልግበት ግብ መድረስ አይችልም። መንፈሳዊ መሪ ኃላፊነቱን መወጣት የሚችለው በኃይለኝነትና በእምባገነንነት ሳይሆን፥ በየዋህነት፥ በትህትና፥ እንዲሁም በርህሩህነትና በልስላሴ ነው። ጳውሎስ ሥልጣን የተሰጠው ለምን እንደሆነ ሲገልጽ፥ *"ጌታ ስለ ሰጠን ሥልጣን በጣም ብመካም አላፍርበትም፤ ምክንያቱም ይህ ሥልጣን የተሰጠን እናንተን ለማነጽ እንጂ ለማፍረስ አይደለም"* ይላል (2 ቆሮ. 10፥8)።

እርማትም ሆነ ግሳጼ ከመልካም ወዳጅ፥ ወይም ጥሩ ግንኙነት ካለን ሰው ከመጣ፥ ገንቢ እንጂ አፍራሽ ስለማይሆን በደስታ እንቀበለዋለን። ጠቢቡ ሠለሞን *"ወዳጅ ቢመታህም እንኳ ለመልካም ነው፤ ጠላት ግን አቅፎ ቢስምህም አትመነው"* ይላል (ምሳሌ 27፥6)። የሚሰጠው ግሳጼም ሆነ እርማት ምንም ያህል ትክክል ቢሆንም፥ በኃይለኛነት መንፈስ የተሞላውን መሪ መቀበልና መታዘዝ ያስቸግራል። መንፈሳዊ መሪ ሥልጣኑን ከእግዚአብሔር የተቀበለው ስለሆነ፣ መገሰጽ የሚገባውን ፊት ለፊት ለመገሰጽ ፍርሃት ሊኖርበት አይገባም። ቀዶ ጥገና እንደሚያደርገው ሀኪም በቂ ዝግጅት አድርጎ፥ በትክክለኛ ቦታ፥ በጥንቃቄና እንዲሁም ጊዜውን ጠብቆ ሊያደርገው ይገባል። ሥልጣን የሚሰ



ጠው ከእግዚአብሔር ስለሆነ፥ ግሳጼና እርማት ለማድረግ መሪው ከእግዚአብሔር ጋር በጸሎት አማካኝነት መማከር አለበት።

## 4.4. ተቀባይነት ማግኘት

እውነተኛ መንፈሳዊ ሥልጣን የሚገኘው፣ ሰዎች በፈቃደኝነት ራሳቸውን ሲሰጡ እንጂ፥ ሰው በራሱ ኃይልና ጉልበት በትዕዛዝ የሚያገኘው አይደለም። ምንም ያህል ሥልጣን ያለው ሰው ቢሆን፣ በግዳጅ ማንንም መምራት አይችልም። በጎች በራሳቸው በጎ ፈቃድ ይመራሉ እንጂ፥ ያለፈቃዳቸው ማንም ሊነዳቸው አይችልም። አማኞችም መንፈሳዊ መሪዎቻቸውን ለመከተልም ሆነ ላለመከተል የራሳቸው የሆነ ምርጫ አላቸው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አማኞች የሚኖራቸውን ነጻነትም ሆነ ምርጫ፣ ሊተላለፍ የሚችል ማንም የለም። አማኝ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊሰጠው የሚችለውን አገልግሎት የሚፈጽመው በራሱ በጎ ፈቃድና ሕሊና በመመራት እንጂ፥ ሥልጣን ባላቸው መንፈሳዊ መሪዎች ተገዶ ወይም ተገፍቶ አይደለም። ምዕመናን መንፈሳዊ ሥልጣን ያላቸውን መሪዎቻቸውን ተማምነው ራሳቸውን በፈቃደኝነት ሲያስገዙ፥ መሪዎችም ለሚመሯቸው ምዕመናን ራሳቸውን የሰጡ መሆናቸውን ማሳየት ሲችሉ፥ በመሪዎችና በተመሪዎች መካከል እውነተኛ አንድነት ሊኖር ይችላል። የእስራኤል ሕዝብ ከነአን ከመግባታቸው በፊት ሙሴ ለሕዝቡ እንዲህ የሚል ምርጫ ሰጥቷቸው ነበር። *"እነሆ እኔ በሕይወትና በሞት መካከል በእግዚአብሔር በረከትና መርገም መካከል ምርጫ አስጣችኋለሁ፤ በምታደርጉትም ምርጫ ሰማይንና ምድርን በእናንተ ላይ ምስክር አድርጌ አጠራለሁ፤ ስለዚህም እናንተና ዘርያዎቻችሁ በሕይወት ትኖሩ ዘንድ ሕይወትን ምረጡ"* (ዘዳ. 30፥19) አላቸው። ከሙሴ በኋላ የተተካውም ኢያሱ የእስራኤል ሕዝብ የራሱን ምርጫ እንዲያደርግ ጠይቋል። *"እርሱን ማምለክ መልካም መስሎ ካልታያችሁ ግን የቀድሞ አባቶቻችሁ ከኤፍራጥስ ወንዝ ማዶ በነበሩበት ጊዜ ያመልኩአቸው የነበሩትን ወይም አሁን በምድራቸው የምትኖሩባቸውን የአሞራውያንን አማልክት ታመልኩ እንደሆን የምታመልኩትን ዛሬውኑ ምረጡ፤ እኔና ቤተሰቤ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን"* (ኢያሱ 24፥15) አላቸው። የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አማኞችም ለቤተ ክርስቲያን ስለሚሰጡት አገልግሎት የራሳቸውን ምርጫ ማድረግ አለባቸው። ቤተ ክርስቲያኒቱን እንዲመሩ ሥልጣን ለተሰጣቸው መሪዎች ራሳቸውን አስገዝተው ከሌሎች አማኞች ጋር በአንድነት ለማገልገልም ሆነ ለመገልገል ፈቃደኞች መሆን አለባቸው። በተለያየ ምክንያት አንዳንድ ሰዎች መንፈሳዊ መሪዎች እንዲሆኑ ሥልጣን የተሰጣቸውን መሪዎች መቀበልና ራሳቸውን ማስገዛት ፈቃደኞች ካልሆኑ፥ ወደ ሌላው አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሄደው ማምለክና ማገልገል ሙሉ መ[illegible]ና ነጻነት አላቸው። ሰዎች ቤተ ክርስቲያናቸውን ጥለው ሲሄዱ በጣም ቅር ይላል። ይሁን እንጂ፥ አስፈላጊ የሚሆንበት ጊዜ አለ።

*የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ያለፈቃዳቸው በግድ እንዳይሄዱ ማድረግ አይችሉም፤ ተገቢም አይደለም።*

አንዳንድ ምዕመናን አንዳንድ ጊዜ መንፈሳዊ ሥልጣን ያላቸውን ሰዎች ምክራቸውንም ሆነ የሚሰጡትን መመሪያና ትእዛዝ፥ እንዲሁም የሚያስተምሩትን ትምህርት ለመቀበልና በተግባር ላይ ለማዋል ፈቃደኞች የማይሆኑበት ጊዜ አለ። በሚሰጡት ውሳኔ፥ በሚወስዱት እርምጃ ብዙ ጊዜ አይስማሙም። እንዲህ ዓይነቶቹ ቤተ ክርስቲያኒቱን ጥለው አይሂዱ እንጂ፥ በውስጣቸው ራሳቸውን ለመንፈሳዊ መሪዎች የሰጡና ያስገዙ አይደሉም። ይሄም ቢሆን "መሪዎቻችሁን ተቀበሉ" ብሎ ሊያስገድዳቸው ማንም የሚችል የለም። አንዳንድ አማኞች እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያኑን እንዲመሩ መንፈሳዊ ሥልጣን የሰጣቸውን መቀበልና ራሳቸውን በእነርሱ ሥር ማስገዛት ሲያቅታቸው፥ እግዚአብሔር በነርሱ አማካኝነት ሊሰጣቸው የሚያስበውን በረከት እንዳይቀበሉ ይሆናል። አንዳንድ አማኞች "እግዚአብሔር ለሙሉ ጊዜ አገልግሎት ጠርቶኛል" በማለት ለመሪዎቻቸው ሲያስታውቁ፥ መሪዎቹ ግን በነዚያ አማኞች ሕይወት ውስጥ ለአገልግሎት የሚያበቃ ጸጋ እንደሌላቸው፥ ወይም በችኮላ ምንም ዓይነት እርምጃ እንዳይወስዱ ሲመክሯቸው፥ "ምክራችሁን አንሰማም" በማለት "እምቢ!" ቢሉ፥ በማስገደድና በመጣላት ፈንታ፥

- *"ከእኛ ጋር በቆየህበት ዘመን ለአገልግሎት ብቃት እንደሌለህ እያወቅን ሌላ ቦታ ሄደህ አገልግል ማለት በበኩላችን ይከብደናል። ይሁን እንጂ፥ መሄድ አለብኝ ካልክ መሄድ ትችላለህ። ጌታ እንዲባርክህ፥ ሁሉም ነገር መልካም እንዲሆንልህ እንጸልይልሃለን"*

በማለት ፈቃዳቸውን እንዲፈጽሙ ነጻነት ሊሰጧቸው ይገባል። ይህን ሲያደርጉ "ነግረንህ ነበር" ለማለት እንዲያበቃቸው በመንገዳቸው መሰናክል እንዲገጥማቸው፥ ክፉ ነገር እንዲደርስባቸው በመመኘት መሆን የለበትም። መንፈሳዊ ሥልጣን ያላቸው መሪዎች የሚሰጧቸውን ምክርና አስተያየት መቀበል ፈቃደኞች ያልሆኑትን አማኞች ምንም ማድረግ አይቻልም። መንፈሳዊ ሥልጣን ጥቅም ላይ ማዋል የሚቻለው፥ ምዕመናኑ በፈቃደኝነት ራሳቸውን ለመሪዎች ሲያስገዙ፥ እንዲሁም መሪዎች ራሳቸውን ለምዕመናን መስጠት ሲችሉ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ የሐዋርያነቱን ሥልጣን መቀበል ላቃታቸው አንዳንድ ሰዎች *"...እግዚአብሔር እኛን ሐዋርያቱን ሞት ተፈርዶባቸው ወደሚገደሉበት ቦታ ከሚወሰዱት ሰዎች መካከል የመጨረሻዎቹ ያደረገን ይመስለኛል፤ ከዚህም የተነሣ በዓለም ሁሉ በመላእክትም ሆነ በሰዎች ፊት እንደ መጫወቻና እንደ መሳቂያ ሆነን እንታያለን፤ እኛ ስለ ክርስቶስ ብለን ሞኞች ሆነናል፤ እናንተ ግን በክርስቶስ ጥበበኞች ሆናችኋል፤ እንዲሁም እናንተ ብርቱዎች ሆናችኋል፤ እናንተ የተከበራችሁ ሆናችኋል፤ እኛ ግን የተዋረድን ሆነናል። አሁንም ቢሆን እስከዚህ ሰዓት ድረስ እንራባለን፤ እንጠማለን፤ እንራቆታለን፤ እንደበደባለን፤ መጠለያ በማጣት እንንከራተታለን።*



*በገዛ እጃችን እየሠራን እንደክማለን፤ ሲረግሙን እንመርቃለን፤ ሲያሳድዱን እንታገሣለን፤ ሲሰድቡንና ስማችንን ሲያጠፉ በጥሩ ቃል እንመልስላቸዋለን፤ እስከ አሁን ድረስ የዚህ ዓለም ውዳቂና የምድር ጥራጊ ጉድፍ ሆነናል"*አላቸው (1 ቆሮ. 4፥9-13)።

የሐዋርያው ጳውሎስ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አንጾኪያ ነበር። ባርናባስና ጳውሎስ ለአገልግሎት የተላኩት ከዚሁ ከአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ነው። ጳውሎስ በአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መንፈሳዊ ሥልጣን እንደነበረው ይታወቃል (የሐዋ. 13፥1)። እንዲሁም አዳዲስ በሚቋቋሙት አብያተ ክርስቲያናትም ላይ ጳውሎስ ሥልጣን እንደ ነበረው እናውቃለን። ይኸውም ሽማግሌዎችን በመሾም (የሐዋ. 14፥23፥ ቲቶ 1፥5)፥ ወደ ኋላ የተመለሱትን አማኞች ዲሲፕሊን በማድረግ (1 ቆሮ. 5፥1)፥ የሚሰበሰበውን የገንዘብ መዋጮ በመቆጣጠር (1 ቆሮ. 16፥1) የመሪነት አገልግሎቱን ይሰጥ ነበር። ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን በጻፈው መልዕክት ላይ እንደምንረዳው አንዳንድ ጊዜ ሐዋርያነቱን መቀበል ያቃታቸውን አንዳንድ ሰዎችን ለማሳመን ከፍተኛ ጥረት ያደርግ እንደነበረ እናያለን። ምክንያቱም ያለውን የሐዋርያነት ሥልጣን መቀበል ካልቻሉ፥ በእርሱ በኩል የሚመጣላቸውን በረከት መቀበል እንደማይችሉ ስለተረዳ ነበር። የእግዚአብሔር ቃል ስለ መንፈሳዊ መሪዎች ምን ይላል?

- *"... በሥልጣን ላይ ላሉ ሁሉ ጸልዩ" (1 ጢሞ. 2፥2)።*
- *"...በእናንተ መካከል በሥራ የሚደክሙትን፥ በጌታ ኢየሱስ አለቆቻችሁንና መካሪዎቻችሁ የሆኑትን እንድታከብሩአቸው እንለምናችኋለን" (1 ተሰሎ. 5፥12)።*
- *"...በሥራቸው ምክንያት ለእነርሱ ታላቅ አክብሮትን ፍቅር ይኑራችሁ..." (1 ተሰሎ. 5፥13)።*
- *"ማንኛውም ሥልጣን የሚገኘው በእግዚአብሔር ፈቃድ ስለሆነና አሁን ያሉትም ባለሥልጣኖች የተሾሙት በእግዚአብሔር ስለሆነ፥ ሰው ሁሉ ለመንግሥት ባለሥልጣን መታዘዝ አለበት" (ሮሜ. 13፥1)።*
- *"የእግዚአብሔርን ቃል በመጀመሪያ የነገሩአችሁን መሪዎቻችሁን አትርሱ፥ አኗኗራቸውንና ሥራቸውን በማስታወስ እምነታቸውን ተከተሉ" (ዕብ. 13፥7)።*
- *"ለመሪዎቻችሁ ታዘዙ፤ በሥልጣናቸውም ሥር ሁኑ፤ ምክንያቱም እነርሱ የሚጠየቁበት ኃላፊነት ስላለባቸው ስለ ነፍሳችሁ ጉዳይ ይተጋሉ፤ እናንተ ብትታዘዙአቸው እነርሱ ሥራቸውን በደስታ ያከናውናሉ፤ ያለበለዚያ ሥራቸውን በሐዘን ይሠራሉ፤ ይህም እናንተን የሚጠቅም አይሆንም" (የሐዋ. 13፥17)።*

- *"ቤተ ክርስቲያንን በደንብ የሚያስተዳድሩ፥ ይልቁንም የምሥራችሁን ቃል በመሰበክና በማስተማር የሚደክሙ ሽማግሌዎች እጥፍ ክብር ይገባቸዋል" (1 ጢሞ. 5፥17)።*
- *"ሁለት ወይም ሦስት ሰዎች ካልመሰከሩበት በቀር በቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ላይ የሚቀርበውን ክስ አትቀበል" (1 ጢሞ. 5፥19)።*

## 4.5. በአግባቡ ማስተዳደር መቻል

አንዳንድ ወላጆች ቤተሰባቸውን በኃይል ወይም ጨቁነው ማስተዳደር ይፈልጋሉ። እንቅስቃሴያቸው የሚያስፈራ፥ ኃይለኛና የራሳቸውን ፈቃድ በሌላው ላይ የመፈጸም ዝንባሌ ያላቸው ናቸው። ምክር በመስጠት ፈንታ ማዘዝ ይቀላቸዋል። በማስተማር ፈንታ ትዕዛዝ ይሰጣሉ። ስህተቱን በማስተካከል ፈንታ ይተቻሉ። ልጆቻቸውን በኃይል ለማስተዳደር የሚሞክሩ ወላጆች፥ ለልጆቻቸው ክፉ ጠባይ ምክንያት የመሆን ዝንባሌ አላቸው። አንዳንድ ወላጆች ኃላፊነታቸው፣ ልጆቻቸውን በሕብረተሰቡ ውስጥ ለራሳቸውም ሆነ ለሌሎች ጠቃሚ ዜጋ ሆነው መኖር የሚችሉበትን መመሪያ እየሰጡ በአግባቡ ማሳደግ እንደሆነ ይዘነጋሉ። ወላጆች በልጆቻቸው ሕይወት ውስጥ የማስተዳደርን ሥራ አንዲፈጽሙ እንጂ፣ በኃይል መግዛት፥ ሁሉን ነገር በቁጥጥራቸው ውስጥ ማድረግ እንዳልሆነ የተረዱት አይመስሉም። ወላጆች የእግዚአብሔር ባላደራዎች ስለሆኑ፥ በእግዚአብሔር ዘንድ ተጠያቂነት እንዳለባቸው ምንጊዜም ቢሆን መርሳት የለባቸውም። እንዲሁም በቤተ ክርስቲያንም ውስጥ እግዚአብሔር ቤቱን እንዲመሩ የመረጣቸውም መንፈሳዊ መሪዎች፣ የእግዚአብሔር ባላደራዎች ናቸው። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን እውነት ሲገልጽ፣ ***"እንግዲህ ሰው ሁሉ እኛን የክርስቶስ አገልጋዮች እንደሆንን የእግዚአብሔርን ምስጢር የመጋቢ ኃላፊነት የተሰጠንም ባለ ዐደራዎች እንደሆንን አድርጎ ሊቆጥረን ይገባል። ባለ ዐደራዎችም ታማኞች ሆነው መገኘት አለባቸው"*** (1 ቆሮ. 4፥1-2) ይላል።

ቤተ ክርስቲያንን የሚያስተዳድሩ መንፈሳዊ መሪዎች በእግዚአብሔር ልጆች ላይ "አምባገነን" መሆን የለባቸውም። በቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ውስጥ አምባገነንነት የሚታይ ከሆነ፥ ትክክል ያልሆኑ አንዳንድ ጤናማነት የሌላቸው ሁኔታዎች በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ መታየታቸው አይቀርም። ሰዎች መሪዎቻቸውን በፍቅር በመታዘዝ ወይም በመከተል ፈንታ ከፍርሃት የተነሳ፥ ደስ ሳይላቸውና ሳያምኑበት "እድርጉ" የተባሉትን ሊያደርጉ ይችላሉ። ይሁን እንጂ፣ "አምባገነን" የሆነ አመራር ወይም አስተዳደር፥ የቤተ ክርስቲያን አካል የሆኑት ክፍሎች፥ ደስ ብሏቸው እንዳያገለግሉ ነጻነት የሚከለክል መሆኑን መዘንጋት የለብንም።

- *አምባገነን የሆነ ሽማግሌ "በግድ ታዘዙኝ፥ በግድ ፍሩኝ" ይላል። አምባገነን መሪ የሌሎችን አሳብና ምክር መቀበል አይፈልግም። ጥሩ ሀሳብ የሚያቀርብ ሁሉ "ሥልጣኔን ይነጥቀኛል" ብሎ ስለሚፈራ፥ ጥሩ አሳብ ያላቸውን ሁሉ እንደ ጠላት በመቁጠር፥ በተለያየ መንገድ ገፍቶ ከሕብረቱ ለማስወጣት ዘዴ ይፈጥራል። አምባገነን የሆነ መሪ ሁልጊዜ ተጠራጣሪ፥ መልካምና በጎ የሆነውን ሁሉ አጨልሞ የሚያይ ነው።*



እንዲህ ዓይነቱ መንፈሳዊ መሪ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በግልጽ እንዳይታይ እንቅፋት ይሆናል። በፍቅርና በየዋህነት ሕዝቡን በማስተዳደር ፈንታ በኃይልና በግዴታ መምራት ይፈልጋል። ይሄም በመሪዎችና በምዕመናን መካከል ግጭትንና አለመተማመንን ያመጣል። ደቀ መዛሙርቱ፣ በአንድ ወቅት የሚያስተላልፉትን መልዕክት እንደጠበቁትና እነርሱ እንደሚፈልጉት ሕዝቡ ስላልተቀበላቸው፥ ከሰማይ እሳት ወርዶ እንዲያጠፋቸው ለኢየሱስ አሳብ እንዳቀረቡ እናስታውሳለን። ኢየሱስም በሁኔታቸው አዝኖ ***"...እናንተ ከምን ዐይነት መንፈስ እንደ ሆናችሁ አታውቁም፤ የሰው ልጅ የመጣው የሰውን ሕይወት ለማዳን ነው እንጂ ለማጥፋት አይደለም"*** አላቸው (የሉቃ. 9፥55)። መሪዎች ሕዝቡን ለመምራት በምን ዓይነት መንፈስ ውስጥ እንደሆኑ ሁልጊዜ ራሳቸውን መመርመርና መጠየቅ አለባቸው። ጳውሎስ የራሱን አቋም ሲገልጽ፥ ***"እናንተ በእምነታችሁ የጸናችሁ ስለሆናችሁ፥ እናንተን ደስ እንዲላችሁ አብረናችሁ እንሠራለን እንጂ በእምነታችሁስ አናዝዛችሁም"*** ይላል (2 ቆሮ. 1፥24)።

## 4.6. ከገንዘብ ፍቅር ነጻ መሆን

ስለ መንፈሳዊ መሪዎች ሥልጣን ስንወያይ፥ ገንዘብ ወይም ምድራዊ ብልጽግና በመሪ ሕይወት ውስጥ ሊያደርስ የሚችለውን አደጋ ሳንገልጽ ብናልፍ፥ ሥራችን የተሟላ አይሆንም። በአንዳንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መንፈሳዊ መሪዎች ያላቸውን ሥልጣን በመጠቀም መልካም ምስክርነት የማያስጥ ተግባር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሲፈጽሙ ማየት በአሁኑ ጊዜ በጣም የተለመደ ነው። ሙሉ ጊዜውን ለአገልግሎት የሰጠ ሰው ከሚያገለግላቸው ሰዎች ተመጣጣኝ የሆነ ቀለብ ሊሰፈርለት ይገባል ብዬ እምናለሁ። መጽሐፍ ቅዱስም ይደግፈዋል። ጳውሎስ ስለዚህ እውነት በሰፊው ጽፏል፥

- *"...የሚያበራየውን በሬ አፉን አትሰር ተብሎ በሙሴ ሕግ ተጽፎአል፤ ታዲያ እግዚአብሔር ይህን ያለው ስለ በሬዎች በማሰብ ነውን? እግዚአብሔር ይህን ያለው ስለ እኛ በማሰብ አይደለምን? የሚያርስ በተስፋ እንዲያርስ፥ የሚያበራይም በተስፋ እንዲያበራይ፥ በዚህ ዐይነት ሁሉም ድርሻውን እንዲያገኝ ይህ የተጻፈው በእርግጥ ስለ እኛ ነው። እኛ መንፈሳዊውን ነገር በዘራንላችሁ ከሆነ የእናንተን ሥጋዊ በረከት ብናጭድ ትልቅ ነገር መሆን ነውን? ሌሎች ይህን ነገር ከእናንተ የመካፈል መብት ያላቸው ከሆነ ታዲያ እኛ በዚህ የሚበልጥ መብት እንዴት አይኖረንም? እኛ ግን በዚህ መብት አልተጠቀምንም፤ ይህን ማድረጋችንም የከ*

*ርስቶስ የምሥራች ቃል ከመስፋፋት እንዳይገታ በማሰብ ሁሉን ነገር ታግሠን እንቻል ብለን ነው። በቤተ መቅደስ የሚያገለግሉ ምግባቸውን ከቤተ መቅደስ እንደሚያገኙና በመሠዊያው ላይ መሥዋዕት የሚያቀርቡና የሚያገለግሉ ከመሥዋዕት ተካፍለው እንደሚበሉ ታውቁ የለምን? እንዲሁም ደግሞ መልካም ዜናን የሚያበሥሩ ቀለባቸውን ከዚሁ ሥራቸው እንዲያገኙ ጌታ ኢየሱስ ደንግጓል" (1 ቆሮ. 9፥6-14)።*

ጳውሎስ ከመቄዶንያ አማኞች የተላከለትን ዕርዳታ እንደተቀበለ ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን በጻፈው መልዕክቱ ገልጿል (2 ቆሮ. 11፥9)። ይሁን እንጂ፣ በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት፣ በተለይ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንዳንድ ችግር ስለነበረ፣ ከቤተ ክርስቲያን ዕርዳታ በመቀበል ፈንታ ድንኳን እየሰፋ ራሱን ያስተዳድር እንደነበረ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል (የሐዋ. 18፥1-11)። ጳውሎስ አገልግሎቱ እንዳይነቀፍ ስለሚያደርገው ጥንቃቄ ሲጽፍ፥ *"አገልግሎታችን እንዳይነቀፍ በምን ነገር ለማንም መሰናከያ አንሆንም። ይልቅስ መከራንና ችግርን ጭንቀትንም እየታገሥን የእግዚአብሔር አገልጋዮች መሆናችንን በሁሉ በኩል እንገልጻለን..."* (2 ቆሮ. 6፥3) እንዲሁም ቁጥር 10 ላይ *"...ድሆች ሆነን ሳለ፥ ብዙዎችን ሀብታሞች እናደርጋለን፥ ምንም የሌለን ስንሆን፥ ሁሉ የእኛ ነው"* ይላል። ጳውሎስ ከሚያገለግላቸው ሰዎች የገንዘብ ዕርዳታ የመቀበል ሥልጣን እንደነበረው ግልጽ ነው። ይሁን እንጂ፥ ለወንጌሉ ዕንቅፋት ወይም መሰናከል ይሆናል ብሎ ስለሚያስብ፥ ድሃ ሆኖ መኖርን የመረጠ ሰው ነበር። ያለውን ሥልጣን ምድራዊ ብልጽግናን ለማትረፍ አልተጠቀመበትም። ያም በመሆኑ ስለ ራሱ ዝቅተኛ ስሜት የነበረው፥ ስለሚያጋጥመው የኑሮ ችግር የሚበሳጭ ሰው እንዳልነበረ ስሜቱን ሲገልጽ፥ *"...ያለኝ ነገር ይበቃኛል ማለትን ተምሬአለሁ። ስለዚህ ማግኘትንም ሆነ ማጣትን ዐውቃለሁ፤ በማንኛውም ቦታ ሆነ በየትኛውም ጊዜ የመጥገብንና የመራብን፤ የማግኘትንና የማጣትን ምስጢር ተምሬአለሁ። ክርስቶስ በሚሰጠኝ ኃይል ሁሉን ነገር ማድረግ እችላለሁ"* ይላል (ፊልጵ. 4፥11-13)። እርግጥ ነው ጳውሎስ በረሀብና በማጣት ብዙ ተንገላትቷል። ይሁን እንጂ፥ በችግሩ ጊዜ ሁሉ ከጌታ ትልቅ መጽናናትን አግኝቷል። መራራነትና ጥላቻ በውስጡ አልነበረም። በእጦት ምክንያት "አገልግሎቴን ማቆሜ ነው" ያለበት ጊዜ አልነበረም። ካልጠበቀው ሥፍራ የሚረዱትን ሰዎች ጌታ ይልክለት ነበር። እንደ ጳውሎስ "ያለነቀፋ ማገልገል እንፈልጋለን" የሚሉ እውነተኛ አገልጋዮች በኑሯቸው የተጎሳቆሉ ይሁኑ እንጂ፥ ደስ ብሏቸው የሚያገለግሉ አገልጋዮች በዘመናችን እንዳሉ እናውቃለን።

በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንድ መንፈሳዊ ሥልጣን ያላቸው ሰዎች ሥልጣናቸውን በመጠቀም በወንጌል ሲበለጽጉ ይታያሉ። እንዲህ ዓይነቶቹ ያሉት በአሁኑ ጊዜ ብቻ ሳይሆን፥ በብሉይ ኪዳን ዘመንም የነበሩ ናቸው። *"የከተማይቱም ሹማምንት የሚፈርዱት በጉቦ ነው፤ ካህናቱ ያለ ዋጋ አያስተምሩም፤ ነቢያቱም ያለ ገንዘብ ትንቢት አይናገሩም፤*



*ይህም ሁሉ ሆኖ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ስለሆነ ምንም ዐይነት ክፉ ነገር አይመጣብንም በማለት በእግዚአብሔር ይመካሉ"* (ሚክያስ 3፥11)። በአሁኑ ጊዜ በተለይ በሰለጠነው ዓለም ውስጥ በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት አካባቢ በሥልጣን ላይ ያሉ አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለመበልጸግ የሚጠቀሙበትን ዘዴ ስንሰማና ስናይ ልባችን በጣም ያዝናል። ከሚያገለግሏቸው ምዕመናን እጅ ለመንጠቅ የሚጠቀሙበት መንገድና ብልሃት ያስደንቀናል። ምዕመናኑ ከሚችለው በላይ እንዲሰጥ የሚጠቀሙበት ረቂቅ የሆነ የሥነ ልቦና ዘዴ እንኳን መለስተኛ የትምህርት ደረጃ ያለውን ሰው ቀርቶ በደንብ ተምሯል የሚባለውንም ሰው ሊያሞኝ የሚችል ነው። መጋቢው ከሚሰፈርበት ቀለብ ሌላ፥ "ዛሬ መጋቢያችንን እንባርከው፥ መኪናው አሮጌ ነችና አዲስ መኪና እንግዛለት፥.... ወዘተ." በሚሉ በመጋቢው የቅርብ ሰዎች አነሳሽነት፥ በየጊዜው "ገንዘብ አዋጣ" እየተባለ የሚጨቀጨቀው ምዕመን ያሳዝናል። ይሉኝታ በመፍራት ብቻ ከአቅሙ በላይ የሚሰጠው የእኛ ሰው ቁጥሩ ትንሽ አይደለም። አንዳንድ ሰዎች በግልም ሆነ በልዩ ልዩ ስጦታ ሊደሰሉ ስለሚችሉ መንፈሳዊ ሥልጣን ያላቸው ሰዎች ምን ዓይነት መሆን እንዳለባቸው መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል፥

- *"ከተጨማሪ ግን ችሎታ ያላቸውን ሰዎች መርጠህ በሕዝቡ ላይ የሺ አለቆች፥ የመቶ አለቆች የኀምሳ አለቆችና የዐሥር አለቆች አድርገህ ሹም። እነርሱ እግዚአብሔርን የሚፈሩ፥ እምነት የሚጣልባቸውና በጉቦም የማይደለሉ ሰዎች መሆን አለባቸው" (ዘጸ. 18፥21)።*
- *"ማጭበርበር ወይም ማድላት ወይም ጉቦ መቀበል በአምላካችን በእግዚአብሔር ዘንድ ከባድ ቅጣት የሚያስከትሉ ስለሆኑ እግዚአብሔርን በመፍራት ትክክለኛ ፍርድ ስጡ" (2 ዜና 19፥7)።*
- *"...የገንዘብ ፍቅር የክፉት ሁሉ ምንጭ ነው፤ አንዳንድ ሰዎች ገንዘብ ለማግኘት በመመኘት ከእምነት ርቀዋል፤ ልባቸውንም በሐዘን ጦር ወግተዋል" (1 ጢሞ. 6፥11)።*

መንፈሳዊ መሪዎች ጠቃሚ የሆነውን መንፈሳዊ ምግብ ሕዝቡን በመመገብ በትጋት ኃላፊነታቸውን መወጣት አለባቸው። የሚመግቡት ሕዝብ ቀለባቸውን ለመስፈር አቅም ባይኖረው፥ ሁሉን ማድረግ የሚችለውን ጌታ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ እንደሚሰጣቸው እምነው መጠበቅ አለባቸው።

ማንኛውም ድርጅት ሥልጣን ባለው ሰው ካልተመራ፣ ሁከት እንጂ ሥርዓት ያለው አመራር ሊኖረው አይችልም። እግዚአብሔር ዓለምንና በዓለም ውስጥ ያሉትን ሁሉ የፈጠረ፣ የንጉሦች ንጉሥ፣ የጌቶች ጌታ ስለሆነ፣ በማንኛውም ነገር ላይ ሙሉ ሥልጣን ያለው እርሱ ብቻ ነው። ንጉሥ ዳዊት ይህን እውነት ሲገልጽ፣ *"እግዚአብሔር ሆይ!*

*በሰማይና በምድር ያለው ሁሉ የአንተ ነውና፤ ታላቅነት፣ ኃይል፣ ክብርና ግርማ የአንተ ነው። እግዚአብሔር ሆይ! መንግሥትም የአንተ ነው፤ አንተም እንደ ራስ ከሁሉ በላይ ከፍ ከፍ ያልህ ነህ። ባለጠግነትና ክብር የሚገኘው ከአንተ ነው፤ አንተም የሁሉ ገዥ ነህ፤ ከፍ ከፍ ለማድረግ፣ ለሁሉም ብርታትን ለመስጠት ብርታትና ኃይል በእጅህ ነው" (1 ዜና 29፥11-12)* ይለናል። መንፈሳዊ ሥልጣንን ለሰው የሚሰጠው፣ በሁሉ ነገር ላይ ሥልጣን ያለው እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔርም ለልጁ ለኢየሱስ ክርስቶስ በሰማይና በምድር ሁሉ ላይ ሥልጣንን ሰጠው (ዮሐ. 17፥2)። የቤተ ክርስቲያንም ራስ አደረገው። የቤተ ክርስቲያን ራሥ የሆነውም ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ሕዝቡን እንዲመሩና እንዲያስተዳድሩ ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሥልጣንን ሰጣቸው። ስለዚህ፣ የመሪነቱን ሥልጣን ከእግዚአብሔር በተቀበሉ መንፈሳዊ መሪዎች ለመመራት ፈቃደኞች ካልሆንን፣ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ መኖራችን እንደሆን ማወቅ አለብን።



## ዋቢ ጽሁፎች


Anderson, Lynn. They Smell Like Sheep, Howard Publishing Co. West Monroe, Louisiana, 1997.

Barclay, William. By What Authority? (Valley Forge, Pennsylvania: Judson Press, 1974.

Bill, Effective Pastoring, 1968.

Blackaby, Henry & Richard. Spiritual Leadership, Broadman & Holman Publishers, Nashville, TN, 1960.

Dayton & Engstrom, Strategy For Leadership, Fleming H. Revell Co. Old Tappan, New Jersey, 1960.

Drucker, F. Peter. Foreword to The Leader of the Future, edited by Francis Hasselbein, 1996.

__________ The Effective Executive in The Executive in Action, Harper Business, New York, 1966.

Duewel, L. Wesley. Ablaze For God, Zondervan Publishing House, Grand Rapids, Michigan, c1989

Eisenhower, D. Dwight, Great Quates from Great Leaders, ed. Peggy Anderson (Lombard: Great Quatations, 1989)

Fant, D.J. A. W. Tozer, Christian Publications, Harrisburg, Pa, 1964.

Gangel, O. Kenneth. Lessons in Leadership From The Bible, BMH Books, Winona Lake, Indiana, 1980.

Getz, A. Gene. Elders and Leaders. Moody Publishers, Chicago, IL. 2003, p. 49.

__________. Sharpening the Focus of the Church. Scripture Publications, Inc. 1984, p. 183

Greenslade. Philip. Leadership, Greatness & Servanthood, Bethany House Publishers, Minneapolis, MN, 1984.

Hayes, Ed, The Church, World Publishing, Nashville, TN 1999 Lawrence,

Hocking, L. David. Be a Leader People Follow, G/L Publications, Glendale, California, 1979.

Klopp, Henry. The Leadership Playbook, Baker Books, Grand Rapids, MI, 2004

Hunter, Todd. "Successful Pastors: Are The Really Different" Equipping the Saints (Spring 1988).

Lawrence, Bill. Effective Pastoring, Word Publishing, Nashville, TN.1999.

MacArthur, John, Jr. Body Dynamics. SP Publications, Inc. Wheateon, ILL, 1982.

Morley, M. Patrick The Man In The Mirror, Wolgemuth & Hyatt, Publishers, Brentwood, TN. 1989.

Morris, H. Charles. The Christian Leader: Leadership Role, Publishers Association of the Philippines, 1980,

Newton, John. Voice of the Heart (Chicago: Moody Press, 1980.)

Ogden, Greg. The New Reformation, Zondervan Publishing House, Grand Rapids, Michigan, c1990

Sanders, Oswald J. Spiritual Leadership, Moody Press, IL. Chicago, c1967

_______. Quated in SamuelBrengle, The Soul-Winner's Secret (London: Salvation Army, 1918), 22.

Scheidler, Bill. The New Testament Church and Its Ministries. Bible Press, Portland, Oregon, 1980..

Shelley, Marshall. Well Intentioned Dragons, Bethany House Publishers, Minneapolis, MN, 1988.

Speed, B. Leas.. Mastering Conflict & Controversy. Multnomah, Portland, Oregon, 1973.

Swindoll R. Charles. Improving Your Serve, World Publishing, Dallas, TX 1981

The Master Builder, Christian Equippers International, c1988.

White. Ernest. The Desk of Decision, (Nashville: Church Administration, 1976).

Wogu, Melese. "የዘመናችን ቤተ ክርስቲያንና አገልጋዮቿ (ክፍል አንድ) 2008.